

# ጥቁር ነጥብ

## የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል (ቆንስላው) እና የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና

ዘላለም መንግሥቱ

ይህ ለሕትመት የተዘጋጀ መጽሐፍ አይደለም። በአንድ ጉዳይ ላይ ለ5 ዓመታት የተጻፉ አሳቦችና መጣጥፎች ስብስብ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ከተበታተኑ ቦታዎች የተባሉ ነገሮችን ከመፈለግ ከአንድ ቦታ መፈለግ የተሻለ በመሆኑ የሰበሰብኳቸው ናቸው።

በቆንስላው (የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) ላይ የተለያዩ ሰዎች በመደገፍም በመቃወምም ጽፈዋል። እኔ ገና ሳይመሠረት ለምሥረታው ወይም ለመጸነሱ ምክንያት የሆኑት 400 ሰዎች በቤተ መንግሥት በተጠሩ ቀን ጀምሮ በመቃወም ነው የጻፍኩት። ቆንስላው የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ጥቁር ነጥብ መሆኑን ከሚያምኑት ነኝ።

ጽሑፎቼን ሁሉንም ከፌስቡክ ገጼ እና ከዩቲዩብ በቪድዮ ያካፈልኳቸው ወደ ጽሑፍ ተመልሰው ነው እዚህ ያጋራኋቸው። እንደኔና ከኔም በላይ አምርረው የተቃወሙ መኖራቸውን አውቃለሁ። በመቃወም ይህን ያህል የጻፈ ሰው ከኖረ አላውቅም።

ሁሉም ፌስቡክ ገጼ ላይ የተለጠፉ ናቸው። ብዙዎቹ ብዙ አስተያየቶች ይዘዋል። እነዚያ አስተያየቶች እዚህ አልተካተቱም። አንዳንዶቹ አስተያየቶች ራሳቸው የመጣጥፍ ያህል ጉልበት ያላቸው ናቸው። ስድብ ከሆኑት በቀር አንዳቸውንም አልሰረዝኩም። አስተያየቶቹን ከስፍራቸው ለመመልከት በተለጠፉበት ቀን በገጼ ማየት ነው። የእያንዳንዳቸውን ቀን የጻፍኩት በተለጠፉበት ቀን ስለሆነ ለመፈለግ አያስቸግሩም። ሌሎች የጻፏቸውን በገጼ ያካፈልኳቸው አሉ። እነዚያን አላካተትኩም። በጣም ጥቂት አንድ ሁለቱን ብቻ አጋርቻለሁ። ጽሑፎቹን ሳይሆን ያጋራሁባቸውን ቀኖች ለማሳየት ያህል ነው።

እነዚህን የኔዎቹን ጽሑፎችም ጥቂት የማይባሉ ወገኖች በገጻቸው አካፍለውታል። የሌሎቹን አስተያየቶች በነሱ ገጾችም ማየት ይቻላል።

በአንድ ላይ በመጽሐፍ መልክ (June 2019) አንሥቶ እስከዚህ ድረስ (March 2024) የጻፍኳቸውን በመጽሐፍ ቅርጽ እነሆ አቅርቤላችኋለሁ።

ዘላለም መንግሥቱ

March 2024

June 20, 2019




ቤተ ክርስቲያን በምድር መንግሥት ላይ እንድትሠለጥን ቃሉ አያስተምርም። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የምትገኝና እስክትነጠቅ ድረስ የሰማዩ መንግሥት አስተዋዋቂም፥ ማስተዋወቂያ መድረክም ናት።

ምድራዊ መንግሥት ደግሞ በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የአደራ ሥልጣን በዜጎች ላይ መለማመድ አለበት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።

በክርስቲያኖች ጤናማ ፖለቲካዊ ተሣትፎና ሰልፈኝነት አምናለሁ።

https://www.youtube.com/watch?v=pY7VPqWPeXo

ይህ ሰኔ 13፥ 2011 (June 20, 2019) ቆንስላውን የመሠረተው የ400 ሰዎች ጉባኤ በቤተ መንግሥት ተጠርቶ በተቀመጠበት ቀን የጻፍኩት ነው። ልብ እንበል በዚህ የመጀመሪያ ቀን የሚመሠረተው ነገር ምንነት ገና ምኑም አልታወቀም። የኔ ፍርሃት ትንቢታዊ ወይም ነቢያዊ ፍርሃት አይደለም። ሲጀመር መሪዎች በአገር መሪ፥ በቤተ መንግሥት ተሰብስበው ሌክቸር ሲሰጣቸውና ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድ መሆን መመሪያ ሲተላለፍላቸው ነው። የኔ ፍርሃት የተጠሩት ሰዎች በምን መስፈርት ተጠሩ? እንዴትስ ይፋዊ ባልሆነ አጠራር ተጠሩ? እንዴትስ ያላስያዙትን አጀንዳ እንዲነጋገሩበት ተደረጉ? የሚል ነው። ያያያዝኩት የዩቲዩብ ማስፈንጠሪያ 'ክርስቲያን እና ፖለቲካ (ቤተ ክርስቲያን እና ፖለቲካ)' ክርስቲያንና ፖለቲካ በሚል ርእስ ያካፈልኩት ቪድዮ ነው። ክርስቲያን ፖለቲከኛ መሆን ይችላል፤ አለበትም። ግን በመጀመሪያ ክርስቲያን፥ ከዚያ ፖለቲከኛ መሆን እንዳለበት አምናለሁ። መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ሥራ ውስጥ ይህን በመሰለ መልኩ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ሕገ መንግሥቱም ደንግጎአል። ያ መጥጠበቅና መከበር አለበት ብዬ አምናለሁ።

June 22, 2019




እንደ ወትሮው ፊሽካ ነው የነፋሁት። ትንሽ ፊሽካ። (June 20 የለጠፍኩት ላይ ከጣልኳቸው አስተያየቶች)

አሁንም እላለሁ፤ ለመንግሥት አካላትም፥ ለሌሎችም፥ ለሁላችንም፤ ቤተ ክርስቲያን የኛ አይደለችም፤ የክርስቶስ ናት፤ ተውአት። ይህን ያልኩት ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። ይህ በገጼ ከዚህ ቀደም የተደጋገመ አሳብ ነው። በእውነቱ 'ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።' ለሚለው ለዚህ ጉዳይ ፪ሺህ ዓመት ያስቆጠረ ሰነድ በእጃችን አለና፥ ይህ ደግሞ ከማስረጃና ከአስረጂ ይበልጣልና ማስረጃ አያሻም።

ኢየሱስ ሰይጣን ነው ከሚል አሳች ጋር ኅብረት ማድረግ ከቶም አያስደነግጥም፤ ሲጀመር፥ መደረግ ስለማይችል። ተዘርፎ (ተሰርቆ) የመጣ ታቦት (እንደ ክብረ ነገሥት ትርክት ማለቴ ነው) መሳለም የሥልጣን ዕድሜ እንደሚያረዝም ከሚያምን አይኮሜኒስት (ኤክዩሜኒስት) ጋር ኅብረት ማድረግም አያስደነግጥም። ሊደረግ ስለማይችል። በቤተ እምነት ስም ሰው መንፈስ ነው፥ ኢየሱስ ለሠላሳ ዓመት ሰው ብቻ ነው እንጂ አምላክነት አልነካውም የሚሉ አሳቾች እና ስለ ቃሉ ዋጋ ከፋይ አገልጋዮች መደመር unity with out purity የሚሉት ነው። እንዲህ የመሰለ መደመር ለቤተ ክርስቲያን የተገባት አይደለምና፥ ቤተ ክርስቲያንን ይጎዳታል እንጂ አይጠቅማትምና፥ ሊተዋት ይገብባል። እርሷ የክርስቶስ ናት፤ ተውአት ያልኩት ያንን ነው።

መንግሥት ሕገ መንግሥት አለው። በዚያ ውስጥ ሃይማኖቶችን በተመለከተ ያወጣው አንቀጽ አለ። በምን ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዳለበት የሚናገር ግልጽ ንዑስ ክፍልም አለ። በዚያ መሠረት መተግበሩ አግባብ ነው እስማማለሁ። ተግባራዊ ያላደረገባቸው ነገሮች መኖራቸውም ሳይካድ ማለት ነው። ለምሳሌ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ከአንቀጽ ፳፯ ማለቴ ነው) መኖሩ የተረሳ ይመስላል። ሰው በሁለንተናው እየተጎዳ፥ እየተዘረፈ፥ እየታመመና እየሞተ ዝም ተብሏልና። መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጣልቃ አይገባም እና አይሠለጥንም የተለያዩ ናቸው። ጣልቃ ሊገባና ፈቃድን ሊያግድም

ይችላል፤ በደነገገበት ፍትሐ ብሔር። ሊሠለጥን ግን የተገባ አይደለም። መንግሥት ለሃይማኖት ተቋማት ያወጣው ጤናማ ሕግና ደንብ በሙሉ ጉልበት ቢተገብረው እንዴት በቂ በነበረ!

ሊሠለጥን የተገባ አይደለም ስል ባለ ሥልጣን መሆንን፥ ሥልጣንን ማሳየትን፥ የበላይ መሆንን፥ መግዛትን፥ መቆጣጠርን ነው። በቃሉ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በምድራዊ መንግሥት ላይ ስትሠለጥን አልታየችም። በቃሉ ውስጥ ነው ያልኩት፤ እንጂ በታሪክ ውስጥ አላልኩም። ምድራዊ መንግሥትም ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድድ እንጂ ሲሠለጥንባት አልታየም። አሁንም በቃሉ እንጂ በታሪክ ውስጥ አላልኩም። በታሪክማ ሆኗል፤ እየሆነም ነው፤ ይሆናልም። ያኔ ያልበረው ዛሬም ያ መሆን የለበትም ነው ነጥቤ። ቤተ ክርስቲያን እና መሪዎቿ በመንግሥታዊ መዘውር ውስጥ ገብተው መሽከርከር የለባቸውም። መንግሥት ቀድሞውኑ ሃይማኖቶችን የተመለከተ ያልወገነ ሕግ ደንግጓል፤ ያ በቂ ነውም። ምድራዊ መንግሥት፥ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን መንግሥትም ጨምሮ በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የአደራ ሥልጣን በዜጎች ላይ መለማመድ አለበት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም። ይህም ግልጽ ነው።

ኅብረትን በተመለከተ ቡናና ወተትም፥ ውኃና ዘይትም ኅብረት ሊያደርጉ ይችላሉ። ዕቃ ውስጥ እስካሉ ድረስ ምን ችግር አለ? ወደ አሁኑ አገልግሎት ከማለፌ በፊት ላለፉት በርካታ ዓመታት ከሠራሁት የኢንስፔክሽን ሥራ አንዱ ሦስት ነገሮች (ውኃ፥ ጋዝ ነዳጅ፥ እና ፈሳሽ ነዳጅ) የሚለዩበት separators ላይ ነበር። እነዚህ ኋላ በየፊናቸው አንዱ ወደ ላይ አንዱ ወደ ታች፥ አንዱ ወደ ጎን እስኪሄዱ ለትንሽ ጊዜ አብረው በጋኑ ውስጥ ይቆያሉ። ያም ኅብረት ነው። ኅብረት ምንም አዲስነት የለበትም ዕቃ ውስጥ እስካሉ ድረስ።

የኔ አመለካከት የግለ ሰብን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያሸበርቃል፤ I do celebrate seeing Christian politicians; in that order. Christians first, then politicians. እና አሁንም ያልኩት፥ 'ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።' ነው።

እንደ ወትሮው ፊሽካ ነው የነፋሁት። ትንሽ ፊሽካ።

September 10, 2019

እየፈራሁ መጣሁ።

በታሪክ ውስጥ የታየ እውነት የመሪዎች ሕልም (በእውነቱ ሕልም ሳይሆን ቅዠት ነው) የአገር ዜጎች አንድ ዓይነት እንዲሆኑ ነው። ልክ እንደ ዝንጀሮ አንድ መልክ እንዲኖራቸው። ለነገሩ ዝንጀሮዎች ለኛ (ለኔ) ነው አንድ የሚመስሉን እንጂ አይደሉም። አንዳንድ መሪዎች የዜጎች አመለካከት አንድ እንዲሆን ይሻሉ። አለባበሳቸውም ሳይቀር አንድ እንዲሆን የሚያስገድዱም አሉ። በኛው አገርም ተጀምሮ ነበር። አይገርምም? ልብስ እንኳ አንድ እንዲመስል! አሐዳዊ ማኅበረ ሰብ (unitary society ይሉታል) ለመፍጠር።

ሃይማኖታቸውም አንድ እንዲሆን መሻሉ። እዚህ ልል የምፈልገው ይህንን ነው። አስገድደው አንድ ሃይማኖት ብቻ የፈጠሩም አሉ። ኮሚኒዝምም ሃይማኖት ነው፥ በነገራችን ላይ።

እኔ መግሥትን ወይም የአገር መሪዎችን የእግዚአብሔር ቃል በሚያስተምረኝ መልክና ልክ አከብራለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህች መልካም አድርጎ የፈጠራት ዓለም ከወደቀች በኋላ የዚህችን ዓለም ዐዛባ መዛቂያ አድርጎ የሠራቸው ሦስት ተቋማት አሉ። ቤተ ሰብ፥ መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ። መንግሥት ከሦስቱ አንዱ ነው።

ቤተ ክርስቲያን መንግሥትን ወይም መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን ሊጎርሱ እጃቸውን ሲያስረዝሙና፥ ሊውጡ፥ ሊሰለቅጡ አፋቸውን እያያሰፉ ሲመጡ እየፈራሁ መጣሁትኝ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርና ጸሎት ሲጠየቁ ሳይሆን እንደ አራተኛ ክፍል ተማሪ ቁጭ ተደርገው ሲለከቸሩ ሳይ እየፈራሁ መጣሁ።

ኤኩሜኒዝምን እንደ አስፒሪን ከአንድ ስኒ ውኃ ጋር ዋጧት ሲባሉና ሲውጡ ሳይ እየፈራሁ መጣሁ።

በቃ የውነቴን ነው፤ እየፈራሁ መምጣቴን አልደብቃችሁም።

ዘላለም ነኝ።

ዘጠኝ ወር ሆነው ከተጸነሰ፤ ፌዴሬሽን እና ካውንስል የሚባሉ ስያሜዎች ብቅ አሉ።

February 29, 2020




ቤተ ክርስቲያን እጅ እጅ ልትሸት ነው።

በታሪክ እንደታየው መንግሥት እጁን፥ ቆሻሻ እጁን ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚከትትበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅ እጅ የምትሸት ቆሻሻ ትሆናለች።

ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ሲዋሸሙ (ቋንቋዩን ይቅርታ አድርጉለትና) የሚወለደው ዲቃላ ልክ ፈረስና አህያ ሲገናኙ እንደሚወልዱት ያለ በቅሎ ዓይነት ነው። በቅሎ መንቻካ፥ ዓመለኛ፥ ዳተኛ፥ ልግምተኛ፥ ተራጋጭ ፍጡር ነው/ናት። ከዚህ በላይ ደግሞ በቅሎ አትወልድም።

ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ሲጋቡ ልክ እንደ በቅሎ ዓይነት ትውልድ ይፈጠራል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ለተዘጋጀላት ቆንስላ (ወይም ፌዴሬሽን)ና በመንግሥት እጅ መነካካት ውስጥ ካለፈች እጅ እጅ እንደምትልና በቅሎ ትውልድ እንደምትወልድ ለመናገር ነቢይ መሆን የለብኝም።

በታሪክ ውስጥ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን፥ ቤተ ክርስቲያንም መንግሥትን ተዳፍረውም፥ ጠምዝዘውም ያውቃሉ። በየትኛውም ወገን፥ እርሷም ትግባ፥

መንግሥትም ይግባባት፥ ቤተ ክርስቲያን ከሁለቱም የምታተርፈው መቆሸሽን ብቻ ነው። መሠዊያ ላይ የሚደረገው ስነ መለኮታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንጽሕናና ወንጌል ነው።

በሰለጠነው አገር ውስጥ ቤተ ክርስቲያኖች ኅብረት ሲመሠርቱ በፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊና ስነ መለኮታዊ ምስስሎሽ ላይ ተመሥርተው ነው። በኛ አገር እየታየ ያለው ግን የነጻና ዲሞክራሲያዊ አገር ሃይማኖታዊ አካሄድ አይደለም።

ባለፈው ጽሑፌ፥ ቤተ ክርስቲያን ገበያም፥ ሰንበቴም፥ ዕድርም፥ ፓርቲም አይደለችም ብዬ ነበር። ደግሞም በተጨማሪ ያልኩት፥ ሐሰተኞችን ሁሉ በስመ ወንጌላዊነት አንድ በረት ውስጥ ተጠቅለሉ ማለት በጉንና ፍየሉን ብቻ ሳይሆን፥ እነዚህን ሁለቱን ከተኩላና ቀበሮ ጋር በአንድ በረት ማሳደር ነው። እንዲህ ያለውን በአንድ በረት ማደር ለተኩላው ይመቸዋልና ቢፈልገው ለምን ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። በጎቹ ደግሞ ከተኩላ ጋር ለማደር ቢፈሩ መፍራታቸው ለምን መሆኑ ገሐድ ነው። በጎች ስለሆኑ ማስገደድ ከተሞከረ እረኛ እንዳላቸው ባለመርሳት መሆን አለበት።

የአገር መሪዎች እንዲህ እንደ አሁኑ ቆንስላ (ፌዴሬሽን) ያለ ዛኒጋባ ሠርቶ ሁሉንም በአንድ ቆጥ ማስፈር ያስደስታቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትራችን እንዲህ ያለ አካሄድን ለምን እንደፈለገ በእውነት አላውቅም። በእውነት። ሕገ መንግሥታችን በግልጽ አንዱ በሌላው ጉዳይ መግባት እንደሌለበት ቢያሰፍርም ለይስሙላ ብቻ ነው? ይመስላል። ወይስ እንደ ሌሎቹ የሃይማኖት ተቋማት እኛም ሰልፋችንን አሳምረን ስንጠራም፥ ሳንጠራም አቤት እንድንል ነው የተፈለገው? ይመስላል። መንግሥት ሆይ! እባክህ መንግሥት ብቻ ሁን። ቤተ ክርስቲያንን ለጌታዋ ተዋት።

የወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ተሰባስባ በአንድ ቆጥ ላይ ተሸጋሽጋ እንድትሰፍር የማያስገድዳት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፤ ማወቂያችንን ጠብሰን ካላበላነው።

በቅሎ ትውልድና እጅ እጅ የምትሸት ቤተ ክርስቲያንን በቅርቡ እንጠብቃለን።

ዘላለም ነኝ።

March 8, 2020




March 9, 2020

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን እይታዬ ባጭሩ

ይህ የተዘጋጀው በቪድዮ ነው። የቪድዮው ሊንክ ይህ ነው፡

https://www.facebook.com/100009781051944/videos/1135994396736585

ይህ ቆንስላውን ቆንስላ በማለት መጻፍ የጀመርኩበት ነው። ተመርቆ ከመከፈቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ያካፈልኩት ነው። በቪድዮ ያካፈልኩት በጽሑፍ ሆኖ ነው።

. . . . .

የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን እይታዬ።

በፊታችን መጋቢት 2012 ተመርቆ የሚጀመረውን የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን እይታዬን አካፍላለሁ። 'ገና ምኑ ታየና ነው የምታካፍለው?' ካላችሁም፥ ሳያዩ ከሚያምኑት ወይም ከሚጠረጥሩት ጋር ደባልቁኝ።

ይህ እይታዬ ከምካቴ ክርስትና አንጻር መሆኑ ይስተዋል። ይህ የምለው ትንቢት አይደለም፤ እኔም ነቢይ አይደለሁም። እግዚአብሔር በንጹሕ ኅብረት፥ ባልተቀየጠ አንድነት፥ በግና ተኩላ አብረው በማያድሩበት የሰላም በረት ይባርከን። እንደ ምካቴ ክርስትና አገልጋይ የማየውን ልናገር እወድዳለሁ። ኅብረት ኅብረት! አንድነት!

ካውንስል! ፌዴሬሽን! በሚባልበት ሰሞን ከዚህ ወጣ ያለ ነገር መናገር ጸረ አብዮተኛነት ነው። ይህ ቆንስላ እስከሚመሠረትበት ድረስ ምንም ሌላ ነገር እንዲነገር የማይፈልጉ ሰዎችም አሉ። በአንድ የሚድያ ዝግጅት ላይ፥ 'ይህን የአንድነት ነገር ካልደገፋችሁ እባካችሁ ዝም በሉ እንጂ የነቀፋ ነገር አትናገሩ፤ ዝም ማለትም መደገፍ ነው። ዝም በሉ።' ብለው ነበር። በጣም እየገረመኝ ነው የሰማኋቸው። እውነት እንደዚያ ነው መባል ያለበት ወይስ፥ 'እስኪ ችግር ነው የምትሉት ነገር ካለ፥ ሥጋት የምትሉት ካለ አምጡና እንነጋገርበት ከምሥረታው በፊት።' ነው የሚባለው? ባህላችን ዱሮም ከዚህ የራቀ አልነበረም፤ አሁን ባሰበት።

ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያትን ስንቃወም ምንም የምትደግፉት ከሌላችሁ ዝም በሉ፤ አትንቀፉ ስንባል ነበር። ነቀፋ፥ ፍተሻ፥ ትችት፥ ሒስ የሚነቀፍበት ባህል ውስጥ ነን። ከሦስት ዓመት በፊት (በ2009) ትልቅ ፎረም ተዘጋጅቶ <u>የሕይወት፥ የአስተምህሮ፥ የአመራር ጥራት</u> በሚል እሳቤ ዙሪያ ሰፊና ጥልቅ ዳሰሳ የተደረገበት ሥራ ተሠርቶ ነበር። ሥራው መጽሐፍም ሆኖ ወጥቶ ነበር። አሁን የዚያ የመጽሐፍ ቀለም ገና ከመድረቁ በነዚህ ሦስት ዘርፎች ችግር ያለባቸው ሰዎች እና ማኅበራትም የፌዴሬሽን መሥራች ሆነው ነገሩ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ሲሆን ካልደገፋችሁ አትንቀፉ፤ ዝም በሉ ማለት ነውር ነው። ስለዚህ ነው ይህንን እይታዬን የማካፍለው። ጉዳዩ ለሰፊ ውይይት ቀርቦ ሳይሆን፥ ለምክክር ወይም ለክርክር ቀርቦ ሳይሆን እንዲያው፥ 'ተቀበል፤ ካልተቀበልክ አለመቀበልህን አታውራ!' ዓይነት ጉዳይ መሆኑ፥ ምን ያህል ኋላ ቀሮች፥ ወይም ጥሬ የዋሆች መሆናችንን ወይም ወደ ፊትም ወደ ኋላም አርቆ ተመልካቾች አለመሆናችንን እየተናገረ ነው። 'ተቀበል፤ ካልተቀበልክ ዝም በል' ነውር ነው።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን በቅርቡ ይመሠረታል። ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ይጠናቀቃል። መጋቢት 5 ለመሪ ምርጫ፥ መጋቢት 12፥ 2012 ለምረቃ ቀጠሮ ተይዞለታል። ይህ የማይቀር ውሳኔ ነው። ሳር እየተነሰነሰለት፥ ግምጃ እየተነጠፈለት፥ ከበሮ እየተደለቀለት፥ ነጋሪት እየተጎሰመለት ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን ልብሱ ተሰፍቶላታል።

በኔ እይታ ፌዴሬሽን ወይም ቆንስላው ለወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን ያለ ልኳ የተሰፋላት ቀሚስ ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህን ያለ ልኳ የተሰፋላትን ልብሷን ትለብሰዋለች። ያለ ልኳ የተሰፋ ልብስ መሆኑን ወዲያውኑ አታስተውለውም። ስለዚህ፥ ልብሱን ለመሙላት ወይ መነፋት ይኖርባታል፤ ወይም እርሷ በልብሱ ልክ ለመሆን መቀናነስና መከከርከም ይኖርባታል። ጠባብ ጫማ ከገዛህ ጫማህ ካልበቃህና አለመጫማትህ ምርጫ ውስጥ የማይገባ ከሆነ እግርህን በጥቂቱ መጠረብና መከርከም ግድ ይሆንበታል።

ከጥቂት ቀናት በፊት፥ 'ቤተ ክርስቲያን ገበያም፥ ሰንበቴም፥ ዕድርም፥ ፓርቲም አይደለችም' እና 'ቤተ ክርስቲያን እጅ እጅ ልትሸት ነው!' የሚሉ ሁለት አጫጭር ጽሑፎች አስነብቤ ነበር።

በሁለቱም ያቀረብኩት አሳብ ከሥጋት የተንደረደረ ነው። ያም ሥጋት ከጥያቄ ጋር የተለወሰ ነው። ጥያቄዬ፥ መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣልቃ የመግባት ግዴታ ወይም መብት ወይም ሥልጣን አለው ወይ? የሚል የሕገ መንግሥታዊነት ጥያቄ ነው። በአንቀጽ 27 እዝባር 5 እገዳ ስለሚደረግባቸው ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የተደነገገ፥ መንግሥት በሃይማኖታዊ ድርጅቶች ላይ እገዳ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው የተጻፈ አለ። እና መንግሥት ጣልቃ እንዲገባና እገዳ እንዲያደርግ አስገዳጅ ነገር ተፈጥሮ ነው መንግሥት ሊያስተባብር ጣልቃ የገባው? ደግሞም ይህ ምሥረታ እንጂ እገዳ አይደለምና መንግሥት ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን ምሥረታ የሚያደርግበት ልዩ ሥልጣን የተጻፈበት አንቀጽ አለ ወይ? አላየሁም። ምናልባት እንደ የኢኦተቤክ በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ከአንድ ሁለት በመሆኗ አድራጊው መንግሥት ያንን ማስተካከሉና በእስልምናም ተመሳሳይ ነገር በመደረጉና ያም በመስተካከሉ እዚህም አይቅር ነው አካሄዱ?

ቤተ ክርስቲያን ገበያም፥ ሰንበቴም፥ ዕድርም፥ ፓርቲም አይደለችም የሚለው ጽሑፍ በአጭሩ ይህ ነው፤

ቤተ ክርስቲያን ለሠርጓ ቀን እየጠበቃት ያለ ሙሽራ ያላት፥ እጮኛ ናት። ሙሽራዋ ደግሞ ጌታዋም ነው። ማንም ሰው፥ አለቃም ይሁን ምንዝር፥ የአገር መሪም ይሁን የዓለም መሪ ሊነካካት የተገባ አይደለም። የእርሷ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና በምንም መልኩ እርሷን መንካት ትልቅ ስሕተት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የአገር መሪ እንደመሆኑ አገርን በሕገ መንግሥቱ ቢመራ የተገባውን ኃላፊነት በተቀበለው ሥልጣን እየተወጣ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ሕገ መንግሥቱ ሊገድባት ከሚችለው ጉዳይ ውጪ ሊያመልክ ብቻ ነው መግባት ያለበት። አጥቢያው እንዲመራት ጠርታው ወይም መርጣው ወይም ሾማው ከሆነም ኃላፊነቱ ከዚያ አያልፍም። ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አካል እንጂ ክልል ወይም ዞን አይደለችምና በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ገብታ መዋቀር አትችልም። ምንም እንኳ በምድር ብትኖርም ጥሪዋና ተልእኮዋ ምድራዊ አይደለም።

ከዚህ በፊት በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ስም ወንጌላውያንም ወንጀላውያንም ተጠርተው አንድ ሁኑ ሲባል፥ 'ሰው መንፈስ ነው' ከሚሉ መናፍቃውያን፥ 'አክሱም ጽዮንን ይሳለሙ' ከሚሉ ኤክዩሜኒካውያን፥ መድኃኒት ከሚያስጥሉ፥ ሰዎችን እያስደበደቡ ከሚያጎሳቁሉ፥ ገንዘብ እየመዘበሩ፥ በጥቁር ገበያ እየመነዘሩ፥ ጸሎት እየሸጡ፥ ቁሳቁሶችንም እየሸጡ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ነቢያት ሐሰተኛ፥ ሐሰተኞቹን ነቢያት እውነተኛ እስከሚያደርጉት ድረስ በአንድ ቅርጫት ውስጥ ግቡና፥ ተሸጋሸጉና አንድ ሁኑ ሲባልና ባለ ፲፭ ሰው ግብረ ኃይል ሲመሠረት ከልብ አዝኛለሁ። ማዘኔንም ገልጫለሁ። ማዘኔም በመንግሥታዊ አካል ዕዝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔ የሚሹት እነዚህ መንፈሳዊ ችግሮች ሳይዳሰሱ አንድ ማኅበር እንዲመሠረት መሠረት እንዲጣል ሲደረግ ነው።

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአጥቢያ ማኅበርነት ወይም ጉባኤነት ላይ የሚያጠነጥኑ ስለሆኑ ማጠንጠኛ እንዝርታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነታቸው ነው

እንጂ ክልላዊ ወይም ጎሳዊ በሚመስል መልኩ፥ ወይም ፖለቲካዊ ወይም ማኅበራዊ በሚመስል ቅርጹ አንድ ሁኑ ማለት ከምን የመነጨ መሆኑ ቢጠየቅ እንደ ነውር መቆጠር የለበትም። ሐሰተኞችን ሁሉ በስመ ወንጌላዊነት አንድ በረት ውስጥ ተጠቅለሉ ማለት በጉንና ፍየሉን፥ ከተኩላና ቀበሮው ጋር በአንድ በረት ማሳደር ነው። እንዲህ ያለውን በአንድ በረት ማደር ተኩላው ቢፈልገው ለምን መሆኑ ግልጽ ነው። በጎቹ ደግሞ ቢፈሩ ሊፈረድባቸው አይገባም። በጎች ስለሆኑ ማስገደድ እረኛ እንዳላቸው መርሳት ነው። ይህ ስሕተት ነው። ጥራትና ንጽሕና፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ስነ መለኮታዊ አቋም በሌሉበት በጅምላ አንድ መሆን unity without purity is union እንደሚሉት ነው።

ማንም የአገር መሪ ሕዝቡ አንድ እንዲሆንለት ቢፈልግ አያስገርምም። የፖለቲካ መሪዎች እንዲህ ያለ ነገር የሚመኙት ነው።በሃይማኖታሓዳውያን አገሮች (አገዛዙና ሃይማኖቱ የተዋሃደባቸው unitary societies ለምሳሌ፥ በሸሪዓ በሚመሩ አገሮች) ይህ ለቁጥጥር የተመቸ አሠራር ነው። ለመሪዎች ይህ የሚመኙት ውቅር ነው።

የኛ መመሪያ ቃሉ እንጂ የሰለጠነው ዓለም ባይሆንም፥ በሰለጠነው ዓለም ከሚታየው እንማር ከተባለም፥ ቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ ቤተ መንግሥት የሚጋበዙት ምክር ለመስጠትና ለመጸለይ እንጂ ምክርና ትእዛዝ ለመቀበል አይደለም። ዶ/ር ዐቢይ የአብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችንና መሪዎችን ቤተ መንግሥቱንና ሌሎች ፕሮጄዎችን ማስጎብኘቱ መልካም ቢሆንም፥ 'አንድ ሁኑ!' ግን የእርሱ ኃላፊነትና ሥልጣን አይደለም። መድደመር ለሌሎች ብዙ ነገሮች መልካም ነው። ለቤተ ክርስቲያን ግን አይደለም።

ቤተ ክርስቲያን ገበያም፥ ሰንበቴም፥ ዕድርም፥ ፓርቲም አይደለችም።

ይህ የመጀመሪያው ጽሑፍ ነው። ኅብረት ሁሌም መልካም ገጽታ አለው። አንድነት፥ ትብብር፥ መተባበር፥ ኅብረት፥ ማኅበር መልካም ነገሮች ናቸው። በተለይ የዓላማ ትስስር፥ የዕርዮት አንድ መሆን ሲኖርበት መልካም ነው። በጫናና በግዴታ ሲሆን ግን ውጪያዊ አንድነት ብቻ ይኖራል። በዘመነ ደርግ የመጀመሪያ ዓመታት ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ነበሩ። ኢድህ እና ኢሕአፓ ወዲያው ቀጭጨው ቀረጨጩ፤ ተቀጩ ማለትም ይቻላል። ሌሎቹ እነ መኢሶን፥ ኢጭአት፥ ወዝሊግ፥ ማሌሪድ፥ አብዮታዊ ሰደድ፥ ሌሎችም ጥቂት ያሉበት አንድ ላይ እንዲሆኑና ኢማሌድኅ ተብለው ለመዋኃድ እንዲዋቀሩ በዕዝ ተሰባሰቡ። ኋላ ሰፊ አፍ የነበረው አንዱ ገሚሱን ውጦ፥ ገሚሱን ቀርጥፎ፥ ኢሠፓአኮ የሚባል ሥሪት ተፈጠረ። ኢሠፓአኮም አደራጅ ኮሚሽንነቱን ጨረሰ ተባለና ኢሠፓ ሆኖ እስከ ደርግ ፍጻሜ ድረስ ኖረና ሞተ።

ኅብረት መልካም ነው፤ መልካምም ላይሆን ይችላል። ኅብረት ቀላል ነው፤ ቀላልም አይደለም። መንፈሳዊ ኅብረትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ግንባር ቀደሙ ማኅበር የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር የሚባለው በ1950ዎቹ በሦስት ቤተ እምነቶች የተመሠረተውና እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ ድረስም የነበረው ነው። ደርግ እንደወደቀ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ተመሠረተ።

በመሠረቱ ኢወአክጎ ቤተ እምነቶችና ኢጋር ድርጅቶች የስደቱ ማግስት በገመደው ገመድ የተሳሰሩ እንጂ የተጠናና የጠለለ ኅብረትም አይደለም። እጅግ በጣም መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች የተጣመሩበት የላላ ማኅበር ብቻ ነው እንጂ ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ የተመሠረተ ኅብረትም አይደለም። አብያተ ክርስቲያናት ያልሆኑ ተጓዳኝ ድርጅቶችም ስላሉበት 'የአብያተ ክርስቲያናት' ኅብረትም አይደለም። ተባባሪ ሆነው የገቡ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያትም አሉበት።

እነዚህ ጉዳዮች ቸል ተብሎ መታለፍ ባይኖርባቸውም ይህ ኅብረት በተቻለው መጠን ከነድካሙም፥ ከነማዝመሙና ማዘንበሉም፥ ለአንዳንድ ጉዳዮችና ለአንዳንድ ሰዎች ከማጎብደዱም ጋር አስመስጋኝ ሥራ ሠርቶአል፤ እየሠራም ነው። አስመስጋኝ ሥራ እና ማዘንበል ያልኩት ሾልከው የገቡ አሳች አስተምህሮዎችን ለመጋፈጥ የተሞከረውን ሙከራና በአንዳንድ ረገድ ሾልከው በመግባታቸው ይህ መክሸፉን በማሰብ ነው። የቃለ እምነት (Word of Faith) ትምህርቶች ከቶም ወንጌላዊ እምነት ሳይሆኑ ኑፋቄዎች ናቸው። የወንጌል እምነትን እና የቃል እምነትን ማደባለቅ  እንደ ቅይጥ ኢኮኖሚ ከተወሰደ ትልቅ ስሕተት ነው። በቆንስላው ደግሞ ማንም ከማን ሳይለይ ሁሉም በ'ወንጌላዊ' እምነት ስም ወንበር ይዘዋል። ከዚህ በኋላ የቃለ እምነት አስተማሪዎችን ማንም፥ 'ይህ የስሕተት ትምህርት ነው፤ እገሌ ሐሰተኛ ነቢይ ነው' ማለት አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ስም ያበቀሉ ሐሰተኛ ነቢያት ንስሐ ሲገቡ አልታዩም። በቅርቡ የቤተ ክርስቲያን ታሪካችንም ስም ካበቀሉ የቃለ እምነት አስተማሪዎች ስም መጥቀስ ቢያስፈልግ፥ 'ተሳስቼ ነበር' ያለውና በዚያው ርእስ መጽሐፍ የጻፈው፥ ጂም ቤከር ብቻ ነው። እሱም ብዙ ሳይቆይ ወደ ሻጭነት ተመልሷል። ቤኒ ሂን ሥላሴ 9 ነው ብሎ በማግሥቱ፥ ሲያፋጥጡት፥ 'ይቅርታ!' ይልና በሣልስቱ ያንኑ የሚደግም ዮዮ እየተጫወተ የኖረ ሰው ነው። የሐሰት ነቢይነትና የሐሰት ሐዋርያነትና የቃለ እምነት ትምህርት መርዝ በቀላሉ የሚወጣ አይደለም። አሁን እየሆነ ያለው በስንዴውም በእንክርዳዱም ጋግረው፥ 'ቢቃ ተጋግሯልና ብሎ!' ነው። ጥያቄው፥ 'ከተበላ በኋላስ?' ነው። ላለመብላትስ፥ ወይም ላለመንከስ ምርጫ አለ?

ኅብረት እንዳልኩት መልካምም መልካም ያልሆነም፥ ቀላልም ቀላልም ያይደለም ነው። ጉዳዩ ማለትም ኅብረቱ የቤተ ክርስቲያን ከሆነ፥ መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊው እሴት ወደ ስሌቱ ውስጥ መግባቱና ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉ ደግሞ አጠያያቂ መሆንና ማስደንገጥ የለበትም። ያለዚያ በታሪክ ውስጥ እንደታየው ሰዋዊና መንግሥታዊ  እጅ ሲገባባት ቤተ ክርስቲያን እጅ እጅ ማለቷ የማይቀር ይሆናል። ባለፈው ባካፈልኩት በሁለተኛው አጭር ጽሑፌ፥ 'ቤተ ክርስቲያን እጅ እጅ ልትሸት ነው።'  ያልኩት ለዚህ ነው። ያ ጽሑፍ በጣም አጭር ጽሑፍ ነውና እንዳለ ላንብበው።

በታሪክ እንደታየው መንግሥት እጁን፥ ቆሻሻ እጁን ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚከትትበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅ እጅ የምትሸት ቆሻሻ ትሆናለች። ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ሲዋሸሙ (ቋንቋዬን ይቅርታ አድርጉለትና) የሚወለደው ዲቃላ ልክ ፈረስና አህያ ሲገናኙ እንደሚወልዱት ያለ በቅሎ ዓይነት

ነው። በቅሎ መንቻካ፥ ዓመለኛ፥ ዳተኛ፥ ልግምተኛ፥ ተራጋጭ ፍጡር ነው/ናት። ከዚህ በላይ ደግሞ በቅሎ አትወልድም።

ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ሲጋቡ ልክ እንደ በቅሎ ዓይነት ትውልድ ይፈጠራል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ለተዘጋጀላት ቆንስላ (ወይም ፌዴሬሽን) እና በመንግሥት እጅ መነካካት ውስጥ ካለፈች እጅ እጅ እንደምትልና በቅሎ ትውልድ እንደምትወልድ ለመናገር ነቢይ መሆን የለብኝም። በታሪክ ውስጥ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን፥ ቤተ ክርስቲያንም መንግሥትን ተዳፍረውም፥ ጠምዝዘውም ያውቃሉ። በየትኛውም ወገን፥ እርሷም ትግባ፥ መንግሥትም ይግባባት፥ ቤተ ክርስቲያን ከሁለቱም የምታተርፈው መቆሸሽን ብቻ ነው። መሠዊያ ላይ የሚደረገው ስነ መለኮታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንጽሕናና ወንጌል እራሱ ነው።

በሰለጠነው አገር ውስጥ ቤተ ክርስቲያኖች ኅብረት ሲመሠርቱ በፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊና ስነ መለኮታዊ ምስስሎሽ ላይ ተመሥርተው ነው [እንጂ በመንግሥት ጫናና ጣልቃ ገብነት አይደለም።] በኛ አገር አሁን እየታየ ያለው የነጻና ዲሞክራሲያዊ አገር ሃይማኖታዊ አካሄድ አይደለም። የአገር መሪዎች እንዲህ እንደ አሁኑ ቆንስላ (ወይም ፌዴሬሽን) ያለ ዛኒጋባ ሠርቶ ሁሉንም በአንድ ቆጥ ማስፈር ያስደስታቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትራችን እንዲህ ያለ አካሄድን ለምን እንደፈለገ በእውነት አላውቅም። ሕገ መንግሥታችን በግልጽ አንዱ አካል በሌላው ጉዳይ መግባት እንደሌለበት ቢያሰፍርም ያ አንቀጽ የሰፈረው ለይስሙላ ብቻ ነው? ይመስላል። ወይስ እንደ ሌሎቹ የሃይማኖት ተቋማት እኛም ሰልፋችንን አሳምረን ስንጠራም፥ ሳንጠራም አቤት እንድንል ነው የተፈለገው? ይመስላል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሆይ! እባክህ መንግሥት ብቻ ሁን። የኢትዮጵያን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንን ለጌታዋ ተዋት። የወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን ተሰባስባ በአንድ ቆጥ ላይ ተሸጋሽጋ እንድትሰፍር የማያስገድዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ያላት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፤ ማወቂያችንን ጠብሰን ካላበላነው።

በቅሎ ትውልድና እጅ እጅ የምትሸት ቤተ ክርስቲያንን በቅርቡ እንጠብቃለን።

እነዚህ ከላይ የጻፍኳቸው ሁለት አጫጭር ጽሑፎች የሥጋቴ ነጸብራቆች ናቸው። ከላይ እንዳልኩት ሥጋቴ በጥያቄ ቢቀመጥ፥ ጥያቄዬ፥ መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣልቃ የመግባት ግዴታ ወይም መብት ወይም ሥልጣን አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ነው።

ጣልቃ መግባት እንደማይችል ሕገ መንግሥቱ በግልጽ አስቀምጧል። የአገሪቱ ሕገ መንግሥት የሚለው ይህንን ነው፤

አንቀጽ ፲፩ የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

፩. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።

፪. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።

፫. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

የሕግ ባለሙያ ስላልሆንኩ እነዚህ ቃላት ምን ያህል እንደሚለጠጡ ወይም በአሠራር መርሁ (working policyው) ምን ማብራሪያ እንደተለጠፈበት አላውቅም። ለኔ ዓይነቱ መደዴ አንባቢ ግን ዐረፍተ ነገሩ ግልጽ ነው። መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት ጣልቃ አይገባም ነው። ሰኔ 13፣ 2011 ዓ. ም. 400 መሪዎችና አገልጋዮች መርጦ ጠርቶ ኮሚቴ መፍጠር (የምክረ አሳብ ግብረ ኃይል) እና በየካቲት 2012 1000 መሪዎችና አገልጋዮች መርጦ ጠርቶ ኮሚቴው በደረሰበት ምክረ አሳብ መሠረት አዲስ ማኅበር መሥርቱ ማለት የተለየ የተሻሻለ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር ጣልቃ ገብነት ነው እላለሁ።

ዜጎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎችና የሚተቿቸው ትችቶች ቦታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ዶ/ር ዐቢይ ሰው ሰው የሚሸትት፥ ሰው ሰው የሚል መሪ ነው። እስካሁን አገራችንን ከመሩት መሪዎች በቅደም ተከተል አስቀምጥ ብባል ቅድሚያ የምሰጠው መሪ ነው። ዜጋ በሆንኩበት አገር የአገር መሪን የምመርጠው፥ እርግጥ ሃይማኖታዊ አቋሙን ማወቅ ብፈልግም፥ ሃይማኖታዊ ጫና እንደማያሳድር ካመንኩ፥ በሃይማኖታዊ አቋሙ ሳይሆን የፓርቲውን ምድራክ (party platform) ገምግሜ ነው። የአገር መሪ እግዚአብሔርን የሚያምን እንዲሆን ብመኝም፥ አማኝ ሁሉ አማኝ ስለሆነ ብቻ መሪ ይሆናል ማለት አይደለም። ለመምራት መስፈርቱም ያ አይደለም። ዶ/ር ዐቢይን፥ ‘እስካሁን አገራችንን ከመሩት መሪዎች በሰልፍ አስቀምጥ ብባል ቅድሚያ የምሰጠው ነው።’ የምለው በሃይማኖት ስለምንመሳሰል ከቶም አይደለም። እንዲያውም አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ የጣልቃ ገብነት ቅዋሜዬን ወይም በጉዳዩ ላይ አቋሜን እየገለጥኩ ነኝ። መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ትልቅ ስሕተት ነው። መንግሥት ሃይማኖቶችን ሁሉ እንደ ሃይማኖት ተቋማት በእኩል ነው ማየት ያለበትና ፖሊሲ መቅረጽ ያለበት። ለየብቻ አዋጅና ድንጋጌ ማውጣት የለበትም።

በደስታ የተሸከምኩት ሸክም ሆኖብኝ የተሰለፍኩት በምካቴ ክርስትና መስክ ስለሆነ፥ ከምካቴ ክርስትና ዘርፎች አንዱ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ያልሆኑ ሐሳውያን ትምህርቶችን መጋፈጥ ስለሆነ የተኩላና የበግ መንጋ አንድ በረት ውስጥ ውለው ይደሩ ሲባል ቢያስደነግጠኝ ማስገረም የለበትም። እርግጥ ነው ኅብረት ሲባል ስሙም ደስ ይላል። ካውንስል፥ ፌዴሬሽን ሲባል ስሙ ያምራል። ምናልባትም የጋራ የሆኑ ማኅበራዊና አገራዊ ጉዳዮችን በአንድነት ሊደረጉ ይችላሉ። የካውንስሉ ዓላማዎች ተብለው የተቀመጡ 13 ነጥቦች አሉ። ከነዚህ መካከል . . . የታላቁ ተልዕኮን ግብ ማሳካት ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤ የወንጌል አማኞች እምነት ተከታዮች ድምጽ ሆኖ ማገልገል፤ በህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ችግር ሲፈጠር ችግሩ እንዲፈታ እና ሰላምና መቀባበል እንዲሰፍን ማድረግ፤ በሕገ መንግሥቱና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተከበሩ የእምነትና የሃይማኖት ነጻነት መብቶች እንዲረጋገጡ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ምርምር ማድረግ፤ ቤተ እምነቶች፥ ኅብረቶች፥ አገልግሎቶች እና አጋዥ ድርጅቶች ጥቃት ሲደርስባቸው አጥፊዎች እንዲጠየቁ ክትትል ማድረግ፤ በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር አለመግባባቱ

ክርስቲያናዊ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚፈታበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ወዘተ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ነገሮች ቆንስላው ወይም ፌዴሬሽኑ ባይኖር አይደረጉም ማለት ነው? መንግሥት እንደ መንግሥት ሊያደርግ የሚጠበቅበትን ነገሮች ይህ ካውንስል ሳይኖር አያደርግም ማለት ነው?

መሥራች አባላትም ቀድሞውኑ ታውቀው ሰርኩላር ተበትኗል። የካውንስሉ መሥራች አባላት 1. የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ፤ 2. የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፤ 3. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት፤ 4. የኢትዮጵያ ቪዥነሪ አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት፤ 5. የኢትዮጵያ ፔንቴኮስታል አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፤ 6. ሌሎች ያልታቀፉ ተብሎ ለምሳሌ፥ ቤዛ ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ሁለቱ ቤተ እምነቶች፥ ሦስቱ ኅብረቶች፥ አንዷ አጥቢያ ናት። አሁን ለማወቅ የቸገረኝ መስፈርቱ ምን መሆኑ ነው። ቃለ ሕይወትና መካነ የሱስ ቀድሞም በኢወአክኅ ውስጥ የነበሩና በአሠራር አለመስማማት የወጡ ናቸው። እርግጥ ትልልቆቹ ቢሆኑም ባይወጡ ኖሮ፥ ወይም ተመልሰው ቢሆኑ ኖሮ ሊጠቀሱም ባልተገባም ነበር። እና በመሠረቱ ካውንስሉ የኅብረቶች ኅብረት ነው? ወይስ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት? የመንፈሳዊ ድርጅቶች ኅብረት ነው ወይስ የክርስቲያናዊ አገልግሎቶች? የቤተ እምነቶች ወይስ የአጥቢያዎች? የሁሉም ይመስላል። ደግሞም፥ “በዚህ ደንብ አንቀጽ --- [አንዝ አልተጻፈም] ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ቤተ እምነት፤ ሕብረት፤ ወይም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ያሉት ሚንስትሪ የካውንስሉ አባል ሊሆን ይችላል።” ስለተባለ ከሚኒስትሪ እስከ ቤተ እምነትና ሌሎችም ኅብረቶችም አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

ከላይ መጠየቅ የጀመርኩትን ልቀጥል፤ መንግሥት በእውነት ይህ ቆንስላ ባይኖር የሃይማኖት ድርጅቶችን መብቶች ለማስጠበቅ አይችልም ማለት ነው? ወይስ ይህ ቆንስላ የመንግሥት እጅና ቅርንጫፍ ሆኖ ፈቃድ ሰጪ፥ ሕግ አውጪ እንዲሆን ነው የተፈለገው? እስካሁን በሕግ የተደነገገ አቋም ያላቸው ሁለት ሃይማኖቶች በአዋጅ አካልነት ተቀዳጅተዋል። በ1952 የኢኦተቤ/ክ፥ ዘንድሮ በ2012 ደግሞ እስልምና ሃይማኖታዊ ተቋም ሆነዋል። ሌሎቹ እንደ ሃይማኖት ድርጅት ሳይሆን እንደ ግብረ ሰናይ ድርጅት ወይም እንደ ማኅበር ነው እውቅናቸው። ይህ ሲጀመርም አድሏዊ አሠራር ነበርና ያንን ማስተካከል አይቻልም ኖሯል? ለእያንዳንዱ ማኅበር ለየብቻው አዋጅ መርቀቅና መጽደቅ አለበት ማለት ነው? ማለት፥ እዚህ ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን ውስጥ እና የትኛውም ውስጥ የሌሉ ሃይማኖቶች አሉ። ለምሳሌ፥ ካቶሊክ፥ አድቬንቲስት፥ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፥ ሞርመኖች፥ ወዘተ። ታዲያ እነዚህ ማኅበራዊ ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን ስለሌላቸው ሃይማኖታዊ መብት ይነፈጋቸዋል? አይነፈጋቸውም። ለነዚህ ለእያንዳንዳቸው የተለየ አዋጅ ይታወጃል? አይመስለኝም። ካልታወጀ ለነሱ የሚሠራው አሠራር ለነባሮቹ ቤተ እምነቶች ለምን አይሠራም? እነዚህ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ሳይሆኑ ሃይማኖታዊ አካላት መሆናቸውን ለማወቅ መንግሥት መመሪያ ወይም መስፈሪያ አድርጎ ቢያውጅ ምን ይከለክለዋል? በዚያ መልኩ መንግሥት ቆንስላ ሳያቋቁም ወይም እንዲቋቋም ሳያደርግ በሌሎቹ አገሮች በሚሠራበት መልኩ በሃይማኖታዊ ተቋማት ላይ ያለውን የራሱን መርህ ቀርጾ መሥራት አይችልም ኖሯል? የማይችል አይመስለኝም ወይም ይችላል። አጠቃላይ

ሃይማኖታዊ አዋጅ ወይም የእምነትና የሕሊና ነጻነት ድንጋጌ ታውጀ መሠራት አይቻልም ነበር? በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው ከሆነ ይቻላል።

ኅብረት እንዳልኩት መልካምም መልካም ያልሆነም፥ ቀላልም ቀላል ያይደለም ነው። የቆንስላው ተልእኮ (Mission Statement) የሚለው ይህንን ነው፤ 'የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያን ካውንስል ተልዕኮ ሕዝቦች ሁሉ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት እንዲቀበሉ እና ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠትና ማገዝ፤ የጋራ ችግሮች፤ ጥያቄዎችና በየወቅቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለሕጋዊ አካላት በማቅረብ እንዲፈቱ ማድረግ እና የአገሪቱ ሰላም እንዳይናጋ ለመከላከል፤ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሲያጋጥሙም የካውንስሉን አባላት በማስተባበር አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲሁም የአባላቱን የእርስ በርስ ግንኙነት ማጠናከርና መልካም ምሳሌነታቸው ጎልቶ እንዲታይ መደገፍ ነው።' ይላል። መርሆዎችና የጋራ እሴቶች ተብለው የተቀመጡም ነገሮች አሉ።

ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን ሳይኖር እነዚህ ነገሮች አልተደረጉም ወይ? ወንጌላውያን አማኞች በመቶ ዓመት ውስጥ ከ0 እስከ 25% የደረሱት በፌዴሬሽን አለመሆኑ ከታወቀ፥ ችግሮች ሳይኖሩ ቀርተው አለመሆኑም ከታወቀ፥ መንግሥት በጠቅላላው ሃይማኖቶችን የተመለከተ ድንጋጌን ማውጣትና ሁሉም በዚያው ድንጋጌ እንዲከናወን ማድረግ ለምን አላስፈላጊ ሆኖበት በእያንዳንዱ ሃይማኖትና ኅብረት ውስጥ መግባት ኖረበት? የቆንስላው መመሥረት እስካሁን የሆኑትን ችግሮች ሁሉ የሚገርዝ፥ ቅርፍ አድርጎ የሚያስወግድ አድርገው የሚያዩ ተስፈኞችም፥ የለም ችግሩ በመንግሥት እጅ የተጀመረ ስላልሆነ በመንግሥት እጅ የማይቀረፍ ነው የሚሉም እየተሟገቱ መቀጠል ይችላሉ።

ኅብረት መልካምም መልካም ያልሆነም፥ ቀላልም ቀላል ያይደለም ነው። በፓርቲዎች ኅብረት እንኳ ጤናማ ያልሆኑ ንጥረ ነገሮች ሊገቡ ስለሚችሉ ከግለሰብ ጀርባ እስከ አጋር ፓርቲ ዳራ ጥናትና ጥንቃቄ ይደረጋል። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ መንፈሳዊ አካል ናትና ችግሮቿም መንፈሳውያን ችግሮች ናቸው። መፍትሔዎቹም መንፈሳውያን፥ መጽሐፍ ቅዱሳውያን፥ ስነ መለኮታውያንና አስተምህሮአውያን ናቸው። መንግሥታውያን አይደሉም። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ሲወዳጁም ሲጣሉም መንግሥት ምድራዊ ስለሆነ በሚታይ ኃይል ስለሚጠቀም አሸናፊ የሚመስለው እርሱ ነው። ተጎጂዋ ቤተ ክርስቲያን ናት። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከነቆስጠንጢኖስ ዘመን ጀምሮ መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ መንግሥትነቱ ሲገባ ወይም እጁን ሲያስገባ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መልእክተኛ መሆኗ ቀርቶ የመንግሥት ተላላኪ ትሆናለች። አጀንዳዋም ይቀየራል ወይ ይበረዛል። በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሆነው ያ ነው። አሁን ያንን አንፈራ ይሆናል፤ ግን እባብ ያየ በልጥ ቢበረይ ለምን ያስገርማል?

400ዎች ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርተው፥ ባለ መድኃኒት ሆይ ራስህን ፈውስ ተብለው ስብሰባው ሲያበቃ 15 ሰዎች ያሉበት ግብረ ኃይል ተቋቋመ። እዚያ ውስጥ ለምሳሌ፥ ኢየሱስ ሰይጥኗል የሚል የተወገዘ ትምህርት ያላቸው ሰዎችም መኖራቸው በቀጣዩ የመፍትሔ ሂደት ውስጥ አስቀድሞውኑ ቅቡል ሊያደርጋቸው የሚችል ወይም ያደረጋቸው አካሄድ አይደለም ወይ? ነው። ይቅርታ መልካም እና መጽሐፍ ቅዱሳዊም

ነው። የአስተምህሮ ዝንፈት ግን በግል ይቅርታ የሚፈታ አለመሆኑን ማስተዋል አይጥፋብን። ለብዙዎች አካላዊና መንፈሳዊ ጉስቁልና እንዲሁም ሞት ምክንያት የሆኑ ኢመጽሐፍ ቅዱሳውያን ልምምዶች እልባትና መፍትሔ ሳያገኙ በአንድ ጎተራ ግቡና ተባበሩ ማለት በራሱ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አካሄድ ነው።

ለነገሩ መፍትሔ ከመፈለጉ በፊት ችግሩ መጤን፥ መጠናትና ችግር መሆኑ መረጋገጥ አልነበረበትም? ችግሩ ምንድርን ነው? የኅብረት ማጣት ነው? የመንግሥት ፈቃድ ለማግኘት ያለው የፈቃድ ምዝገባ ቢሮክራሲ ነው? የሕግ ባለሙያዎች እንዳሉት ይህ ጉዳይ በተቀላጠፈ መንገድ መካሄዱ ከሆነ ገና ወደፊት የሚፈጠሩትን የስሕተት ማኅበሮች አለማብዛቱ በምን ይታወቃል? በምንስ ይገደባል? ቤተ ክርስቲያን ራሷ ምንድን ናት? የማን ናት? ተልእኮዋስ ምንድን ነው? ይህ የምንነትና የማንነት (የማን መሆንነት) ከተጤነ መንግሥት እዚህ ውስጥ ሚናው ምንድርን ነው? ከመንግሥት ጋር ባለው ግንኙነትስ የተሰመረ መስመር አለ? ሲጀመር፥ መንግሥት የመሠረተው ወይም ያስመሠረተው ማኅበር መንግሥታዊ ነው? ወይስ ድርጅታዊ? ማኅበራዊ? ወይስ መንፈሳዊ? ይህ ቀዳሚ ጥያቄዬ ነው።

ዱሮ በነገሥታቱ ዘመን ቁራኛ የሚባል ሥርዓት ነበረ። ካልተሳሳትኩ በልጅ ኢያሱ ዘመን መሰለኝ እንዲቀር የተደረገው። ቁራኛ ማለት ወንጀለኛ ከተያዘ ለፍርድ እስኪቀርብ ድረስ እንዳያመልጥ ተብሎ ከከሳሽ ጋር ይቆራኛል። በሰንሰለት ሁለቱም አንድ አንድ እጅ ይታሰሩና እስከ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ በቀጠሮ ቢራዘምም፥ ለቀናትም፥ ለሳምንታትም፥ ለወራትም አብረው ታስረው ይቆያሉ። በዳይና ተበዳይ፥ ከሳሽና ተከሳሽ አብረው ታስረው ይሰነብታሉ፥ ይባጃሉ ወይ ይከርማሉ። እውነትን ከውሸት ጋር፥ የጸዱ አሳቦችን ለእውነት አንገታቸውን ከሚሰጡ ከቅዱሳን ጋር መደመር ሊታሰብ የሚቀፍፍ ነው።

አሁን ሁሉም ኅብረት፥ ማኅበር፥ አንድነት፥ ትብብር፥ መተባበር፥ መደማመር፥ ካውንስል፥ ፌዴሬሽን እያለ የዚህ ሁሉ ድምጽ የሌሎቹን ድምጽ የዋጠበት ጊዜ ስለሆነ በወጉ ጥያቄ ለመጠየቅ እንኳ መድረኩም፥ እድሉም የለም። ሚድያው ሁሉ ይህንን እንዲያናፍስ ማበረቻም ጫናም እየተደረገበት ነው። ብዙ የማኅበራዊ ሚድያ ሰዎች፥ ዩቲዩበሮችና ፌስቡከኞች ኅብረት ኅብረት! ካውንስል፥ ፌዴሬሽን! እያሉ ስለሚጮሁ ከዚያ በላይ ድምጽ አውጥቶ መጮህ አልተቻለም። ለመሆኑ አስፈላጊ ነው ወይ? ማለት አሁን ነውር መስሏል። ያለጥያቄ ኮሚቴ ተዋቀረ፤ ያለጥያቄ የኮሚቴው አሳብ ጸደቀ፤ ያለጥያቄ ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን ተመሠረተ፤ ያለጥያቄ 2500 መራጮች በተገኙበት የፊታችን ቅዳሜ ምርጫ ተደርጎ በወዲያኛው ሳምንት በይፋ ሊመረቅ ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን መደበኛ አሠራር ነው ወይስ የመንግሥት? እንደዚህ ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ነው ዕድሉ ያልነበረው። እና ነጻ ውይይት ያልነበረበት ሪፖርት የቀረበው።

መቼም፥ ኅብረት፥ ማኅበር፥ አንድነት፥ ትብብር፥ መተባበር፥ ካውንስል፥ ፌዴሬሽን በሚባልበት ጊዜ፥ እነ ጳውሎስን፥ እነ ዮሐንስን መጥቀስ እንደ ነውር ሳይታይ አይቀርም።

ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። (2ተሰ. 3፥6)

ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ (ሮሜ 16፥17)

ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና። (2ዮሐ. 10)

እንደዚህ ያሉትን፥ የመሰሉትን ጥቅሶች መጥቀስ በአብዮት ወቅት ጸረ አብዮተኛነት ነው። መግቢያው ላይ ያልኳቸው የሚድያ ሰዎች እንዳሉት፥ 'ይህን የአንድነት ነገር ካልደገፋችሁ እባካችሁ ዝም በሉ እንጂ የነቀፋ ነገር አትናገሩ፤ ዝም ማለትም መደገፍ ነው። ዝም በሉ!' ነው የሚባለው። 'ምርጫው አንድና አንድ ብቻ ነው፤ አማራጭ አያስፈልግም' ነው ነገሩ።

ይህ ከላይ ያልኩት ትንቢት አይደለም፤ እኔም ነቢይ አይደለሁም። ይህ እይታዬ ከምካቴ ክርስትና አንጻር መሆኑ ይስተዋል። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ቆንስላ ወይም ፌዴሬሽን አመሠራረትና አካሄድ ላይ የራሴን መረዳት ይህን ከላይ ያልኩትን የሚመስል ነው። የራሴ መረዳት ስል ወከዬ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

እግዚአብሔር በንጹሕ ኅብረት፥ ባልተቀያየጠ አንድነት፥ በግና ተኩላ አብረው በማያድሩበት በሰላም በረት፥ በሰላም ጋጣ፥ በሰላም ግርግም ይባርከን። አሜን።

አመሰግናለሁ።

March 13, 2020 ጀምሮ የዣንጥላው ነገር በሚል አጫጭር ነገሮችን መለጠፍ ቀጠልኩ።

የዣንጥላው ነገር . . . የቆንስላው ነገር። 1




የሃይማኖትና የሕሊና ነፃነት፥ ተሰብስቦ ማምለክም እኮ የዜግነት መብት ነው። በስደት ውስጥ ስለኖርን (መንግሥታዊ ፖሊሲን በተመለከተ እስካሁንም ጭምር) መብትም አልመስል ብሎን ዣንጥላውን መብት አስከባሪ አድርገን እያየን ነን፤ አድርገው እያሳዩን ስለሆኑ።

ወንጌላውያን አማኞች አስቀድሞም አድልዎ ያለበት ሕገ መንግሥት በራሱ ሊያስተካክል የሚችለውን የሃይማኖት አካልነት መብት፥ የማምለክ ፈቃድ ማግኘት፥ የአምልኮ ቦታ በነጻ የማግኘት፥ . . . መብት፤ ለሌሎች የመጠንቀቅ፥ የመድረስ፥ የማገዝ ሳምራዊ ግዴታ፥ ከጌታ በአደራ የተሰጠንን የታላቁን ተልእኮ ኃላፊነት ለመወጣት የግድ በአንድ ዣንጥላ ስር መሆን የለብንም።

ሰማያዊ ዜግነታችን በልጦብን የምድሩን አለመጓጓታችን ጌታን የመምሰል ትሕትና እንጂ ሞኝነት አይደለም። ቤተ ክርስቲያናችንም ሬሳችንም ሲቃጠል ዝም ማለታችን

ዘላለማዊው መብለጡን ማወቃችን እንጂ መብታችንን አለማወቃችን አይደለም። እኛ ዝም ስላልን መንግሥትም ዝም ማለት ግን አልነበረበትም። ዝም እንዳይል አንድ ዣንጥላ ስር ሆነን ሰላማዊ ወይም የተቃውሞ ሰልፍ መውጣት አልነበረብንም።

መንግሥት እስከዛሬ ያላደረጋቸውን ወይም ምናልባት ሊያደርግ ያልቻላቸውን የራሱን ሽንቁሮች እንዳናይ ዣንጥላውን መብት አስከባሪ አድርገን እንድናይ እያደረጉን ነው።

የዣንጥላው ነገር።

March 14, 2020

የዣንጥላው ነገር . . . የቆንስላው ነገር። 2




ብዙ ሚሊየኖችን የሚወክሉ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ጉባኤ ለመጥራት ፈቃድና ሕጋዊነት ያለው አካል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? ወይስ እንደ ሰላማዊ ሰልፍ ጥቂት ሰዎች ወጥተው አሳባቸውን አሳውቀው መመለስ ይችላሉ? ይህ ደግሞ ያንን አይመስልም። ቋሚና ዘላቂ የሚመስል ነገር መሥራች ጉባኤ ነው።

የተጠሩት ታዳሚዎችስ በመጥሪያ ደብዳቤ ነው ወይስ በቃል ጥሪ ነው? ለምሳሌ፥ ታጋባዦች፥ ዘማሪዎች፥ ትልቅ ጉባኤ የሚያህል የመዘምራን ቡድንም ጭምር፥ ተናጋሪዎች፥ እና ሌሎችም ተጋብዘዋል። በተዋረድ ወደ ታች ጥሪውን በቃል የሚነግሩት የአብያተ እምነት መሪዎች ሲሆኑ እነሱ ራሳቸውም የተጻፈ ሕጋዊ መጥሪያ የላቸውም። ጋባዡ ግን ሕጋዊነት እና አካልነት ያለው ነው ወይስ ጥላ ብቻ ነው?

መንግሥት መንፈሳዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሥራዎቹን outsource ያደርጋል ማለት ነው?

መቼም በዚህ ጉዳይ መጠየቅን የመሰለ ደግም ክፉም ነገር የለም።

የዠንጥላው ነገር።

March 16, 2020

የሆንጥላው ነገር 3




የትብብር ምክረ አሳብ አመንጪ ኮሚቴው በእውነቱ ኃላፊነቱ አሳብ አመንጭቶ፥ ዘጠኝ ወር አርግዞ የወለደውን ለመረጠው አካልና ለዚያ አካል ብቻ አቅርቦ መፍረስ ነበረበት። ግን በዘመነ ግርንቢጥ አንድ አካል ወክሎ ኃላፊነት ይሰጣል፤ የተሰጠው አካል ኃላፊነቱን ፈጽሞ ውጤቱን ለሌላ አካል ያቀርባል፤ ያ የተቀበለው አካል በተራው ሌላ አካል ይጠራና አሳቡን በመተግበር አዲስ አካል ያስመርጣል፤ ይህ የተመረጠው አካል ደግሞ ሠርግና ምላሽ ይደግስና የራሱን ሹመት ያጸድቃል። 'የምርጫው ሂደት ሥርዓትና ወግስ ዘላቂውን ረዥም ጉዞ የተለመ ነው? ወይስ የቤተ ሙከራ ነገር ነው?' ብሎ ማን ይጠይቃል?

እንግዲህ ይህ ሁሉ ትግል ወንጌላውያኑን እንደ ሃይማኖት ለማስመዝገብ ነው። በእውነቱ መንግሥት የሃይማኖት ነጻነትን ካልፈቀደ አልፈቀደም ነው። ከፈቀደ ደግሞ ፈቀደ ነው። ከፈቀደ፥ መጀመሪያ በማኅበር ተደራጁና በርከት ብላችሁ ብትመጡ፥ አንድነትና አንድ ድምጽ ቢኖራችሁ አዋጅ እናውጅላችሁና መብት እንሰጣችኋለን የሚል የዜግነት መብት ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ሳይሆን፥ ይህን የዜግነት መብት

የሚፈቅድበትን መንገድ ለሁሉም ሃይማኖቶች ሁሉንም በሚመጥን መልኩ ቀርጾ በማውጣት ነው።

ለእያንዳንዱ ሃይማኖት የተለያየ አዋጅ ማውጣት ሲጀመር የማበላለጥ ጉዳይ ሲኖርበት፥ ኋላም ይህ አዋጅ የመንግሥት ሃይማኖት እንዲኖር መሣሪያ ሊሆን፥ ወይም ሃይማኖታዊ መንግሥት እንዲኖር በር ሊከፍት ይችላል። የማበላለጥና የማዳላቱ ጉዳይ ባለፈው የጠቀስኩት ነው። የኢኦተቤ/ክ መንግሥታዊ ሃይማኖት ሆና ከሺህ ዓመት ተኩል በላይ የኖረች ናት። የ1952ቱ አዋጅ ለዘመናዊው አሠራር ሕጋዊ አካልነት ከማቀዳጀቱ ባለፈ የቀድሞው ሢሦ ለቀዳሽ ሥርዓት ለይስሙላ የተሻረ ይመስል ነበር።

አንድ ሃይማኖት አዋጅ እንዲታወጅለት የግድ የአገሪቱን ሕዝብ እርቦ መድረስና እወቁኝ ማለት አለበት ማለት ነው? ሃይማኖቱ እስላም ይሁን ክርስትና፥ ይሁዲ ይሁን አረሚ፥ ወይም ሌላ፥ መንግሥት ሁሉን በእኩል ዓይን የሚያይበት፥ የሚያስተናግድበት፥ ፈቃድ ይሁን የአካልነት መታወቂያ የሚሰጥበት ከአድልዎና መድልዎ የጸዳ አሠራር ሊኖረው ግድ ይላል።

ይልቅስ ከዣንጥላው ይበልጡን ሕዝቡን አንድ እያደረገ ያለው ሌላው ነው።

የዣንጥላው ነገር . . .።

March 19, 2020




ዣንጥላው ያስጠልላል?

የቆንስላው ነገር . . ።

በእውነቱ ችግሮቹ ችግሮች ከሆኑ መንግሥት፥ ወይም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር፥ ‘እንዲህ ነው እንዴ? እውነት የመሰብሰቢያና የመቀበሪያ ቦታ የላችሁም? እንደ ሃይማኖት አትቆጠሩም? ብሎ ባያውቅም እንኳ፥ (ነገሩ የአደባባይ ምስጢር ነው መሆኑ ሳይጠፋን) እንዲህ ነው ወይ? ብሎ እንዲጠና እንዴት ሊያደርግ አልሞከረም? ችግሩን ካወቀ፥ (መቼም ሳያውቅ አልቀረም የመገንዘብና የመቀበል ችግር እንጂ) ችግሩ መሠረታዊ መሆኑን ከተገነዘበና ከተቀበለ ደግሞ፥ አዋጁን ለማርቀቅ ምንም አያግደውም። የኛ በኅብረት መሆንና አለመሆን የሃይማኖት ነፃነት አዋጅን ለማወጅ ቅድመ ሁኔታ አይደለም። ወንጌላዊ እምነት እኮ ታሪካዊ ሃይማኖት ነው። ይህ እኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃይማኖት ነው። ምንም እንኳ በአንዳንዶች፥ ‘መጤ’ እየተባለ ቢጠራም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ነው። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ ሃይማኖት የለም፤ ሁሉም የመጣ ነው። የሁላችንም ሃይማኖት መጤ ነው። ማን ነው ያልመጣው?

# መንፈሳዊ ኅብረት ወይም ክርስቲያናዊ አንድነት ምንድርን ነው?




ባለፈው ሳምንት ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ወይም ፌዴሬሽን እይታዬን እንዳካፈልኩት አሁንም ማካፈሌን እቀጥላለሁ። ሰሞኑን የተለያዩ ሚድያዎች በቆንስላው ወይም ፌዴሬሽኑ ጉዳይ የተረዱትን እያካፈሉን ናቸው። አንዳንዶቹ ሚድያዎች ሕዝባዊ ናቸው፤ ሌሎቹ ማኅበራዊ ናቸው፤ ሌሎቹ አድርጉ የተባሉትን የሚያደርጉ የካድሬ ሚድያ ናቸው።

ባለፈው የቆንስላውን እይታዬን ባካፈልኩበት ቪድዮ፥ 'ስለ አንድነቱ የምትናገሩት ነገር ከሌላችሁ አትቃወሙ፤ ዝም በሉ፤ ዝም ማለትም መደገፍ ነው።' ያሉትን አካፍዬ ነበር። በጣም የሚያሸማቅቅ ነው የሚድያ ሰዎች እንደዚያ ሲሉ መስማት። የራሳቸውን አሳብ ከመናገር አልፈው፥ (መናገራቸው ትክክል ነው) ያንን አልፈው ሌሎች ያንን የሚቃወም ነገር እንዳይናገሩ የሚከላከሉ ከሆኑ፥ እነዚህ **ካድሬዎች እንጂ ጋዜጠኞች አይደሉም!** ካድሬ ይሞላበታል፤ ይጠቀጠቅበታል፤ ወይም ይከፈለዋል፤ ከዚያ ካዳሪ ነውና ይካድራል፤ የካድሬ ሥራ ይሠራል። የተጠቀጠቀበትን **ያስወጣል።** ካድሬ። የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴ የእንግሊዝኛ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ሆኖ ጋዜጠኝነትንም ይጨምራልና ጋዜጠኛን ከሩቅ በሽታ መለየት እንድንችል አድርገውናል። ጋዜጠኛን ብቻ ሳይሆን ጋዜጠኛ የሚመስል ካድሬንም እንደዚያው እንድናውቅ አድርገውናል።

ዛሬ በኒቆዲሞስ ሾው ከቀረበ ሌላ ዝግጅት ጥቂት አሳብ በመውሰድ እንዳለፈው ጊዜ የራሴን እይታ አካፍላለሁ። ዝግጅቱ ዶ/ር ማሙሻና ዶ/ር ሰብለ ወንጌልን ያቀረበው ሲሆን ቃለ ምልልሱ እዚህ ይገኛል፤ https://www.youtube.com/watch?v=LD1CXBNFVmo ከቃለ ምልልሱ ጥቂት እወስዳለሁ። ከዚያ ጋር GMM TV ካቀረበው ውስጥም ጥቂት እወስዳለሁ። የነዚህ

ምንጭ ደግሞ ይህ ነው፤ https://www.youtube.com/watch?v=Xsdifcx2LsM። https://www.youtube.com/watch?v=IdRl9hExaKo።

ዛሬ የማካፍለው ወይም የማተኩርባቸው ሁለት ነጥቦች አንዱ በክርስቲያናዊ ኅብረት ምንነት ላይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ መንግሥት በእውነቱ ለወንጌላውያን አማኞች ወይም በአገሪቱ ላሉ ሃይማኖቶች ሁሉ ሙሉ ሃይማኖታዊ ነጻነቶችና መብቶች ለማጎናጸፍና ለማወጅ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደማያስፈልገው የሚል ነው።

. . . . .

ምክንያት = ከምዝገባ ጋር የተያያዙ የሙብት እጦት የማምለኪያና የቀብር ቦታ እጦት። ለዚህ ነው? የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳብ፥ 'ጥያቄዎቹ ጥሩ ናቸው፤ የተበታተነ ድምጽ አይሰማም። . . . ሰብሰብ ማለት ያስፈልጋል። የሚሰበስብ አካል ያስፈልጋል። አንድ አሥር አሥራ አምስት ሰዎች ስጡኝና እነዚህ ሰዎች ተሰባስበው ምክረ አሳብ ያቅርቡልኝ።' የሚል ነው።

ጨቋኝ ባልሆነና ሃይማኖታዊ ባልሆነ ዘመናዊ መንግሥት ዘንድ የሃይማኖትና የሕሊና ነፃነት፥ ተሰብስቦ ማምለክም፥ የቀብር ሙብት ማግኘትም እኮ የዜግነት ሙብት ነው። እኛ ወንጌላውያን አማኞች በስደት ውስጥ ስለኖርን፥ መንግሥታዊ ፖሊሲን በተመለከተ አሁንም ጭምር በስደት ነን ማለት ይቻላል፤ ቆንስላውን፥ ዣንጥላውን ሙብት አስከባሪ አድርገን እያየን ነን፤ አድርገው እያሳዩን ስለሆኑ። 'የተበታተነ ድምጽ አይሰማም። . . . ሰብሰብ ማለት ያስፈልጋል።' የምር? ሃይማኖትን ለሚያህል ግዙፍ ነገር? የአምልኮ ቦታን ለሚያህል ትልቅ ጉዳይ? ቀብርን ለሚያህል ክቡር ሥርዓት? 'የተበታተነ ድምጽ አይሰማም።' የእውነት? ከፍቼ አዲስ አበባ አምጥቶ ሬሳ መቅበር አዲስ ነገር ነው? አይደለም። ግን አይሰማም? የምር? ይህንን ለማሰማት ነው ተሰባስበን መጮህ ያለብን? የእውነት? እኛ አገር እኮ ሬሳ መቅበሪያ ማጣት ብቻ ሳይሆን የተቀበረም እየወጣ ተቃጥሏል። የከበረ ሕዝብ ያለንን ያህል የረከሰና ነውረኛም ሕዝብ አለን። ይህን ሁሉ መንግሥት ሳያውቅ ቀረ? የሃይማኖት ሕጉ ቀድሞም አሁንም አድሏዊ ነው። አድሏዊ ያደረገው መንግሥት ነው። ፍትሐዊ የሚያደርገውም መንግሥት ነው። የኛ መሰብሰብና አለመሰብሰብ አይደለም።

መሰባሰብን በተመለከተ ማወቅ ያለብን፥ በየትኛውም ብሔራውያን የወንጌላውያን ኅብረቶች ውስጥ የቃለ እምነት (Word of Faith) አስተማሪዎች እና የአዲሱ ሐዋርያዊ ዳግም ሥሪት ወይም አሐዳስ (New Apostolic Reformation – NAR ይባላል) የነዚህ 'ሐዋርያት እና ነቢያት' የተባለ መለዮ ያደረጉ ሰዎች እንደ ወንጌላውያን አማኞች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ነው። ሁለት ምሳሌዎች ብቻ ልውሰድ።

አንደኛ፥ እነ ኬነት ኮፐላንድ፥ ጆወል ኦስቲን፥ ቤኒ ሂን፥ እና ሌሎችም የአሐዳስ እና ቃለ እምነት ሰዎች በአሜሪካ የአሜሪካ ማኅበረ ወንጌላውያን (NAE) ተቀባይነት

የላቸውም። ይህ የሆነበት ምክንያት፥ ከሌሎች ኮተቶቻቸው ጋር፥ ትምህርታቸው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መስመር የወጣ በመሆኑ ነው። ይህ **በሽተኛ** ክርስትና ነው ወደ አገራችንና ወደ ሌሎች አገሮች ኤክስፖርት የተደረገው። ያውም **በገፍ ተመርቶ፥ በርካሽ ተሸጦ፥ አገራችንን የበከለው!** የአገራቸው አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ያወገዟቸውን ሰዎች ቡችሎች ነው እኛ፥ 'በትከሻችሁ እንኮኮ በሏቸው!' የምንባል ያለነው። ይህ ቀልድ ነው? ወይስ የምር? ይህንን የሚለን መጽሐፍ ቅዱስ ነው? ወይስ **የኮሚኒስት ማኒፌስቶ?** የነዚህ ሰዎች በሽተኛ ትምህርት ምን መሆኑን ለመረዳት American Gospel የተባለ ዶክሜንተሪ ፊልም መመልከት ብቻ በቂ ነው። American Gospel። ማንበብ አይጠይቅም፤ ፊልም ነው፤ ትምህርታዊ ፊልም፤ ተመልከቱት።

ሁለተኛ ምሳሌ፥ ከአህጉራችን ልውሰድ። በናይጄሪያ Christian Association of Nigeria (CAN) የሚባል የወንጌል አማኞች ማኅበር አለ። ሐሰተኛው ነቢይ ቲ. ቢ. ጆሹዋ እና ድርጅቱ የዚህ ማኅበር አባል ሊሆን ጨርሶ የማይታሰብ ነውና አይደሉም። ምክንያታቸው ምንድን ነው? ሐሰተኛ ነቢይ በመሆኑ። በናይጄሪያ ሌላ ጴንጤቆስጣዊ ማኅበርም አለ። PFN ይባላል፤ Pentecostal Fellowship of Nigeria። ቲ. ቢ. ጆሹዋ ያ ማኅበርም በግልጽ ያወገዘው ሰው ነው። በMay 2013 በበተንኩት የዕዝራ መጽሔት ቁጥር 21 በዚህ ጉዳይ ላይ ከጻፍኩት ላንብብ።

> ቲ. ቢ. የናይጄሪያ ጴንጤቆስጣውያን ማኅበር (PFN) በግልጽ ያወገዘው ሰው ነው። አንድ ሰው እንዳለው፥ 'እና ምን ይጠበስ? ነቢይ በገዛ አገሩ ባይከበር ምን ያስገርማል?' ማለት ይቻል ይሆናል። እንዲያስገርም የሚያደርገው ልዩነት ግን፥ እነዚያ፥ ያንን የናዝሬቱን ነቢይ ያልተቀበሉት ሰው ብቻ የመሰላቸውና የተሰናከሉበት አይሁድ ሲሆኑ እነዚህ ግን የዚያ የናዝሬቱ ነቢይ የክርስቶስ ተከታዮች መምሰላቸው ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት። ልዩነቱ ያ ነው።
>
> የወንጌላዊ ቦንኬ አገልግሎት የሆነው CFAN በናይጄሪያ ብዙ የጅማ ስብከቶችን አካሂዶአል። የCFAN ምክትል ፕሬዘደንት Peter Vandenberg ከዓመታት በፊት በናይጄሪያ ስለነበረው አገልግሎት ሲናገር፥ ከ2000 የሚበዙ የናይጄሪያ አብያተ ክርስቲያናት በተሳተፉበት በናይጄሪያ ባደረጓቸው ጉባኤዎች፥ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ቲ. ቢ. ን ማውገዛቸውን፥ የሚሠራቸው ሥራዎች ምንም በኢየሱስ ስም ቢሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑንና በናይጄሪያ በሰፊው ከተለመዱ የጥንቆላ አሠራሮች ጋር የተያያዙ እንደሆኑ መናገራቸውን ጠቅሶአል። ከዚህ የተነሣ CFAN በናይጄሪያ ከቲ. ቢ. ጋር እንደማይሠራ ገልጦ፥ "በናይጄሪያ ያሉት ወንድሞቻችን በዚያ ምድር የሚኖሩ ናቸውና ከኛ ይበልጥ ስለጉዳዩ እነርሱ ያውቃሉ።" ብሎአል።
>
> በሌጎስ የቤተ ክርስቲያን ቄስ የሆነው Chris Okotie "ቲ. ቢ. ጆሹዋ ድብቅና ምስጢራዊ አሠራሮቹ መወገዝ ያለባቸው በቀላሉ የሚታመን አጭበርባሪ (charlatan) ሰው ነው" ብሏል። Joseph Thompson የተባለ የናይጄሪያ የወንጌል አገልጋይ ደግሞ፥ "ቲ. ቢ. ጆሹዋ በናይጄሪያም ሆነ በጠቅላላው ዓለም ላለችው ለክርስቶስ አካል አደገኛ ሰው ነው።" ብሏል። እነዚህ ሰዎች ደጋግመው የሚጠቅሱት ቲ. ቢ. በኢየሱስ ስም ቢጸልይም በመጽሐፍ ቅዱስ ከቶ ያልተደረገ

ክርስትናን ከጥንቆላ ጋር የመበረዝ ድፍረት እንደሚታይበት ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን ሰው በቅርብ የሚያውቁ የአገሬው ሰዎች ናቸው።

እነዚህን የአገሩ ሰዎች አውቀዋቸው ሲነቅፏቸውና ሲያወግዟቸው እያየን የኛዎቹ ደግሞ የነዚህን እንጀራ ልጆች፥ በኅብረት ስም እቀፏቸው፤ 'አንድ ላይ ተቃቀፉና ኑ ድምጻችሁ እንዲሰማ' ይሉናል። የጉማሬ ቆዳ ከለበስክ ጃርት ማቀፍ ትችላለህ፤ ያለዚያ ግን ዋጋ ትከፍላለህ ወዳጄ። በኛው አገር ዣንጥላ በጉም ተኩላውም ዣንጥላው ከተመሠረተበት ቀን ሳይሆን ዣንጥላውን በመሥራቱ ሂደትም አብረው ናቸው። ተኩላና በግ የጋራ ቤት እየሠሩ ናቸው። አብረው በሚሠሩት ቤት ተኩላው ምን ሊሠራ እንደሚያስብ የወንጌል ኮንትሮባንድ ነጋዴው ምን ሊያተርፍ እንደሚያስብ መገመት ብቻ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የምናነብባቸው የአባቶች ጉባኤዎች የተቀመጡት እኮ፥ 'አንድ የሚያደርገን ምንድርን ነው?' እያሉ ሳይሆን፥ 'ይህ ኑፋቄ ነው' በማለት፥ ለዚያ መልስ በመስጠት ነው። በታሪክ ውስጥ ሐሰተኞችን ያወገዙ ጉባኤዎች፥ 'ሰውየውንና ትምህርቱን ነጣጥለን እንይ፥ ትምህርቱት እንተው፤ ሰውየውን እንቀፈው . . .' ማለት አላቃታቸውም። እኛም፥ 'ነቢዩንና (በመጽሐፍ ቅዱስ መለኪያ ነቢይ አይደለም እንጂ) ነቢዩንና ትንቢቱን ነጣጥለን እንይ፤ ትንቢት ይሳሳታል እንጂ ነቢይ አይሳሳትም፤ ሐዋርያውንና ትምህርቱን ነጣጥለን እንይ ጎበዝ! ትምህርቱ እንጂ እሱ አልተሳሳተም፤ . . .' እያልን ራሳችንን በመሸንገል መቀጠል እንችላለን። እንክርዳዱን አለመንቀል ሳይሆን አበርክተን መዝራትም ማን ያግደናል?

የቪዥነሪዎች (ወይም ራእያሞች ነው የምላቸው) ኅብረት እኮ የወንጌላውያን ኅብረት ውስጥ መግባት ስላልቻሉ የመሠረቱት አጸፋ ነው። የቀድሞዎቹን አብያተ ክርስቲያናት፥ 'አሮጊቷ' እያሉ የወጣት ድርጅት መሥርተው ራሳቸውን፥ 'ባለ ራእይና መሥራች' እያሉ የጀመሩ ናቸው።  ተንባዮች፥ ዘራፊዎች፥ መድኃኒት አስጣዮች፥ አስደብዳቢዎች ያሉበት ማኅበር ነው። ሰው መንፈስ ነው፤ ኢየሱስ ከጌቴሴማኒ ጀምሮ እስከ ትንሣኤው ድረስ 3 ቀንና 3 ሌሊት ሰይጣን ሆኖ ነበር፤ የሚሉ ናቸው። ክርስቲያን መታመም የለበትም፤ ፈውስ መብቱ ነው፤ ብልጽግና መለኮታዊ መብቱ ነው የሚሉ ናቸው። እነዚህ እኮ ኋላ ተፈትሸው፥ ተጣርተው የሚገቡ ሳይሆኑ መሥራቾች ናቸው። እንዴት ነው ሌላ ኢየሱስ የሚሰብክ ሰው ንስሐ ሳይገባ አንድ የሚያደርገን ይበዛል የሚባለው? ያ ሰይጣን የሆነው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አለመሆኑን ማወቅ እንዴት ተሳነን?

ባለፈው ዝግጅት የጠቀስኩት ይህ መጽሐፍ፥ ***የተሐድሶ ጥሪ*** መጽሐፍ ከ3 ዓመት በፊት ሲሠራ እንደዚህ ያሉ ዝንፈቶችን ለማሳወቅና ለማጥራት ነበረ። ያንን ተከትሎ ውጤቱ ምን ነበር? ከ2009 ወዲህ ምን ሆነ? እየባሰና እየከፋ ነው የሄደው። ይህ ሥራ የተሠራበት ፎረም በ6 አገልግሎቶችና በ22 ተሳታፊዎች ነው። በዚያ ውስጥ በሦስት ክፍሎች የተሰደሩ ጉዳዮች ተወስተዋል፤ ጥሪት **ሕይወት፥** ጥራት **አስተምህሮ፥** እና **የአመራር** ጥራት። በሦስቱም ውስጥ በቂና ዝርዝር ነጥቦች ተተንትነዋል። . . .

ብናስተውለው፥ ቢገባን፥ ተበታትነን የምንጮኸው የኛ ጩኸት ከቁጥር ሳይገባ፥ ይህ ብቻውን ግዙፍ የመመለስ ምክንያት ሊሆናቸው ይችል ነበር።

. . . . .

እኛ ስደትን እንደ መደበኛ የክርስትና አካል አድርገን የምናየው የመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሞዴሎቻችን ስለሆኑ ነው። የመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናትና መሪዎች ስደተኞች ነበሩ። የኢትዮጵያዋ ወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያንም ገና ከጥንስሱ ከነኦነሲሞስ መጫፈ ቁልቁሉ አገር እንዳይገባ መታገድ፥ ከነ አባ ሮሜ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይገባ መከልከል፥ ከነ አለቃ ዘነብ፥ ከነከንቲባ ገብሩ ጀምሮ እስከነ አባባ ወንዳሮ፥ እስከኛዎቹ ዘመን እስከነ ተስፋዬ ጋቢሶ ከነገሥታቱ እስከ ደርግ ዘመን ስደት እራታቸው ነበሩ። በእውነቱ፥ እኛ መብት **<u>ቢኖረንም ባይኖረንም እንኖራለን።</u>** እንደ ተወደደው መዝሙራችን ጠፉ ስንባል የምንበዛ ሰዎች ነን።

ሰማያዊ ዜግነታችን በልጥብን የምድሩን አለመጓጓታችን ጌታን የመምሰል ትሕትና እንጂ ሞኝነት አይደለም። ቤተ ክርስቲያናችንም ሬሳችንም ሲቃጠል ዝም ማለታችን ዘላለማዊው መብለጡን ማወቃችን እንጂ መብታችንን አለማወቃችን አይደለም። እኛ ለነገሩ ዝም አላልንም እንጂ፥ ዝም ብንልም እንኳ መንግሥትም ዝም ማለት አልነበረበትም። መንግሥት ዝም እንዳይል ደግሞ አንድ ዣንጥላ ስር ሆነን ሰላማዊ ወይም የተቃውሞ ሰልፍ መውጣት አልነበረብንም፤ የለብንምም።

አስቀድሞም አድልዎ ያለበትን ሕገ መንግሥት መንግሥት በራሱ ሊያስተካክል የኛን ጉንተላና የኛን፥ 'የተበታተነ የማይሰማ ድምጽ' እንዲሰማ የኛን መሰባሰብ ከፈለገ ሕገ መንግሥቱ አድሏዊ መሆኑን ተቀብሏል ማለት ነው። **<u>ይህንን ትልቅ ነጥብ ያዙልኝ።</u>** አድሏዊ መሆኑን ከተቀበለ ማሻሻያውን ማድረግ ነው ያለበት? ወይስ፥ 'በአንድ ዣንጥላ ስር ተሰባሰቡና በአንድ ድምጽ ኑ' ማለት ነው ያለበት? መንግሥት ሊያደርግ የሚችለውን የሃይማኖት አካልነት መብት፥ የማምለክ ፈቃድ ማግኘት፥ የአምልኮ ቦታና የቀብር ቦታ የማግኘት መብት ለመስጠት የኛ መሰባሰብ **<u>አያስፈልገውም።</u>** መንግሥት እስከዛሬ ያላደረጋቸውን ወይም ምናልባት ሊያደርግ ያልቻላቸውን የራሱን ሸንቁሮች እንዳናይ ዣንጥላውን መብት አስከባሪ አድርገን እንድናይ ማድረጉ ስሕተት ነው። ወይስ ባለፈው በፌስቡክ ገጼ እንደጠየቅኩት መንግሥት መንፈሳዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሥራዎቹን outsource ያደርጋል ማለት ነው? Outsource ማድረግ ጉልበት በረከሰበት አገር በቀላል ዋጋ ሌላውን ማሠራት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንም ለሌሎች የመጠንቀቅ፥ የመድረስ፥ ግብረ ሰናይ የመፈጸም፥ የማገዝ ሳምራዊ ግዴታ፥ ከጌታ በአደራ የተሰጣትን የታላቁን ተልእኮ ኃላፊነት ለመወጣት የግድ በአንድ ዣንጥላ ስር መሆን የለባትም። ሳትሆንም እያደረገች ኖራለች።

. . . . .

ይህ ጣልቃ መግባት ሳይሆን አሳብ መስጠት ነው ተብሏል። እዚያው ቤተ መንግሥት ውስጥ ኮሚቴ ተመሥርቶ? እንዲያው ለወጉ ምን ነበር ቤተ መንግሥት ባይሆን? ሲሆን ሲሆን እናንተ ቃሉ እንደሚላችሁ አንድ ሁኑ እኛ ሕጉን እንሠራለን። ቢባል አይሻልም ነበር? በእውነቱ ችግሮቹ ችግሮች ከሆኑ መንግሥት፥ ወይም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር፥ 'እንዲህ ነው እንዴ? እውነት የመሰብሰቢያና የመቀበሪያ ቦታ የላችሁም? እንደ ሃይማኖት አትቆጠሩም? ብሎ ባያውቅም እንኳ፥ (ነገሩ የአደባባይ ምስጢር ነው መሆኑ ሳይጠፋን) እንዲህ ነው እንዴ? ብሎ እንዲጠና እንዴት ሊያደርግ አልሞከረም? ችግሩን ካወቀ፥ (መቼም ሳያውቅ አልቀረም የመገንዘብና የመቀበል ችግር እንጂ) ችግሩ መሠረታዊ መሆኑን ከተገነዘበና ከተቀበለ ደግሞ፥ አዋጁን ለማርቀቅ ምንም አያግደውም። የኛ በኅብረት መሆንና አለመሆን የሃይማኖት ነፃነት አዋጅን ለማወጅ ቅድመ ሁኔታ <u>**አይደለም።**</u> ወንጌላዊ እምነት እኮ ታሪካዊ ሃይማኖት ነው። ወንጌላዊ እምነት እኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃይማኖት ነው። ምንም እንኳ በአንዳንዶች፥ 'መጤ' እየተባለ ቢጠራም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ነው። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ ሃይማኖት የለም፤ ሁሉም የመጣ ነው። የሁላችንም ሃይማኖት መጤ ነው። ማን ነው ያልመጣው?

የሙብት ጥያቄዎች ድምጾች ያልተሰሙት ማኅበረሰቡ በጣም የተበታተነ ስለሆነ ነው? ጥያቄዎቹ ጥሩ ከሆኑ፥ የሙብት ጉዳዮች ከሆኑ፥ የሃይማኖት ነጻነት ጉዳይ ከሆነ፥ መበታተኑ እንዴት ነው ችግርነቱ? መሰባሰቡስ እንዴት ነው መፍትሔነቱ? መንግሥት ይህን መሰባሰብ አድርጉና እናውጃለን፥ ሙብት እናስጠብቃለን ሲል የየትኛውን አገር ተሞክሮ ወስዶ ነው? በየትኛው አገር ነው ሃይማኖት ሙብት ለመሆን ከዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር የተደራደረው? የኢትዮጵያ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ነው እስከምናውቀው፤ ኢፌዲሪ ውስጥ ያለው ዲ ዲሞክራሲያዊ ማለት ነው። የትኛውም ዲሞክራሲያዊ አገር ለሃይማኖት እና ለኅሊና ነጻነት ሙብት ተሰባሰባችሁ አመልክቱ ብሎ አያውቅም። ካወቀ አስተምሩን።

እንግዲህ ይህ ሁሉ የትብብር ምክረ አሳብ አመንጪ ኮሚቴው አሳብ አመንጭቶ፥ ዘጠኝ ወር አርግዞ የወለደው ትግል በአንድነት ድምጽ አሰምቶ ወንጌላውያኑን እንደ ሃይማኖት ለማስመዝገብ ነው? እንዝርቱ ያ ይመስላል። መንግሥት የሃይማኖት ነጻነትን ካልፈቀደ አልፈቀደም ነው፤ ከፈቀደ ደግሞ ፈቀደ ነው። ከፈቀደ፥ መጀመሪያ በማኅበር ተደራጁና በርከት ብላችሁ ብትመጡ፥ አንድነትና አንድ ድምጽ ቢኖራችሁ አዋጅ እናውጅላችሁና ሙብት እንሰጣችኋለን የሚል የዜግነት ሙብት <u>**ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አይደለም።**</u> ለእያንዳንዱ ሃይማኖት የተለያየ አዋጅ ማውጣት ሲጀመር፥ የማበላለጥ ጉዳይ ሲኖርበት፥ ሲቀጥል ደግሞ፥ ይህ አዋጅ የመንግሥት ሃይማኖት እንዲኖር፥ ወይም ሃይማኖታዊ መንግሥት እንዲኖር በር ሊከፍትም፥ መሣሪያ ሊሆንም ይችላል። የማበላለጥና የማዳላቱን ጉዳይ ባለፈው በትንሹ ተናግሬበታለሁ። የኢኦተቤ/ክ መንግሥታዊ ሃይማኖት ሆና ከሺህ ተኩል ዓመት በላይ የኖረች ናት። የ1952ቱ አዋጅ ለዘመናዊው አሠራር ሕጋዊ አካልነት ከማቀዳጀቱ ባለፈ የቀድሞው ሢሦ ለቀዳሽ ሥርዓት ለይስሙላ የተሻረበት አካሄድም ነው።

አንድ ሃይማኖት የነጻነት አዋጅ እንዲታወጅለት የግድ ተሰባስቦ 'እወቁኝ' ማለት የለበትም። ሃይማኖቱ እስላም ይሁን ክርስትና፥ ይሁዲ ይሁን አረሚ፥ ወይም ሌላ፥ መንግሥት ሁሉን በእኩል ዓይን የሚያይበት፥ የሚያስተናግድበት፥ ፈቃድ ይሁን የአካልነት መታወቂያ የሚሰጥበት ከአድልዎና መድልዎ የጸዳ አሠራር ሊኖረው ግድ ይላል። መንግሥት እነዚህን ነገሮች በራሱ አሠራር ማድረግ አለበት እንጂ እኛ የኛ ሕግ አርቃቂና አጽዳቂ አይደለንም።

. . . . .

እርግጥም መንግሥት ይህን አድርጉ ሲል አሺ፥ ያንን ሁኑ ሲል አሺ ስንል ከኖርን የአሁኑን አሺ ከሌላው ምን ለየው?

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለመበታተኗ የከፈለቻቸው ዋጋ? በእውነቱ ምንድነው መበታተን? መቼ ነው የተበታተንነው? ከስንትነት ነው የተበታተንነው? ስንት ኖረን ስንት ሆንን? ባለፉት አምስት ዓመታት ስንት የሐሰተኛ ነቢያትና ሐዋርያት ድርጅቶች ፈቃድ አገኙ? መበታተን ያሰኘው ያ የመሥራችና ባለ ራእዮች ቁጥር መብዛቱ ነው? አይደለም፤ መበታተንና መከፋፈል ማለት አንድ ኖረን ብትንትናችን ሲወጣ ነው። እንጂ፥ ሽቃጮችና አታላዮች ፈቃድ አውጥተው ተመዝግበው ቁጥሩን ከፍ ስላደረጉት አይደለም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት እየተመዘገቡ ቁጥሩን ያናሩት ድርጅቶች አመዘጋገባቸውም፥ አደረጃጀታቸውም ልክ እንደ ንግድ ድርጅት ነው። ከሽያጭ እስከ ባለቤትነት ድረስ አሠራራቸውም እንደ ንግድ መደብር ነው።

ከመበታተን አንድ መሆንስ ምኑ ነው? አሁን ይህ ዣንጥላ ከተመሠረተ አንድ ሆንን ማለት ነው? ወይም ኅብረት ተፈጠረ ማለት ነው? እንበልና ይህ አይስማማንም የሚሉ ይወጣሉ፤ ከወጡ ሃይማኖታዊ መብት አይኖራቸውም? ሃይማኖት ይገደባል? ፈቃዳቸውንስ ይነጠቃሉ? መሰብሰብስ ይከለከላሉ? ከአየርስ ይወርዳሉ? እነዚህ ሐሰተኞች ንስሐ ከገቡ እሰይ! ግን ባለፈው እንዳልኩት ከታሪክም ከዘመናችንም ንስሐ የገቡ አሳቾችን እስታቲስቲክስ መፈተሽ እንችላለን። ላለመደንገጥ ወስነን መፈተሽ እንችላለን።

ለማውገዝስ ሕብረት ያሻል? ለመሆኑ ኅብረት ሲባል መንፈሳዊ ኅብረትነቱ እንዴት ነው የታየው? ያልገባኝ ትልቅ ጉዳይ ይህ ነው። ይህ እዚህ የምንነጋገርበት ጉዳይ እኮ መንፈሳዊ ኅብረት ነው። ባለፈው ዝግጅት እንደ አዝማች የደጋገምኩትን ቃል ልበለው፤ ኅብረት መልካም ነው፤ መልካምም አይደለም። እኔ በክርስቲያናዊ ኅብረቶች ውስጥ በመገልገልም በማገልገልም አልፌ ስለማውቅ ኅብረት፥ አንድነት ሲባል የማይገባኝ ሰው አይደለሁም። አዲስ ክርስቲያን ከነበርኩበት የዩኒቨሲቲ ዓመታቴ ጀምሮ አሁንም በአማርኛ የምናመልክበት በኅብረታዊ ቤተ ክርስቲያን ነው። ብዙዎቻችንም ይህ ይገባናል። መንፈሳዊ ኅብረት፥ መንፈሳዊ አንድነት ሲባል የሚጠፋን አይደለንም።

መንፈሳዊ ኅብረት ከኅብረቶች ሁሉ በላይ የሆነ ኅብረት ነው። የገንዘብ ማጠራቀሚያ ዕቁብ አይደለም። የክፉ ቀን መረዳጃ ዕድር አይደለም። የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። የኅብረት ሥራ ማኅበር አይደለም። የሙያ ትብብርም አይደለም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የማንነታችንን አንድ ነገር ይጠይቃሉ። አንዳንዱ ቦታ በአካል ሳንገኝ፥ በስሜት ሳንገኝ፥ በአእምሮ ሳንገኝ ገንዘባችንን ብቻ ልከን አባልነታችንንም መጠበቅ እንችላለን። መንፈሳዊ ኅብረት ግን እንደዚህ አይደለም። 'መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ አንድነት ግን ምንድርን ነው?' ቢባል መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ አንድነትና ኅብረት ሁለመናችንን የሚይዝ ኅብረት ነው። የመንፈስ አንድነት የአካል አንድነት አይደለም፤ ብዙ የመንፈስ ያልሆኑ የአካል አንድነቶች አሉ።

ጳውሎስ በኤፌ. 4፥3 በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። ይላል። መንፈስ ውስጣዊ ማንነታችን ነውና ሁለንተናችንን የያዘ ማንነት ነው። በሽንገላ ኅብረት አናደርግም። እግዚአብሔርን ስንወድ ወይም ስናመልክ የተነገረን ይህ ነው፤ *አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን* ***<u>በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ</u>*** *ውደድ።* ዘዳ. 6፥5። ይህ ሁለንተናችንን ይጠይቃል። ሳያውቅ ሳይሆን፥ አውቆ፥ አስልቶ፥ አውጥቶ አውርዶ፥ አጥንቶ፥ ሸምድዶ፥ ሰዎችን ሁሉና፥ በተለይም ቅዱሳንን ከሚያጠቃ፥ ከሚጎዳ ሰው ጋር አብሬ ማምለክ አልችልም። ይህ አምልኮ እስብሰባ ላይ ከመቀመጥ ያለፈ ነው። ትምህርት ቀምሮ፥ ጥቅሶች አሰባጥሮ ኢየሱስን ሌላ ከሚያደርግ አሳች ጋር አሳችነቱን ለመንገር ካልሆነ በቀር ለሌላ ነገር አብሬው እንድቀመጥ ቃሉ አላስተማረኝም። እንደ ሰውነቱ ያንን ሰው መውደድና ከነስሕተቱ አብረን እንተባበር ማለት መደመር ማለት ከሆነ መደመር ለቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ሳይሆን፥ የማይሠራ ብቻም ሳይሆን፥ እንዲያውም ለቤተ ክርስቲያን አፍራሽ ፍልስፍና ነው።

እንደ ሰውነቱ ያንን ሰው መውደድ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው፤ የሚጠሉንንም እንድንወድድ ተነግሮናልና ይህንን፥ 'መውደድ' የሚለውን ቃል ግን ሐሰተኞችን ለመተባበር መሸንገያ መንጠቆ ቃል አድርገን ልንጠቅስ የተገባ አይደለም። ከዚያ ሰው ጋር አብሬ ለማምለክ የማልችለው አምልኮ ንጹህ ነገር ስለሆነ ነው። አምልኮ በልዑል እግዚአብሔር ፊት መቆየት ነው። ልብን፥ ነፍስን፥ ኃይልን፥ ስሜትን፥ አእምሮን የሚይዝ ግንኙነት ነው። አስልቶ የሚያስት አሳች ሰው ስሕተቱን ሳይቀበል ቆሞ ሲሸነግለኝ፥ ወንድሜን ያስደበደበ ሰው ይቅርታ ሳይጠይቀው አብሮኝ ሲንበረከክ፥ እኅቴን መድኃኒት አስጥሎ እንድትሰቃይና እንድትሞት ያደረገ ሰው ሳይጸጸት ገና ሌሎችንም እያስጣለ እጁን አንሥቶ ቢዘምር እዚያ ቦታ መቆም አልችልም። እቆም ይሆናል ማምለክ አልችልም። አምልኮ ሁለንተናን ስለሚጠይቅ ከውስጤ አንዱ ክፍል ይቆጣል፤ ወይ ስሜቴ፥ ወይ መንፈሴ፥ ወይ አእምሮዬ ይቆጣል፥ ይረበሻል፥ ተግባሩን ያቆማል። መንፈሳዊ ኅብረት ሁለንተናን ይጠይቃል። በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ከመቀመጥ ያለፈ ነው።

ይህ አሁን ኅብረት፥ ትብብር፥ ካውንስል፥ ፌዴሬሽን የምንለው ነገር የበግና የፍየል ትብብር ሳይሆን የበግና የተኩላ አንድነት ነው። እንኳን ተኩላና በግ፥ በግና ፍየልም

ለየቅል ናቸው። *የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።* ይላል ማቴ. 25፥31-33። ከዚያ ለሁለቱም የሚላቸው ተጽፏል። አይደለም በግና ተኩላ፥ በግና ፍየልም ለየቅል ናቸው።

ኅብረት ሲባል እንደ ፓርቲ፥ እንደ መረዳጃ አንድነት፥ እንደ ሙያ ማኅበር ከሆነ ችግር የለበትም። ግን መንፈሳዊ ኅብረት ወይም ክርስቲያናዊ አንድነት ሲባል ከዚህ ያለፈ መሆኑ ካልታወቀ የኅብረትን ትርጉምና ጥራት የሚጠይቁ ሰዎችን፥ ዝም በሉ፥ በማኅበራዊ ሚድያ የማታውቁትን ነገር አትለፍልፉ፥ ከምንጩ ቅዱ፥ ጸረ ኅብረቶች፥ ጸረ አንድነቶች ምናምን ማለት ወግ አይደለም። ያ ኅብረት የመመሥረት ጉዳይ ነው። ይህ እኛ የምንሞግተው ጉዳይ የቃሉ እውነትና መሬት ላይ ያለው እውነት ነው።

በነዚህ ጥቂት ቀናት በርካታ ቃለ ምልልሶች ወጡ፤ በርካታ አስተያየቶች በምክረ አሳብ ኮሚቴው ሰዎች ተደምጠዋል። በቃሉ የተወገዙ ትምህርቶችና በቃሉ የተወገዙ ድርጊቶች ግን **አንዴም እንኳ** በስም ተጠርተው አልተወገዙም። የሐሰት ነቢያት፥ የሐሰት ሐዋርያት አይባልም! መንፈሱን ያበላሸዋላ! የመደመር እሳቤውን ያቀጥነዋላ! ደግሞም መሥራቾቹም ናቸዋ! እነዚህ የተወገዙ ነገሮች አንዴም ሳይነኩ ለኅብረት ሲባል ግን፥ ይህንን አካሄድ ከጅምሩ ጀምሮ የሚገዳደሩትን፥ የሚቃወሙትን ሁሉ፥ 'በማኅበራዊ ሚድያ ምንም ሳያውቁ የሚተቹ' ማለት ወግ ነው?

ከሚድያዎቹ መካከል ደጋፊዎችን እንጂ የሚተቹትንና የሚቃወሙትን ለማቅረብ የሞከረ አንድም የለም፤ አላየሁም። በዚህ ጉዳይ ከመጀመሪያም ጀምሮ (ከሰኔ 2011) ሲቀነቀንለት የኖረው አንድነቱ ነው እንጂ ሌላኛው ገጽታው ከቶም አይደለም። በተለይ በነዚህ ሁለት ሳምንታት (ምክረ አሳብ በቀረበበትና ምረቃው ሊደረግ በታቀደበት መካከል) በኅብረት፥ በፌዴሬሽን፥ በትብብር፥ በአንድነት ላይ፥ አንድ ስለመሆን ብቻ እንጂ ልዩነት ያለው አሳብ ለምን ይቀርባል? ይህ ነውር ብቻ ሳይሆን ወንጀልም እንዲመስል እየተደረገ ነው። ሳይሆንስ ይቀራል? ለምሳሌ፥ ከ15ቱ መካከል የወጣ ወይም የወጡ ሰዎች ነበሩ። ለምን ወጡ? እነዚያ ቀርበው ቢጠየቁ ኖሮስ? ለምን እንደወጡ የሚሉት ነገር የላቸውም? ወይስ ቁጥራቸው አንድ ወይ ሁለት ስለሆነ፥ 'ምን አላት ይህቺ?' ተብሎ ነው? በፐርሰንት ከ15 ውስጥ 1 ወይም 2 ወደ 10% ነው። 'ምንድነው አሁን እየሆነ ያለው?' ብለን ብንጠይቅ፥ አንድና አንድ ነገር ነው። አንድና አንድ አሳብ ብቻ። ልዩ አሳብ ይውደም፤ አንድነት ይለምልም። 'ካልደገፋችሁ ዝም በሉ' እንደተባለው ነው።

ሕዝባዊ ተቀባይነት ብቻ እንጂ ሕዝባዊ ምክክር አልታሰበም። አዎ፥ ጉዳዩ ለቤተ እምነት መሪዎች ቀርቦ ነበር ተብሏል፤ በተናጠል? ወይስ በጋራ? ሕዝባዊ ኅብረት ሕዝባዊ ምክክርና ክርክር ሊደረግበት ያልተገባው ጉዳዩ በአገር መሪ ስለተጀመረ ነው? በአጭር ቋንቋ ሰሞኑን የሚደለቀው 'አንድ ነን አንድ ነን አንድ ነን አንድ!' የሚለው

አታሞ አንድ አቅጣጫ ብቻ ለማሳየት ነው። ጉዳዩ እንደ ግዝፈቱ ልክ ለሕዝባዊ ምክክር እና ክርክር ክፍት አልነበረም። 'ባትደግፉ ዝም በሉ' ሲባል፥ ሰፊውና መደዴው ክርስቲያን እንዲቀበል እንጂ እንዲጠረጥርና እንዲጠይቅ አለመፈለጉ ግልጽ ነው። ይህ አካሄድ ትክክል አይደለም የሚሉት ሰዎች አሳብ እንዲሰማ ያልተፈለገው የዚህን ጉዳይ ሌላውን አቅጣጫ የሚያሳዩ ሰዎች ጠፍተው ነው? አይደለም። አሉ በርካታ ሰዎች። 'ሳይሰሙ እየጻፉ . . . በሶሻል ሚድያ የሕዝብ አእምሮ የሚበክሉ . . . ከምንጩ ያልቀዱ፥ ወዘተ' የሚባሉ ሰዎች አሉ። ሰው ጠፍቶ አይደለም። አንዱ ብቻ እንጂ ሁለቱም ወገን እንዲቀርብ አልተፈለገም። እንኳን ይህንን የሚያህል ትልቅ ጉዳይ ቀርቶ፥ እንደ ዘፈን ባሉ ጉዳዮችም እኮ ክርክሮችና ውይይቶች ተደርገው ነበር። ይህ ከዘፈን አንሶ ነው? ምናልባት አንሶ ነው ማለት ነው።

'ባትደግፉ ዝም በሉ' እንደተባለው ነው አሁንም። ዝም እንላለንም፤ ዝም አንልምም። እስካሁን ይህ ሰው ሠራሽ ቆንስላ እንዳይመሠረት ነበር ያልነው። አሁን ተመሥርቷል፤ በ9 ወር የተወለደው፥ በጥቂት ወራትና ዓመታት ሲያድግ እናየዋለን። ወደ ነበርንበት ሐሰተኞቹን ወደ መግለጥ ተግባራችን እንመለሳለን። 'እኛ ቡችላ ብቻ ነን' የሚሉትን ጃርቶቹን በማቀፉ ሂደት ውስጥ አንዳንዶች የጉማሬ ቆዳ ስለለበሱ እሾሁ አይወጋቸው ይሆናል። እስካሁን በተወጉት ላይ በተጨማሪ የሚውወግጉ መኖራቸው ግን እውነት ነው።

እግዚአብሔር በንጹሕ ኅብረት፥ በግና ተኩላ አብረው በማያድሩበት በሰላም በረት፥ በሰላም ጋጣ፥ በሰላም ግርግም ይባርከን። አሜን።

አመሰግናለሁ።

March 20, 2020




መንፈሳዊ ኅብረት ወይም ክርስቲያናዊ አንድነት ምንድርን ነው? የመንግሥት ሚናስ?

ቆንስላውን ወይም ፌዴሬሽኑን በተመለከተ የምልከታዬ የመጨረሻ ክፍል። በቪድዮ የተዘጋጀው ጽሑፍ።

ባለፈው ሳምንት ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ወይም ፌዴሬሽን እይታዬን አካፍዬ ነበር። ይህ የእይታዬ ሁለተኛና የመጨረሻ ክፍል ነው። ሰሞኑን የተለያዩ ሚድያዎች፥ አንዳንዶቹ ሕዝባዊ፥ ሌሎቹ ማኅበራዊ፥ ሌሎቹ አድርጉ የተባሉትን የሚያደርጉ የካድሬ ሚድያዎች በቆንስላው ወይም ፌዴሬሽኑ ጉዳይ የተረዱትን እያካፈሉን ናቸው።

እዚህ የማካፍለው ወይም የማተኩርባቸው ሁለት ነጥቦች ናቸው። አንዱ የክርስቲያናዊ ኅብረት ምንነት ነው። ሁለተኛው፥ መንግሥት ለወንጌላውያን አማኞች ወይም በአገሪቱ ላሉ ሃይማኖቶች ሁሉ ሙሉ ሃይማኖታዊ ነጻነቶችና መብቶች ለማጎናጸፍና ለማወጅ ከወደደ፥ በቆንስላ ስር መሆንንም ጨምሮ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደማያስፈልገው የሚል ነው።

ጨቋኝ ባልሆነና ሃይማኖታዊ ባልሆነ ዘመናዊ መንግሥት ዘንድ የሃይማኖትና የሕሊና ነፃነት፥ ተሰብስቦ ማምለክም፥ የቀብር መብት ማግኘትም የዜግነት መብት ነው። የአገራችን የሃይማኖት ሕጉ ቀድሞም አሁንም አድሏዊ ነው። አድሏዊ ያደረገው መንግሥት ነው። ፍትሐዊ የሚያደርገውም መንግሥት ራሱ ነው። የኛ መሰብሰብና አለመሰብሰብ አይደለም።

መሰባሰብን በተመለከተ ማወቅ ያለብን፥ በየትኛውም ብሔራውያን የወንጌላውያን ኅብረቶች ውስጥ የቃለ እምነት (Word of Faith) አስተማሪዎች እና የአዲሱ ሐዋርያዊ ዳግም ሥሪት ወይም አሐዳስ (New Apostolic Reformation – NAR) 'ሐዋርያት እና ነቢያት' እንደ ወንጌላውያን አማኞች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ነው። ሁለት ምሳሌዎች ብቻ ብናይ፥

አንደኛ፥ እነ ኬነት ኮፐላንድ፥ ጆወል ኦስቲን፥ ቤኒ ሂን፥ እና ሌሎችም የአሐዳስ እና ቃለ እምነት ሰዎች በአሜሪካ የአሜሪካ ማኅበረ ወንጌላውያን (National Associatio of Evangelicals - NAE) ተቀባይነት የላቸውም። ይህ የሆነበት ምክንያት፥ ከሌሎች ኮተቶቻቸው ጋር፥ ትምህርታቸው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መስመር የወጣ በመሆኑ ነው።

ሁለተኛ ምሳሌ፥ ከአህጉራችን ብንወስድ፥ በናይጄሪያ Christian Association of Nigeria (CAN) የሚባል የወንጌል አማኞች ማኅበር አለ። ሐሰተኛው ነቢይ ቲ. ቢ. ጆሹዋ እና ድርጅቱ የዚህ ማኅበር አባል ሊሆን ጨርሶ የማይታሰብ ነውና አይደሉም። ምክንያታቸው ሐሰተኛ ነቢይ በመሆኑ ነው። በናይጄሪያ ሌላ ጴንጤቆስጣዊ ማኅበርም አለ። Pentecostal Fellowship of Nigeria (PFN) ይባላል። ቲ. ቢ. ጆሹዋ ያ ማኅበርም በግልጽ ያወገዘው ሰው ነው።

እነዚህን የአገሩ ሰዎች አውቀዋቸው ሲነቅፏቸውና ሲያወግዟቸው እያየን የኛዎቹ ደግሞ የነዚህን እንጀራ ልጆች፥ በኅብረት ስም እቀፏቸው፤ 'አንድ ላይ ተቃቀፉና ኑ ድምጻችሁ እንዲሰማ' ይሉናል። የቪዥነሪዎች (ወይም ራእያሞች ነው የምላቸው) ኅብረት እኮ የወንጌላውያን ኅብረት ውስጥ መግባት ስላልቻሉ የመሠረቱት አጸፋ ነው።

ሰማያዊ ዜግነታችን በልጦብን የምድሩን አለመጓጓታችን ጌታን የመምሰል ትሕትና እንጂ ሞኝነት አይደለም። ቤተ ክርስቲያናችንም ሬሳችንም ሲቃጠል ዝም ማለታችን ዘላለማዊው መብለጡን ማወቃችን እንጂ መብታችንን አለማወቃችን አይደለም። እኛ ለነገሩ ዝም አላልንም እንጂ፥ ዝም ብንልም እንኳ መንግሥትም ዝም ማለት አልነበረበትም። መንግሥት ዝም እንዳይል ደግሞ አንድ ዣንጥላ ስር ሆነን ሰላማዊ

ወይም የተቃውሞ ሰልፍ መውጣት አልነበረብንም፤ የለብንምም። አስቀድሞም አድልዎ ያለበትን ሕገ መንግሥት መንግሥት በራሱ ሊያስተካክል የኛን ጉንተላና የኛን፥ 'የተበታተነ የማይሰማ ድምጽ' እንዲሰማ የኛን መሰባሰብ ከፈለገ ሕገ መንግሥቱ አድሏዊ መሆኑን ተቀብሏል ማለት ነው። መንግሥት እስከዛሬ ያላደረጋቸውን ወይም ምናልባት ሊያደርግ ያልቻላቸውን የራሱን ሽንቁሮች እንዳናይ ዣንጥላውን መብት አስከባሪ አድርገን እንድናይ ማድረጉ ስሕተት ነው።

መንግሥት ይህን መሰባሰብ አድርጉና የሃይማኖት አዋጅ እናውጃለን፥ መብት እናስጠብቃለን ሲል የየትኛውን አገር ተሞክሮ ወስዶ ነው? በየትኛው አገር ነው ሃይማኖት መብት ለመሆን ከዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር የተደራደረው? የትኛውም ዲሞክራሲያዊ አገር ለሃይማኖት እና ለኅሊና ነጻነት መብት ተሰባሰባችሁ አመልክቱ ብሎ አያውቅም። መንግሥት የሃይማኖት ነጻነትን ካልፈቀደ አልፈቀደም ነው፤ ከፈቀደ ደግሞ ፈቀደ ነው። ከፈቀደ፥ መጀመሪያ በማኅበር ተደራጁና በርከት ብላችሁ ብትመጡ፥ አንድነትና አንድ ድምጽ ቢኖራችሁ አዋጅ እናውጅላችሁና መብት እንሰጣችኋለን የሚል የዜግነት መብት <u>**ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ አይደለም።**</u>

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለመበታተኗ ዋጋ ከፍላለች ተብሏል። በእውነቱ መቼ ነው የተበታተንነው? ከስንትነት ነው ተበታትነን ስንት የሆንነው? ባለፉት አምስት ዓመታት የፈሉት ሐሰተኞች መብዛት ነው መበታተን ያሰኘው? ከመበታተን አንድ መሆንስ ምኑ ነው? አሁን ይህ ዣንጥላ ከተመሠረተ አንድ ሆንን ማለት ነው? ወይም ኅብረት ተፈጠረ ማለት ነው?

መንፈሳዊ ኅብረት ከኅብረቶች ሁሉ በላይ የሆነ ኅብረት ነው። የገንዘብ ማጠራቀሚያ ዕቁብ፥ የክፉ ቀን መረዳጃ ዕድር፥ የፖለቲካ ፓርቲ፥ የኅብረት ሥራ ማኅበር፥ የሙያ ትብብርም አይደለም። መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ አንድነትና ኅብረት በቃሉ ላይ የቆመ ሁለመናችንን የሚይዝ ኅብረት ነው። ጳውሎስ በኤፌ. 4፥3 *በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።* ይላል። ይህ አሁን ኅብረት፥ ትብብር፥ ካውንስል፥ ፌዴሬሽን የምንለው ነገር የበግና የፍየል ትብብር ሳይሆን የበግና የተኩላ አንድነት ነው። እንኳን ተኩላና በግ፥ በግና ፍየልም ለየቅል ናቸው።

በነዚህ ጥቂት ቀናት በርካታ ዘገባዎችና ቃለ ምልልሶች ውስጥ በቃሉ የተወገዙ ትምህርቶችና በቃሉ የተወገዙ ድርጊቶች ግን <u>**አንዴም እንኳ**</u> በስም ተጠርተው አልተወገዙም። የሐሰት ነቢያት፥ የሐሰት ሐዋርያት አንዴም አልተባለም። ዜግነታቸው የተቀየረ ይመስላሉ። ደግሞም መሥራቾቹም ናቸዋ! እነዚህ የተወገዙ ነገሮች አንዴም ሳይነኩ ለኅብረት ሲባል ግን እቀፏቸው ተብለናል።

ሌላው በነዚህ ጥቂት ቀናት ከሚድያዎቹ መካከል ደጋፊዎችን እንጂ የሚተቹትንና የሚቃወሙትን ለማቅረብ የሞከረ አንድም የለም። የሚቀነቀንለት አንድነቱ ሆኖ ሌላኛው ገጽታው ከቶም እንዲታይ አልተፈለገም። ለምሳሌ፥ ከ15ቱ መካከል የወጣ ወይም የወጡ ሰዎች እንደ ነበሩ ተሰምቷል። ለምን ወጡ? እነዚያ ቀርበው ቢጠየቁ ለምን እንደወጡ የሚሉት ነገር የላቸውም? ሕዝባዊ ተቀባይነት ብቻ እንጂ ሕዝባዊ ምክክር አልታሰበም። አንዱ ብቻ እንጂ ሁለቱም ወገን እንዲቀርብ አልተፈለገም። እንኳን ይህንን የሚያህል ትልቅ ጉዳይ ቀርቶ፥ እንደ ዘፈን ባሉ ስንቅር ባህሎችም እኮ ክርክሮችና ውይይቶች ተደርገው ነበር። ይህ ከዘፈን አንሶ ነው?

'ባትደግፉ ዝም በሉ' እንደተባለው ነው አሁንም። ዝም እንላለንም፤ ዝም አንልምም። ወደ ነበርንበት ሐሰተኞቹን ወደ መግለጥ ተግባራችን እንመለሳለን። ጃርቶቹን በማቀፉ ሂደት ውስጥ እስካሁን በተወጉት ላይ በተጨማሪ የሚውወግጉ መኖራቸው ግን እውነት ነው። እግዚአብሔር በንጹሕ ኅብረት፥ በግና ተኩላ አብረው በማያድሩበት በሰላም በረት ይባርከን። አሜን።

ዘላለም ነኝ።

March 30, 2020




. . . ነው ተጠለሉ የምንባለው?

ከዚህኛው ቀደም ሲል ያካፈልኳቸው ተመሳሳይ አሳብ ካካፈሉት የጥቂቱን ነው።

April 8, 2020

በቪድዮ የቀረበና ወደ ጽሑፍ የተመለሰ።




"እንደው ስር የሰደደ የስሕተት አስተማሪና ትምህርት፥ ወጥ የሆነ የታሰበበት የቤተ ክርስቲያንን ነገር ሊያናጋ የሚችል፥ ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም።"

ዶ/ር ምሕረት ደበበ

# የምር?

ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። ዶ/ር ምሕረት ደበበ (ከቆንስላው መሥራች ኮሚቴ አባላት አንዱ)

በርእሱ ላይ እንዳልኩት፥ ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። የሚል አሳብ ላይ ነው ዛሬ የማካፍለው። ይህ ዣንጥላው፥ ቆንስላው እንዲመሠረት ምክረ አሳብ ያቀረበው ባለ 15 ሰዎች ኮሚቴ አባላት ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠበት ቀን የተነገረ ነው። ጠቅላላውን መግለጫ እዚህ ማግኘት ይቻላል። https://www.youtube.com/watch?v=BTmHBpLCDCc በነገራችን ላይ፥ ማንም ተቃዋሚና ተቃራኒ አሳብ ያለው ሰው፥ ማንም ስጋትና ጥያቄ ያለበት ሰው፥ በዚህ ጉዳይ ላይ በነጠላ ከመጮህ በቀር ሰፊ የሚድያ ሽፋን የሰጡና የመስጠት አቅም ያላቸው የቲቪ ባለቤቶች እንዲቀርቡና እንዲነጋገሩ አልተፈለገም። እነዚህ ሰዎች አንድ አሳብ አቀንቃኝና አስቀንቃኞች ናቸው።

የዛሬው ትኩረቴ ከኮሚቴው መካከል የአንዱ የዶ/ር ምሕረት ደበበ አንድ አሳብ ላይ የሚያተኩር ነው። የነገረን ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለአቅመ አሳችነት የደረሱ አሳቾች አለመኖራቸውን ነው።

"እኔ አላውቅም ፐርሰናሊ፤ እናንተ ታውቁ ይሆናል። እንደው ስር የሰደደ የስሕተት አስተማሪና ትምህርት፥ ወጥ የሆነ የታሰበበት የቤተ ክርስቲያንን ነገር ሊያናጋ የሚችል፥ ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። ደኅና መጽሐፍም የጻፈ ሰው፥ አብዛኛው ስሕተት የምንለው ነገር፥ ከአሳቾች የወጣ ሳይሆን ከተሳሳቱ ሰዎችና ከማያውቁ ሰዎች የተዋጣ ነገር ነው። ይህንን አልሠራነውም ገና በበቂ ሁኔታ እኛ እንደ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ዕድል ላይ ነው ያለነው። እንደነዚያ ዓይነት ልንቋቋማቸው የማንችል ጥልቅ የሆነ የስሕተት ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች ቢነሡ አሁን ያለንበት ሁኔታ ያፈራርሰናል። ለዚያም ራሱ መፍትሔ የሚሆነው አሁን ያሉትን፥ ባለማወቅም ይሁን በተለያዩ ምክንያት አሉ ምንላቸውን ነገሮች ፕሮፕርሊና ፖዚቲቭሊ ኢንጌጅ ማድረግ ይቻላል። በጣም አስቸጋሪና ጥልቅ የስሕተት ትምህርቶች እኮ አሉ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፤ እንደዚያ ለምንለውም ደግሞ ከምሑራንም ይሁን ከቲዮሎጂያንስ የተመለሰና ወጥ የሆነ የተሠራ ሥራም የለም። ስለዚህ የምንሰጋቸው ነገሮች ሊመጡ ይችላሉ፤ ግን አሁን እንደው ከምናስበው የተጋነነ እንዳይሆንም ይሄ መድረክ ለዚያም እንኳን መፍትሔ ነው ሚሆነው የሚል እይታ ነው ያለኝ።"

እንደ ዶ/ር ምሕረት እይታ፥ 'እንደዚህ የሚል እይታ ነው ያለኝ' ነው ያለው፤ አይደል? ይህ የኮሚቴውን የ9 ወራት ሥራ ዘገባ ያቀረቡበት ጋዜጣዊ መግለጫ ነውና የግል እይታ ብቻ አይደለም። ይህ በጋራ መግለጫ የተሰጠበት የጋራና የኮሚቴ እይታ ነው። ይህ፥ ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። ያለው ቃል ሌሎቹም አደናንቀው ያራገቡት ነው።

ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም? አለ ብለን ስለማናስብ የኛ ማሰብና አለማሰብ ነው እንዳለና እንደሌለ የሚወስነው? ለመሆኑ ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ ምን ማለት ነው? የጎበዝ የስሕተት አስተማሪ መለኪያ ምንድርን ነው? ብዙ ሕዝብ ማሳቱ ነው? ስንት ሰው ማሳት አለበት አንድ አሳች አሳች ለመባል? ምንድነው መለኪያው? አሳቹ ባለ 300ና ባለ 500 የሐሰት ትምህርት ማኑዋል መጻፉ ነው? ቀንድና ጥፍር ማብቀሉ ነው? ምንድነው መለኪያው? አገር በቀል መሆኑ ነው? ውጉዝ እንደ አርዮስ መባሉ ነው? ከመጋረጃ ጀርባ ተደብቆ ቡና ማስፈላቱ ነው? እንደ ጂም ጆንስ በአንድ ምሽት 918 ሰዎች በአንድ ምሽት መፍጀት ነው? ጎበዝ የመባላቸውና ጎበዝ የመሆናቸው ምንድነው መለኪያው? እስኪሆኑስ ድረስ አፋችንን ዘግተን መቀመጥ አለብን?

እርግጥ ነው፤ አንዳንድ የአገራችን አሳቾች፥ የሐሰት ነቢያትና የሐሰት ሐዋርያት ቃሉን አያስተምሩም። ስግብግቦች ናቸውና ገንዘብ ላይ ነው ትኩረታቸው። ሁሉም እንደዚያ ናቸው ግን የነዚህ የከፋ ነው። ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ በስሕተት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን፥ አልተቀበሉም። ጎበዝ አሳች ለመሆን ያንን መሆን የለባቸውም። ጨርሶ ስለማያስተምሩም የተደራጀ የሐሰት ትምህርት የላቸውም። ይህ ከአሳችነት ያጸዳቸዋል? ለማሳት 'ጎበዝ የስሕተት አስተማሪ' መኮን አለበት? ወይም ቄስ ግርማ

ዘውዴ፥ "አንድን ሰው ለአቅመ አዳምና አቅመ ሔዋን አልደረሰም እንደሚባለው ሁሉ ባደረግሁት ጥናትና በእኔ መረዳት ተሳስቶ ለአቅመ አሳሳችነት የደረሰ የስህተት አስተማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ብዬ አላምንም።" እንዳለው፥ የለም ብለን እጃችንን አጣጥፈን ብቻ ሳይሆን እኛም ተጣጥፈን መቀመጥ አለብን ማለት ነው? ለማሳሳት እኮ አቅምም ጉብዝናም አያስፈልግም። አቅሙም፥ ጉብዝናውም ያለው አሳች አለ፤ የሱ መሣሪያ ብቻ መሆን ነው የሚያስፈልገው።

አንድ የስሕተት ትምህርት አንድን ሰው ብቻ ካሳተና ከእምነት መስመር ካወጣ ስሕተት ነው መባል የለበትም? 2ዮሐ. 7 *ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው።* ይላል። ይህንን መቼ ነው ዮሐንስ የጻፈው? ገና በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዓመታት። 'ቆዩ መጽሐፍ ይጻፉ፤ ቆዩ ብዙ ሕዝብ ያስቱ፤ ቆዩ ስመ ጥር ይሁኑና ይታወቁ፤ ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ ይሁኑ' አላለም።

ኢየሱስ ሰይጥኖ ነበር የሚል ትምህርት ስለመኖሩ ዶ/ር ምሕረት ወይም ቀድሞም አያውቅም፤ ወይም ለማወቅ አልፈቀደም ማለት ነው፤ ኢየሱስ ለ33 ዓመታት ሰው ብቻ፥ እንደኔና እንደናንተ ያለ ሰው ብቻ ነበረ የሚል ስሕተት መኖሩን ሰምቶ አያውቅም ማለት ነው። ወይም እንደዚያ ብሎ ካስተማረ ሰው፥ ከዘላለም ጌታቸው (ዘላለም ፖዝ) ጋር ለ9 ወራት አብሮ ስለቆየ፥ 'የስሕተት ትምህርት' የሚባለው ነገር ሟሙቶ ጠፍቶበታል ማለት ነው፤ ይመስላል።

በዚህ ዝግጅት ይህንን አንድ ሰው ብቻ (ዘላለም ፖዝን) እና አንድ ስሕተቱን ብቻ (ሌላ ኢየሱስ ማስተማሩን) በማሳየት ትንሽ ስለ ስሕተት ትምህርትና አስተማሪ እናገራለሁ። እዚህ የምወስዳቸው ጥቂት ነጥቦች፥ ከአራት ዓመታት በፊት በ2016 ልክ በዚህ ጊዜ (በኛ በሚያዝያ 2008) ባሰራጨሁት የዕዝራ መጽሔት ጽሑፍ ይህንን የዘላለም ፖዝን ስሕተት በመቃወም ጽፌ ከነበረው ነው። እዚያ ፖዝ ስለ ኢየሱስ ከተናገራቸው ነጥቦች፥ ኢየሱስ ፖዝ አስደራጊ፥ የሰየጠነ ሰይጣን፥ ለ33 ዓመታት ሰው ብቻ፥ እና ታጃቢ መሆኑን የተናገረባቸውን ስሕተቶች ነበር የገለጥኩት። 'ታጃቢው ኢየሱስ' የተባለው፥ እነዚህ ጉረኞች ለመታጀብ ብለው የፈጠሩት ፈጠራና የcelebrity cult በሽታቸው ጠንቶባቸው የፈጠሩት ነው። እዚህ መነሣትም የለበትም። ኢየሱስ የክብር ዘብ ያልነበረው መሆኑን ማንም ያውቀዋል። ይህ ሰይጣኑና ሰውየው ብቻ ኢየሱስ ግን ሌላ ኢየሱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሌላ ኢየሱስ መኖሩንና አሳቾች ያንን ኢየሱስን እንደሚያስተምሩ ይናገራል። *የሚመጣውም ያልሰበክነውን <u>ሌላ ኢየሱስ</u> ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።* 2ቆሮ. 11፥4። ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ ትታገሱታላችሁ አለ ጳውሎስ። ዛሬም እኛም ታገሡ ሳይሆን ጭራሽ የለም እየተባልን ነን።

አንዱን ነጥብ እንይ። ኢየሱስ ሰይጣን ሆነ ወይም የሰይጣንን ባሕርይ ተላበሰ፤ ከጌቴሴማኒ እስከ ትንሣኤው ድረስ ሰየጠነ የሚለው ትምህርት ኮሚቴው ውስጥ ከዶ/ር ምሕረት ጋር ለ9 ወራት በቆየው በፖዝ የተጀመረ አይደለም፤ በእርሱም የሚደመደምም አይደለም። ይህ መርዘኛ ትምህርት የስሕተቱ ዋና አቀንቃኝ የሆነው

የአሜሪካዊው የዊልያም ኬንየን ስሕተት ነው። ዶ/ር ምሕረት በኬንየን ዘመን ቢገኝ ኖሮ፥ ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ እኔ አላስብም። ይል እንደነበር እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ያኔ ገና ብዙ ሰዎች አልሳቱማ! ያኔ ስሕተቱ ገና እንጭጭ ነበራ!

ከWilliam Kenyon በኋላም፥ ከዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ አስተማሪዎች መካከል Kenneth Hagen, Kenneth Copeland, Frederick Price, Benny Hinn እና ሌሎችም ይህንን ትምህርት አስተምረውታል። ቤኒ ሂን፥ 'He [Jesus] who is righteous by choice said, "The only way I can stop sin is by Me becoming it. I can't just stop it by letting it touch Me; I and it must become one! Hear this! He who is the nature of God became the nature of Satan where He became sin! ብሎ ነበር።[1] ጻድቁ ኢየሱስ ነው ይህን እንዳለ ቤኒ ሂን የተናገረው፥ 'ኃጢአትን ማስቆም የምችልበት መንገድ አንድ ብቻ ነው፤ ያም እኔ እርሱን በመሆን ነው፤ ኃጢአት እንዲነካኝ በመፍቀድ ሳይሆን እራሱን በመሆን ነው፤ ይህን ስሙ፤ የእግዚአብሔር ባሕርይ የነበረው ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ በመውሰድ ኃጢአት ሆነ።' ይህ የቤኒ ሂን ትምህርት ነው። ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ መውሰዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም። ኃጢአትና ሰይጣን አንድ አይደሉም። ሰይጣን ሲፈጠር ኃጢአት አልነበረም፤ ኃጢአተኛም አልነበረም። ሊጋርድ የተቀባ ኪሩብ ነበረ፤ እንከን እስኪገኝበት ድረስ። ምንድነው እንከኑ? ኃጢአት። ኢየሱስ ሰይጣን አልሆነም። ኢየሱስ ሰይጣን ሆኖ ነበር የሚል አሳች ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ አይደለም፤ ለዶ/ር ምሕረት።

ኬነት ሄገን ስለ ኢየሱስ መሰይጠን ሲናገር፥ "Spiritual death means something more than separation from God. *Spiritual death also means having Satan's nature. . . .* Jesus tasted death - spiritual death - for every man."[2] "መንፈሳዊ ሞት ማለት ከእግዚአብሔር ከመለየት ያለፈ ነገር ነው። መንፈሳዊ ሞት የሰይጣንን ባሕርይ መውረስም ነው። ኢየሱስ ስለ እያንዳንዱ ሰው ሞትን፥ ማለትም መንፈሳዊ ሞትን ቀመሰ።" ይላል። የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ ሰየጠነ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የሚሉት ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ የሚሉት ነገር ያልተጻፈና የተፈጠረ ነገር መሆኑ ነው። ያልተጻፈውን ነገር ልክ እንደተጻፈ አድርገው ነው የሚናገሩትና መጽሐፍ ቅዱስን የማያነብቡትን የማያስተውሉ ሰዎች የሚያወናብዱት። እኛጋም ያልተጻፈውን የሰዎች ትምህርት ሸምድደው የሚያገሱ ሰዎች ቃሉን የማያነብቡ ሰዎችን ሲያስቱ ገና ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ ለመሆን አልበቁም ይባልልናል።

Fred Price የተባለው ከሄገን ደቀ መዛሙርት አንዱ የመምህሩን ስሕተት የሚያስከነዳ ነገር በመናገር ኢየሱስ መንፈሳዊ ሞትን የሞተው፥ ማለትም፥ ወደ ሰይጣንነት የተለወጠው በትክክል የት እንደነበርም ሊያስረዳ ሞክሯል። እንዲህ ይላል፤ "Somewhere between the time He was nailed to the cross and when He

---

1 በፈረንጆች በ12/1/90 በTBN ቲቪ ከቀረበው ትምህርቱ።

2 እላይ የተጠቀሰው።

was in the Garden of Gethsemane - somewhere in there - He died spiritually. Personally, I believe it was while He was in the garden."[3] በመስቀል ላይ በመቸንከሩና በጌቴሴማኒ አትክልት ስፍራ መካከል ባለው ጊዜ፥ እዚያ መሐል ላይ ነው መንፈሳዊ ሞትን የሞተው። እኔ በግሌ እንደማምነው፥ በአትክልቱ ስፍራ ነው የሞተው።" መንፈሳዊ ሞት መሞት ማለት ከላይ ያየነው ሄገን ኢየሱስን ሰየጠነ ወይም የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ ያለበት ቋንቋ ነው።

ከላይ በጠቀስኩት ከ4 ዓመት በፊት ባሰራጨሁት የዕዝራ ጽሑፍ ይህንን የዘላለም ፖዝን ስሕተት በመቃወም ጽፌ ነበር። እዚያ ከጻፍኩት አንድ ሦስት መስመር ላንብብ፤

"ፖዝ የነዚህን ሰዎች መርዛማ አስተምህሮ እያኘከ ኖሮ፥ ነገር ግን እንደነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በግልጥ ሊናገር ያልደፈረውና ዳር ዳር እያለ ያለው በአገሪቱ ያለውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ተግዳሮት በመፍራት፥ ያለዚያም ወኔ እስኪቀዳጅና በድፍረት ለመናገር ምቹ ጊዜ በማድባት እየተጠባበቀ ይመስላል።" ብዬ ነበር። አሁንማ ለአቅመ ኅበዝ ስሕተት የደረሰ አስተማሪ የለም ከተባለለት ምን ያግደዋል?

ዘላለም ፖዝ ሰይጣን የሆነውን ብቻ ሳይሆን ሰው ብቻ የሆነውን ኢየሱስም አስተምሯል። ኢየሱስ 33 ዓመታት በምድር ሲመላለስ ሰው ብቻ፥ መለኮት ያልሆነ ሰው ብቻ መሆኑን ያስተማረ ሰው ነው ፖዝ። በ2016 (በኛ 2008) በExodus TV Show (ቤተልሔም ታፈሰ) በተዘጋጀው ቃለ ምልልስ ሲናገር ካላቸው ነገሮች መካከል ጥቂት አለፍ አለፍ እያልኩ ላንብብ፤

<u>ክርስቶስ ኃጢአትን አሰረየ የምንልባቸው ነገሮች አምላካዊ ማንነትን አያሳዩም።</u> . . . <u>አንዳንዶች ስግደትን ተቀብሏልና አምላክ ነው ይላሉ፤ ለዳዊትና ሰሎሞንም ተሰግዶአል።</u> . . . አንዳንዶች በውኃ ላይ ሄዶአል ይላሉ፤ ስንቶች አስማተኞች አሉ በውኃ ላይ የሚሄዱ . . . መለኮት ናቸው ወይ? . . . የኛ ጌታ በውኃ ላይ ሲሄድ 'መለኮት ስለሆንኩ ሄድኩ' አላለም። ጴጥሮስም በውኃ ላይ ሄዶአል። ውኃ ላይ መሄድ መለኮት አያሰኝም። . . .

እኔ ዘላለም መለኮትን እንዴት ብለህ ስለምታምን ነው በምድር ላይ አልተጠቀመም ብለህ ያልከው? መለኮትን ገልጧል? ተአምራት መለኮት አይደለም። ተአምራት መሥራትሽ፥ የሆነ ነገር ማድረግሽ መለኮትነትሽን አያሳይም። . . . ለምሳሌ በምድር ላይ ሠላሳ ዓመት ሲመላለስ መለኮት ተገልጦበታል? ወይንስ መንፈስ ቅዱስ ተገልጦበታል? በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት በጥበብም በሞገስም ያድግ ነበር ነው የሚለው።

. . . <u>በምድር ላይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ አልተመላለሰም።</u> አሁን በሰማይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው። ዱሮ ወደ ምድር ሳይመጣ በፊት ፍጹም አምላክ ብቻ ነበር። በምድር ላይ ቤዛ ሲሆን በሰው ማንነት ሁለተኛው አዳም ሆነ። የአዳምን

[3] እላይ የተጠቀሰው።

ቤዛነት በሚጨርስ ማንነት እራሱን ባዶ አድርጎ በምስሉ እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋርዶ ነው ሚለው። ጳውሎስ ነው ሚለው፤ የጳውሎስ መረዳት ነው ያለን።

. . . እስከ 30 ዓመቱ ማንኛውም ሰው የሚኖረውን ነው የኖረው፤ አናጢ ነበር ነው የሚለው፤ በቃ ኖርማል ነገር ነው። ከ30 ዓመቱ በኋላ ግን የጌታ መንፈስ በኔ ላይ ነው ብሎ የተቀባው መሢሕ አገለገለ ማለት ነው። ጌቴሴማኒ ጽዋውን ከጠጣ በኋላ ቤዛ ሊሆነን እያንዳንዷን የኃጢአተኛ ዋጋና ሥርዓት ከፈላት ማለት ነው፤ እስከ መስቀል። ከሙታን ሲነሣ የ30 ዓመቱ ኢየሱስ ነው? የ3 ዓመቱ አገልግሎት ነው? መስቀል ላይ ያለው ነው? አይደለም። አሁን በሌላ ክብር አይደል ምናውቀው? እስኪ ጳውሎስ ያለውን ጥቅስ ልጥቀስና ልጨርስልሽ፤ 2ቆሮ. 5 ማለት ነው፤ ክርስቶስን በሥጋ ያወቅነው ብንሆን እንኳ ከዚህ በኋላ እንደዚህ አናውቀውም ይላል። በሌላ መልክ እናውቀዋለን ማለት ነው። ስለዚህ መገነጣጠል ለምን አስፈለገ? እንግዲህ የሰነፍ አሳብ ነው።

የፖዝ ኢየሱስ በምድር ባገለገለበት ዘመን ሰው ብቻ (ሰውየው) ኢየሱስ ነው። ተወልዶ እስከሚሞት እንደ ሰው ብቻ ኖሮ ከሞት ሲነሣ ግን እንደገና አምላክና ሰው ሆነ። በሥጋው ወራት መለኮት ያልነካው፤ አማኑኤልነትን ያልተቀዳጀ፤ መንፈስ ቅዱስ እኛን እንደሚረዳን ብቻ የረዳው፤ ነፋሱ፥ ማዕበሉና ተፈጥሮ የታዘዘው በመለኮትነቱ ያልሆነ፥ 'እወዳለሁ ንጻ' ብሎ ያነጻው በመለኮት ያይደለ፥ ደካሞችን ወደራሱ የጠራ ወደ ሰውነቱ ብቻ የሆነ፥ የሰንበት ጌትነቱ የሰው ጌትነት ብቻ የሆነ፥ ቃል ተናግሮ በውኃ ላይ የሚያስኬድ የሰውነቱ ቃል ብቻ የሆነ፥ በፊታቸው ተለውጦ እንደ ፀሐይ የበራ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስነቱና የአይሁድ ንጉሥነቱ ሲጠየቅ እውነቱን የገለጠው ሰውየው ብቻ ኢየሱስ ነው! ታዲያ ይህ ሌላ ኢየሱስ አይደለም?

ትናንት ስለዚህ ጉዳይ ከለጠፍኩ በኋላ ብዙ አስተያየቶች በፌስቡክ ገጼ ተጽፈዋል ከጻፉት መካከል ቢሾፕ አምኃ ይገኛል። አምኃ በዘላለም ፖዝ ድርጅት ውስጥ ለአያሌ ዓመታት ያገለገለና ስሕተቱን ተረድቶ የወጣ ሰው ነው። ወንድም ነው። አስተያየቱ ይህ ነው፤

Bishop Ameha እኛ የሆነውን እና እየተማርን ያደረግነውን ሰውየው ዶክተር ተብየው ያውቁት ይሆን ? ለማንኛውም እኛ ያደግንበትን አስተምህሮ፤ (1) ቤተክርስቲያን ሚስቴ ናት (2) እኔ ሙሽራው ነኝ (3) እኔ የመጨረሻው መልዕክተኛ ነኝ (4) እኔ የወይን ግንድ ነኝ (5) እኔ ምንጫችሁ ነኝ (6) እኔ በኩር ነኝ (7) እኔ የመጨረሻው አባት ነኝ (8) እኔ የኢትዮጵያ በር ነኝ (9) እኔ የመጨረሻው መልዕክተኛ ነኝ (10) የመሲሁ ትንቢቶች ለእኔ ናቸው (11) ኢየሱስ ሰው ብቻ ነው በምደር (12) ኢየሱስ ሦስቴ ተወልዷል (13) ኢየሱስ ሰየጥኗል (14) መስቀል የተሰቀለው የእግዚአብሔር ልጅ ሳይሆን ሰይጣን እራሱ ነው (እባቡ )ነው (15) ወዘተ ለዶክተር ለሳይኮሎጅስቱ ይህ ሀሰት ከሆነ እብደት ነው።

ያ ለ33 ዓመታት የተመላለሰው ኢየሱስ ሰውና አምላክ (ሰዋምላክ - ቴአንትሮፖስ) የሆነው ሳይሆን ሰው ብቻ የሆነው ኢየሱስ ነው። አንድ ባህርይ ብቻ ያለው ኢየሱስ። ታዲያ ይህ ሌላ ኢየሱስ አይደለም?

ሌላነቱ ብቻ አይደለም፤ የሚገርመው፥ ግንዛቤውም ነው። ኢየሱስ ያንን ሁሉ ያደረገው እንደ ሰው ብቻ ሆኖ ከሆነ እኛም አሁን ያለምንም መከልከል ያንን ማድረግ እንችላለን። ቃላችን እንደ ቃሉ መፍጠር ይችላል። ነገሮችን ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት ይችላል። ቃል እምነት የሚባለው ስሕተት ያ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተደረጉት ትልልቅ ጉባኤዎች በኢየሱስ ማንነት ላይ የተከራከሩና ያረጋገጡ ጉባኤዎች ነበሩ።

በኬልቄዶን በ325 ዓ. ም. የተደረገው በአርዮስ ትምህርት ላይ፤

በ381 ዓ. ም. በቁስጥንጥንያ የተደረገው በአርዮስ፥ በአቡልናርዮስ፥ እና በሰባልዮስ ትምህርት ላይ፤

በ431 ዓ. ም. በኤፌሶን የተደረገው በንስጥሮስ፥ በጳላግዮስ ትምህርት እና በእመአምላክነት ጉዳይ ላይ፤

በ451 በኬልቄዶን የተደረገው በአውጣኪ እና በኢየሱስ መለኮትና ስብዕና ላይ (ይህ 4ኛው ጉባኤ አውጣኪና የአንድ ባሕርይ ትምህርቱ በአገራችን ተዋሕዶ የሚባለው የተወገዘበት ትምህርት ነው)።

እንዲህ እያልኩ ቀጣዮቹን ጉባኤዎችም መዘርዘር ይቻላል። ነጥቤ፥ እነዚህ ጉባኤዎች ስለተቀመጡና ተነጋግረው እምነታቸውን ስለገለጡ ወይም ስሕተትን ስላወገዙ ብቻ ትክክል ናቸው ማለት ሳይሆን የተነጋገሩባቸው የቃሉ እውነቶችና ያወገዟቸው የተሳሳቱ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ወይ ማለት አግባብ መሆኑና እነዚህ ስሕተቶች እንዳልኖሩ መቁጠር ስሕተት መሆኑን ነው። ለአቅመ ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ መሆን የደረሰ አሳች የለም ከተባልን ትጥቃችንን ፈትተትን እንተኛ!

የኒቅያ ጉባኤ የተቀመጠው አርዮስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተለየ ማንነት ስላለው ነው ብሎ ያስተማረው ትምህርት ስለናኘ ነበር። ዘመናዊዎቹ አርዮሳውያን የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት የሆነው የዋችታወር ተከታዮች ይህንን ነው የሚያስተምሩት። ንስጥሮስ የተባለው ኢየሱስ ሰው ብቻ ሆኖ ነገር ግን በአምላክ ቃል (ሎጎስ) ይደገፍና ኃይል ያገኝ ነበር ይላል። አውጣኪ የተባለው ክርስቶስ ሰውም አምላክም ያይደለ ሦስተኛ ሌላ (በሮማይስጥ tertium quid) ነው ብሎ ነበር። ይህን ተከትሎ ሞኖፊሳይቶች (አንድ ባሕርይዎች) መለኮታዊው ባሕርይ ሰብዓዊውን ሰልቅጦታል የሚል ትምህርት ገነነ። እንዲህ እያሉ የክርስቶስን መለኮትና ስብዕና በተመለከተ የተፈጠሩትን ስሕተቶች ሁሉ ለመዘርዘር ብዙ ናቸው። ለፖዝ የተገለጠው የሰውየው ኢየሱስ ስሕተት አዲስ ስሕተት አይደለም።

በአገራችንም እንኳ በኛ ቆጠራ በ1870 ዓ. ም. በቦሩ ሜዳ የተደረገው ጉባኤ በክርስቶስ ማንነት ላይ ነበረ። ቀድሞ ቅባት፥ ካራ፥ ተዋሕዶ፥ እና የጸጋ ልጅ የተባሉ በክርስቶስ ማንነት ላይ የነበሩ የቆዩ የተለያዩ ትምህርቶች ነበሩ። ወደነዚህ ሁሉ በዝርዝር መግባት ራሱን የቻለ ሥራ ነው። ግን የቀደሙትም ሆኑ የአገራችን ጉባኤዎች እዚህ ሰየጠነ፥ ሰው ብቻ ነው፥ በተባለው ኢየሱስ ላይ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። የፖዝ አቋም ኢየሱስ ከጽንሰቱ እስከ ትንሣኤው ሰይጣንነትንም ጨምሮ፥ ሰው ብቻ ነው እንጂ ምንም መለኮትነት የለውም የሚል ነው። ታዲያ ይህ ሌላ ኢየሱስ አይደለም? ይህ የስሕተት ትምህርት አይደለም? ምን ሲሆን ነው ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ የሚባለው? ኀበዝ የስሕተት አስተማሪን ማን ነው የሚለካልን? የሚመዝንልን? የኀበዝ ስሕተት አስተማሪን መለኪያውንስ ማን ነው የሚሰጠን?

ይህንን የስሕተት አስተማሪዎችን ማንነት የሚያሳየንን መለኪያ የሚሰጠን ቄስ ግርማ ነው? ዶ/ር ምሕረት ነው? የሚሰጡንስ በዘልማድና በስነ አእምሮ ልኬት ለክተው ነው? ወይስ መለኪያችን ስለ አሳቾች ማንነት ገልጦ የሚነግረን ዘመን የማይሽረው ቅዱስ ቃሉ ነው? ዞሮ ዞሮ የዚህ፥ ‘ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ የለንም’ የሚባለው ነገር ጉዳይ፥ የቆንስላውን ነገር እንድንቀበል የሐሰት አስተማሪዎችንም ሳይቀር፥ ‘ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ አይደሉም’ ተብሎ ‘በአንድ ዣንጥላ ስር ተጠጋግታችሁ ቁሙና እንጠለል፤ ተጠለሉ፤’ እንዲባል ነው።

ኀበዝ የሐሰት አስተማሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ? ለአቅመ አሳችነት የደረሱ አሳቾች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ? ምን ጥያቄ አለው? ለማሳት ደግሞ ኀበዝ መሆን የለብህም። ሰነፍ አሳችም ሆነህ ኀበዝ አሳች የሚያስተውን ያህል ማሳት ይቻላል። ለማሳት አቅም ወይም ጉብዝና ሳይሆን ለአሳቹ ራስን መሸጥ ብቻውን በቂ ነው።

ከሐሰተኞች እንራቅ፤ ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጋር እሽኮለሌ እንድንጫወት ከሚጋብዙንም እንጠንቀቅ። ዶ/ር ምሕረት ደበበና ቄስ ግርማ ዘውዴ በምን ስሌት አስልተው፥ በየትኛው መጽሐፍ መርምረዋቸው፥ ከየትኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጋር አስተያይተው፥ ‘ኀበዝ አሳቾች የሉም’ እና ‘ለአቅመ አሳችነት የደረሱ የሉም’ እንዳሉ አላውቅም። እኔ እስከተረዳሁት ድረስ፥ በምካቴ ክርስትና ዘርፍም የአቅሙን እንደሚያካፍል ሰው፥ ‘ኀበዝ አሳቾች የሉም’ ማለትና ‘ለአቅመ አሳችነት የደረሱ የሉም’ ማለት ለአሳቾች ጥቃት የሽፋን ተኩስ መስጠት ነው። የሽፋን ተኩስ መስጠት ማለት ዋናው አጥቂ በአንድ በኩል ሊወርርና ሊያጠቃ ሲዘጋጅ፥ በተቃራኒው አቅጣጫ ተኩስ መክፈትና ተከላካዮች ወደዚያ እንዲያተኩሩና እንዲሳቡ ማድረግ ነው። ያኔ ዋናው አጥቂ ሥራውን መሥራት ቀላል ይሆንለታል። በኔ መረዳት፥ ‘ኀበዝ አሳቾች የሉም’ ማለትና ‘ለአቅመ አሳችነት የደረሱ የሉም’ ማለት ራሱ አሳችነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ይነሣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ ነው ያለን እንጂ ለአቅመ አሳችነት የደረሱ ኀበዝ አሳቾች ይነሣሉ አላለንም። አሳቾችንና የስሕተት አስተማሪዎችን የሚገልጥልን የሰዎች መለኪያና ነሲባዊ ግምታቸው ሳይሆን፥ ዘመን የማይሽረው ቅዱስ ቃሉ ነው። ቅዱስ ቃሉ። ቃሉን እንመርምር፤ ቃሉን እንበርብር። ወደ ጌታ ቃል እንቅረብ፤ ወደ ቃሉ ጌታም ደግሞ።

April 21, 2020




የዣንጥላው ነገር . . .

የቆንስላው ፈብራኪ (የቅድመ ምሥረታው ምንጭ ወይም አመንጪ፥ ዲዛይነር ወይም አርኪቴክት፥ ነዳፊና ቀራጺ) ማንም ይሁን፥ ስለ ክርስትና በአጠቃላይ እና በተለይም ስለ ኢትዮጵያዋ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንና የቀደመ ታሪኳ እውቀት የሌለው ሰው ነው። እውቀት ከኖረውም ደንታ የሌለው ሰው ነው። ደንታ ከሌለው ቆንስላውን ለፖለቲካ ፍጆታና መገልገያ እንዲሆን ብቻ የቀረጸው የችግር ጽዋ ነው። የሚብሰው ችግር ጽዋው ብቻ ሳይሆን፥ ከጽዋው የሚቀዳው ምን ይሆን? ጠጪዎቹስ እነማን ይሆኑ? የሚለው ነው። ጽዋው የችግር ዋንጫና የገፈት መጠጫ ነው።

ወንዝን መፍሰሱ በራሱ ንጹህ አያደርገውም። ምንጭ ከቆሸሸ ጅረቱም ቆሻሻ ነው። መፍሰሱ ወይም እንዲፈስስ መደረጉ፥ ወይም መፍሰስ መቻሉ አያነጻውም። ወደ

ቆንስላው ጅማሬ ብቻ ሳይሆን ከጅማሬው በፊት ወዳለው ዳራ ሄደን፥ 'ለቆንስላው ጅማሬ እነማን ምን ጥናት አድርገው፥ ምን ነድፈው አቀረቡ?' ማለትና 'እነዚያ 'እነማን' ደግሞ እነማን ናቸው?' ማለቱ ተገቢ ጥያቄ ነው።

ምክረ አሳብ ኮሚቴው 9 ወራት አርግዞ ወልዷል። መቼም፥ ከመረገዝ በፊት ብቻ ሳይሆን፥ ከጽንስ በፊትም ብቻ ሳይሆን ከዚያም አስቀድሞ በአሳብ ደረጃ የሚደረጉ ሂደቶች አሉ። የለም ቃል ሥጋ እንደሆነው ነው ካሉም ይንገሩን። በኔ መረዳት ከ400ው ጥሪ በፊት የታሰበ አሳብ አለ፤ የተነደፈ ንድፍ አለ። በዚያ ንድፍ ውስጥ እጃቸው ያለ ሰዎች ቢታወቁ ቆንስላው ማንን እንደሚመስል ከመገመት እንድናለን። ልጅ ወላጁን መምሰሉ ገሃድ ነውና።

April 26, 2020

የገነጋላው ነገር . . .




ቆንስላው ሕገ መንግሥታዊ ነው? ሕጋዊ ነው? ወይስ ቤተ መንግሥታዊ?

ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ሲመሠረት የሚሟ የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር የሚባል ነበረ። በመጀመሪያ በ1948 ኋላ ቃለ ሕይወት በሆነችው የኤስ አይ ኤም ማኅበራት ተወካዮች ተመሥርቶ፥ በ1953 ደግሞ ሦስት አብያተ እምነት (ቃለ ሕይወት፥ የወንጌላውያን መጥምቃውያን ማኅበር እና የክርስቶስ አንድነት ወንጌላዊት ማኅበር) ሆነው ያጠነከሩት ጤናማ ማኅበር ነበር።

ከመጀመሪያው ምሥረታ በኋላና ከሁለተኛው ዙር መጠናከር በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንግሥታዊ ሃይማኖት የሆነችበት አዋጅ በ1952 በመውጣቱ ወይም መንግሥት ኦርቶዶክሳዊ በመሆን ሌሎች ሃይማኖቶችን የሚጫን አድሏዊ በመሆኑ ምክንያት ለሚደርሱባቸው ሃይማኖታዊ ጭቆናዎች ለመጸለይም፥ ለመወያየትም፥ በጋራ ለወንጌል ሩጫ ለመትጋትም የጀመሩት ማኅበር ነበረ። “ያለ ሕግ የሚደርስባቸውን መገፋት እንደ ባለ አእምሮ በሕግ ለመቋቋም ሕጋዊ ማኅበርን ለመመሥረት የመጀመሪያ ስብሰባቸውን በኤስ አይ ኤም ግቢ በ1948 አደረጉ። የጋራ ችግራቸውን በጋራ ለመጋፈጥ እና ለታላቁ ተልእኮ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚቆሙበት ይህ ማኅበር፥ ‘የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር’ የሚል ስያሜ ተሰጠው። (ወንድዬ አሊ፥ የእኩል ሌሊት ወገግታ፥ ገጽ 309።) ይህ ማኅበር እስከ ደርግ ዘመን ፍጻሜ ቆይቶ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን መመሥረት ተከትሎ የሚሟ ማኅበር ነው። አንድ ጊዜ በማኅበሩ አጠቃላይ ስብሰባ የመካፈል ዕድል ገጥሞኝ ነበር።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በስደት ማግሥት የተጀመረ፥ ሁሉንም ለማቀፍ የሞከረ፥ ኋላማ ሐሰተኞቹንም ተባባሪ አድርጎ የተቀበለ አስደሳች ኅብረት ነበር/ነው። ሆኖም ህ ኅብረት ከነ ድክመቶቹ ጥሩ ያገለገለ ኅብረት ነው። ቆንስላው ሲመሠረት ከመሥራቾቹ ሆኖ በመግባት ተዋጠ። አሁን ንዑስ ስብስብ (sub set) ነው። በውስጡ ጉምቱ አብያተ እምነቶችን የያዘ ቢሆንም በኅብረቱ ንዑስ ስብስብነት እነዚያም በሳል አማኞችና አገልጋዮች፥ እንዲሁም አብያተ እምነቶቹ ራሳቸው እንዲሚሸሹ ምክንያት ሆኗል። በአንድ ፊቱ ይህ ኅብረት ቀድሞውኑ ሚሙቶ በስሩ ያሉት አብያተ እምነቶች እንደ ቃለ ሕይወትና እንደ መካነ የሱስ በነጠላ እንዲገቡ ወይም ካልፈለጉ እንዳይገቡ በለቀቀ በተሻለ ነበረ። የድምጽ ጉራማይሌ መኖሩ ሳይዘነጋ ነው። ከወዲያ ሐሰተኞቹ አንዳችም ሳይባሉ እንዳሉ አሉ። ከወዲህም ግርምታው ወደ ግርታ ተቀይሯል።

የቃለ ሕይወትና የመካነ የሱስ አብያተ እምነት (ሁለቱም በጤናማው ስሌት የአገሪቱን ወንጌላውያን አማኞች 70% ግድም የያዙ መሆናቸው ሳይዘነጋ) የተሸነገሉበት አካሄድ በግልጽ ታይቷል። ከሌሎቹ በዕድሜና በቁጥርም ባይሆን በታሪክና በአገልግሎት አቻዎች ከሆኑት ተለይተው ለብቻ መሥራች የሆኑበት አካሄድ ከቶም ጤናማ አይደለም። ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያኔ በመሆኗ ከዚህ እንድትርቅ አሳቤን አካፍዬ ነበር። ሳካፍል ምናልባት ዘግይቼ ሳልሆን አልቀርም፤ ወይም ከዚህ ስሕተት ውስጥ አትገባም የሚል የስንፍና መመካት ነበረብኝ፤ ብቻ ድምጼ ተሰሚ አልሆነም፤ ወይም ሌላ የሥልጣን ስሌት ጨዋታው ውስጥ ገብቷል ማለት ነው። ወይም አስቀድሞም አንዳች የማመቻመችና የመቻቻል ልክፍት ወደ አብያተ እምነቶቹ ሳይገባ አልቀረም። ሐሰተኛው ነቢይ እስራኤል ዳንሳ ላፍቶ ቃለ ሕይወት እና ደሴ መካነ የሱስ ገብቶ ሲያስት በአደባባይ ለተደረጉ ማሳቶች በጓዳ ምላሽ ሰጥተው ከሆነ አላውቅም፤ የጓዳ ስለሆነ፡ በአደባባይ ዝም ማለታቸው ግን በፎርፌ የመሸነፍ ያህል ተቆጥሮባቸዋል። እኔም ቆጥሬዋለሁ።

ዣንጥላው ውስጥ በነጠላ መግባት አብያተ እምነቶችን ብቻ ሳይሆን አጥቢያዎችንም ያካትታል። በተለይ ራሳቸውን ከአቅማቸው ያለፈ ያገዘፉ አጥቢያዎች ለራሳቸው ትልቅ ስም የለጠፉና ራሳቸውን በአክብዶት ያራቁትም አሁን በአክብሮት ተጠግተዋል። እውጪ ያሉትም የዲያስጶራ ማኅበራት ንዑስ ስብስቡ ውስጥ (የኢወአክኅ ውስጥ) መኖራቸውንና በታሳቢነት መግባታቸውን ወዲያው ረስተው እንደገና ወጥቶ መግባት ወይም ክፍል መቀየር እያማራቸው ነው።

የመንግሥትና የፖለቲካው ነገርማ፥ እሱ እየቆየን ይቆየን። ከመጀመሪያዎቹ 400 የቤተ መንግሥት ግብዣ እስከ በቀደሙ የቆንስላው መሪዎች የራት ግብዣና ስጦታም ጉዳይ፥ ‘ . . . አይታ ማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ’ ሆኗል። ወደ ቀብሯ እየሄደች የተባለላት ነው። ወደ ቀብሯ።

ቆንስላው ሕገ መንግሥታዊ ነው? ሕጋዊ ነው? ወይስ ቤተ መንግሥታዊ? ብሎ ለመጠየቅ ያስገደደኝ ሕገ መንግሥታዊ ሊሆን እንደማይችል ሕገ መንግሥቱን ምስክር

መጥራት ስለሚቻል ነው። ሕጋዊ ለመሆን ደግሞ ሕጋዊ ውክልና ባላቸው ማኅበራት አካል እና ወኪሎች አሳብ አመንጪነትና አስጀማሪነት መጀመር ስለሚኖርበት ነው።

የቀረው አማራጭ ቤተ መንግሥታዊነት ነው። አንድ ሃይማኖታዊ ማኅበር ከአዋጅም፥ ከሕገ መንግሥትም፥ ከሕጋዊ ማዕቀፍም ውጪ በቤተ መንግሥት ውስጥ መመሥረቱ ሕጋዊም ሕገ መንግሥታዊም አያደርገውም። ቤተ መንግሥታዊ ግን ያደርገዋል።

የዣንጥላው ነገር።

ዘላለም ነኝ።

May 7, 2020

የሚንስትሮች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ሕጋዊ ዕውቅና ለመስጠት የወጣውን ረቂቅ አዋጅ ዛሬ እንደተቀበለ ከጠቅላይ ሚንስትሩ ፌስቡክ ገጽ ተገለጠ። ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጁን ለሕዝብ ተወካዮች መርቶታል።

በዚህ ሰሞን ከሁለት የቅርብ ባልንጀሮቼና ሌላ ሦስተኛ ወዳጃችን ጋር ሁለት ጊዜ በዙም ስብሰባ አድርገን ከነዚህ በቆንስላው ላይ ከምጽፋቸው ነገሮች እንድታቀብ ብዙ ብዙ ነገሩኝ። ስላልተግባባን ወደ መከፋፋትና መለያየት አለፍን። እኔ እነሱ ቆንስላውን ከልብ ማፍቀራቸውን አላጥላላሁም። እንዲያቆሙም አልጠየቅኋቸውም። ምርጫቸውን አከብረዋለሁ። እነሱ ግን እኔ መንቀፌን እንዳቆም መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ቢችሉ ለማስገደድም የሚችሉትን ያህል ሄዱ። ይህንን ቅርርብ መሻከር ለመቅረፍ ከ3 ዓመታት በላይ ቆይተናል። አቋማቸው የተለወጠ አልመሰለኝም። የኔ በእርግጥም አልተለወጠም። ቆንስላው ዛሬም የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ጥቁር ነጥብ ነው ባይ ነኝ።

ከጓደኞቼ ጋር ንግግራችንን በሁለት ሳምንታት ውስጥ ነው በሁለት ዙር ያደረግነው። ሳንግባባ እንደተለያየን በማግሥቱ የቆንስላውን አመሠራረት ስሕተት እና አደገኛ እርምጃ መሆኑን አካፈልኩ።

May 7, 2020




የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አመሠራረት በሁለት ትልልቅ ምክንያቶች ስሕተት እና ለኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና አደገኛ እርምጃ ነው።

May 8, 2020 (በማግሥቱ) በፌስቡክ በአጭሩ ዋናውን ነጥብ አጋርቼ ቪድዮውን አካፈልኩ። አጭሩ ዋና አሳብ ይህ ነው። ረጅሙንና የቪድዮውን ሊንክ ከታች አስቀምጣለሁ። 'ሁለቱ ምክንያቶች እና የምናልባት መፍትሔዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አመሠራረት ሁለት ስሕተቶች እና አደጋዎች።

የመጀመሪያው ስሕተትና አደጋ እውነትና ሐሰት ተደባልቀው የጀመሩት፥ እውነተኛ ወንጌላውያንና ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት በአንድነት ሆነው ከመሥራች ኮሚቴው ጀምሮ ተባብረው፥ ተነባብረው የመሠረቱት በመሆኑ ነው።

ለዚህ መፍትሔው በኅብረት መደባለቅ ሳይሆን ሐሳውያኑ ስሕተታቸውን እንዲያውቁ፥ እንዲጸጸቱ፥ እንዲናዘዙ፥ ንስሐ እንዲገቡ፥ የጎዷቸውን ሰዎች ይቅርታ እንዲጠይቁ፥ ለበደሏቸው እንዲክሱ፥ ያሳቷቸውን ሰዎች ማሳታቸውን እንዲያምኑ፥ እውነቱ የቱ መሆኑን ገልጠው ተናግረው ቀድሞ ያስተማሩትና ያለማመዱት የማሳት አካሄድ ስሕተት መሆኑን እንዲናገሩ እውነተኛ መመለስ እንዲሆንላቸው ማድረግ ነው።

ሁለተኛው ስሕተትና አደጋ የካውንስሉ ጅማሮው መንግሥታዊና ቤተ መንግሥታዊ መሆኑ ነው። ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 11፥1-3 ይህን ይላል።

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።

2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።

3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

ሰኔ 13፥ 2011 የተደረገው ይህንን ያፋልሳል። ስሕተቱ ምንድን ነው? ሃይማኖቶችን በጣጥቆ ለተለያዩ ሃይማኖቶች የተለያዩ አዋጆችን ማወጅ፥ ሃይማኖቶችን ለያይቶ የተለያዩ አዋጆችን ማወጅ ሃይማኖቶችን በእኩል ዓይን ያለማየት ነው። መነሻው አሳብ ተበታትናችኋል፤ ተሰባሰቡና ጥያቄአችሁን አቅርቡ፥ መብታችሁንም አስከብሩ የሚል ነው።

መፍትሔው መንግሥት ሃይማኖቶችን ለአዋጅ በሚመች መልክ የሚያሰባስብበት ሳይሆን በእኩል ዓይን የሚያይበት ሕገ መንግሥት እና አዋጅ ሊኖረው ይገባል። ከሕግ በታች ሁሉም ዜጋ ሳይሳቀቅ፥ አንዱ ከሌላው እኩል መሆኑ የሚታወቅበትና የሚረጋገጥበት፥ አንዱ ሕጋዊ ሃይማኖት፥ ሌላው ሕጋዊ ማኅበር ሳይሆን ሁሉም፥ ማንም ከማንም ሳይለይ በሕግ ዓይን ፊት እኩል የሚሆኑበት፥ መብታቸው እኩል፥ ግዴታቸው እኩል የሚሆኑበት፥ ማኅበረ ሰቡንና የዜጋውን መሠረታዊ መብቶች የሚጎዱበት ነገር ከኖረ ሊገደቡ የሚችሉባቸው፥ ሌሎች ሃይማኖታዊ ጥቅሞችም፥ በንጹሕና ዘላቂነትና ቋሚነት ባለው መልኩ መደንገግ ነው።

. . . . .

'እመለስበታለሁ።' ካልኩ በኋላ በቪድዮ ነው ያቀረብኩት። ይህ የቪድዮው ሊንክ ነው፤ https://www.youtube.com/watch?v=S5iihCTg02c ወደ ጽሑፍ የተመለሰው ደግሞ ይህ ነው።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አመሠራረት በሁለት ትልልቅ ምክንያቶች ስሕተት እና ለኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና አደገኛ እርምጃ ነው።

ሁለቱ ምክንያቶች እና የምናልባት መፍትሔዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. እውነትና ሐሰት ተደባልቀው የጀመሩት በመሆኑ ነው። እውነተኛ ወንጌላውያንና ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት በአንድነት ሆነው ከመሥራች ኮሚቴው ጀምሮ ተባብረው፥ ተነባብረው የመሠረቱት በመሆኑ ነው።

ስሕተቱ፤

መጽሐፍ ቅዱስ ከአሳቾችና ከሐሰት አስተማሪዎች እንድንርቅና እንድንገልጣቸው እንጂ ከእነርሱ ጋር ተባብረን እንዳንገኝ ያስጠነቅቀናል። ይህን አድርገን ከተገኘን የጌታን ቃል እና ቃሉን የሰጠውን ጌታም መናቃችን መሆኑ ነው። ክርስቲያኖች ከጨለማ ሥራ ጋር እንዳይተባበሩና እንዲገልጡት ተነግሮአል፤ ኤፌ. 5፥11። ከቃሉ ጋር የማይተባበር

ቢኖር እንዲያፍር ከእርሱ ጋር እንዳይተባበሩ ተናግሯል፤ 2ተሰ. 3፥14። ማንም ጤናማውን የጌታን ቃል ትምህርት ይዞ ወደ ቤታቸው ባይመጣ እንዳይቀበሉትና ሰላምም እንዳይሉት ተናግሯል፤ 2ዮሐ. 10። ከሐሰተኛ ነቢያት እንዲጠነቀቁ ይመክራል፤ ማቴ. 7፥15። ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች ናቸውና አገልጋዮች ከነዚህ እየተጠበቁ መንጋውን በመጠበቅ እንዲተጉ ይናገራል፤ ሐዋ. 20፥ 28-30። እነዚህ አሳቾች ምን እንደሚመስሉና ከእነርሱ እንዲርቁ ሰፊ ትምህርት ይሰጣል፤ 2ጴጥሮስ እና ይሁዳ። እነዚህን የመሰሉ ብዙ ትምህርቶች በቃሉ ውስጥ ይገኛሉ።

ቆንስላውን ከመሠረቱት መሥራች አንዱ የራዕያም (ቪዥኑሪ) አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሲሆን በዚህ ማኅበር ውስጥ ኢየሱስ ሰው፥ ኢየሱስ ሰይጣን፥ ሰው አምላክ፥ የእግዚአብሔር ዓይነቶችና የእግዚአብሔር መደብ የሆንን፥ ከዘላለም ወልድ ያልሆነ፥ ኢዮብ ከፍት አፍ፥ ፈውስ መብታችን፥ ብልጽግና የኛ፥ የሚሉ ሰዎች ሰዎችና ማኅበራትም አሉባቸው። ገንዘብ ሲወዱ እንደ ይሁዳ፥ አገዛዛቸው እንደ ኩባንያ፥ በጅምላና በችርቻሮ ሲሸጡና ሲሸቅጡ ከሸቀጥ እስከ ጸሎትና እስከ ቃሉ ድረስ የሆኑ ሰዎች አሉባቸው። የውሸት ትንቢቶችን ደግሞ ደጋግሞ በመናገር ሬከርድ የሰበሩ ሐሰተኞች ይገኙባቸዋል። መድኃኒት እያስጣሉ የሚያምኗቸውን የቀሆችና አላዋቂዎች ለስቃይና ለሞት የዳረጉ ወንጀለኞች ይገኙባቸዋል። አላግባብ የበለጸጉና ገንዘብን በመተማመን፥ ባለሥልጣኖችን የሚገዙና ሰዎችን በአካል የመጉዳትን እርምጃ የሚለማመዱ ወንጀለኞችም ይገኙባቸዋል።

እነዚህ ነገሮች በገሃድ፥ በአደባባይ፥ በሚዲያው ላይ ወለል ብለው እየታዩ፥ እየታወቁ፥ የተጎዱ ሰዎችና ተባባሪዎች የነበሩ ሰዎች ወጥተው እየተናገሩ ሳሉ ምንም እንዳላደረጉ ሁሉ ወንጌላውያንን አብያተ ክርስቲያናት ከሐሳውያን ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር አንድ የሚያደርግ ካውንስል መሥርቶ ማጣበቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አካሄድ አይደለምና ይህ ስሕተት እና ለኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና አደገኛ እርምጃ ነው።

መፍትሔ፤

እነዚህ ሐሰተኞች ከምንም ነገር በፊት ስሕተታቸውን እንዲያውቁ፥ እንዲጸጸቱ፥ እንዲናዘዙ፥ ንስሐ እንዲገቡ፥ የጎዷቸውን ሰዎች ይቅርታ እንዲጠይቁ፥ ለበደሏቸው እንዲክሱ፥ ያሳቷቸውን ሰዎች ማሳታቸውን እንዲያምኑ፥ እውነቱ የቱ መሆኑን ገልጠው ተናግረው ቀድሞ ያስተማሩትና ያለማመዱት የማሳት አካሄድ ስሕተት መሆኑን እንዲናገሩ እውነተኛ መመለስ እንዲሆንላቸው መደረግ አለበት። የቀድሞው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት (አሁን በካውንስሉ ውስጥ የተዋጠው) በአቅሙ ይህንን ለማድረግ ሙከራ አድርጎ ነበር። አሁን አብረው ተቀምጠዋልና እንደዚያ ያለ ነገር ማድረግ ዋዛ ባይሆንም፥ ያኔ በመጠኑም ቢሆን የማንቃት ሙከራ ተደርጎ ነበር። አሁንም ቢሆን መፍትሔው በማኅበር ተባብሮ፥ ተነባብሮ መቀመጥ ሳይሆን ስሕተትን አሳቾቹም ሳቾቹም እንዲያስተውሏት እና እንዲመለሱ መርዳት ነው።

2. ሁለተኛው ስሕተትና አደጋ የካውንስሉ ጅማሮው መንግሥታዊና ቤተ መንግሥታዊ መሆኑ ነው። በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሃይማኖት በ10 አንቀጾች ውስጥ ተጠቅሷል (መግቢያ፥3፥11፥21፥25፥27፥34፥38፥78፥ እና 90)፤ እና ሃይማኖት ተገቢ ስፍራ ያለው መሆኑ ይታያል።

ስሕተቱ፤

*መንግሥት ተሰባሰቡና ድምጻችሁ ይሰማል በሚል አስተያየት ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። ጣልቃ መግባት እንደሌለበት አንቀጽ 11፥1-3 ይደነግጋል።*

*መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።*

*መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።*

*መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።*

*አንቀጽ 25 የእኩልነት መብት*

*ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡* ይላል። ይህም የሃይማኖት መድልዎ አለመኖሩን ይጠቁማል።

ሰኔ 13፥ 2011 የተደረገው ይህንን ያፋልሳል። ቦታው ቤተ መንግሥት ነው፤ ጠሪው ጠቅላይ ሚኒስትር ነው፤ ተጠሪዎቹ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንሥቶ ከቤተ ክርስቲያን ጋር መልክ ያለው ምንም ግንኙነት እስከሌላቸው ሰዎች ድረስ ነው። ጥሪው በደብዳቤ የሆነ ይፋ ሳይሆን በስልክ ነው፤ ትእዛዙ ወይም ምክሩ አንድ ሁኑና ተሰባሰቡ ነው፤ ኮሚቴ የተመሠረተው እዚያው ነው፤ ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፤ ምክረ አሳብ አቅራቢው ኮሚቴ ሲሰየም ሰያሚው ጉባኤው ብቻ አልነበረም፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ነው።

‘የለም፤ የምክር አሳብ ብቻ ነው የሰነዘሩት፤ ኮሚቴው መመሥረቱ በኛ ጥያቄ ነው፤ ካውንስሉ የኛ አሳብ ነው።’ ሲባል ተደምጧል። መነሻው አሳብ ተበታትናችኋል፤ ተሰባሰቡና ጥያቄአችሁን አቅርቡ፥ መብታችሁንም አስከብሩ የሚል ነው። በእርግጥ በማኅበር መደራጀት አናሳ መብቶችን ሊያስከብር ይችላል። ሃይማኖት እና የሕሊና ነጻነት ግን በየትኛውም መስፈርት የተፈጥሮ ስጦታና የዜግነት መብት እንጂ አናሳ ችሮታ አይደለም።

ስሕተቱ ምንድን ነው? ሃይማኖቶችን በጣጥቆ ለተለያዩ ሃይማኖቶች የተለያዩ አዋጆችን ማወጅ። ሃይማኖቶችን ለያይቶ የተለያዩ አዋጆችን ማወጅ ሃይማኖቶችን በእኩል ዓይን ያለማየት ነው። የመንግሥት አድሎአዊነት ወይም መንግሥታዊ ሃይማኖት ወይም ሃይማኖታዊ መንግሥት ባሉበት የሚደረግ አካሄድ ነው። እንዲህ ያሉ መንግሥታት ወይም ሃይማኖቶች ባሉበት አንዱ ሃይማኖት ብሔራዊ ሆኖ ሌላው ወይም ሌሎቹ የበታችና አናሳ ይሆናሉ። ምዕመናንም ዋጋ ከፋዮች ይሆናሉ። እስልምና በተስፋፋባቸው ዘመናትና አገራት ይደረግ የነበረውና የሚደረገው የዲሚ ወይም ዚሚ አሠራር የዚህ አንድ ምሳሌ ነው። ለብዙ ክፍለ ዘመናት፥ በኢጣልያ የካቶሊክ፥ በእንግሊዝ የአንግሊካን፥ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ እምነቶች እንዲህ የባለ ልዩ ማዕረግ ባለ መብቶች ሆነው ኖረዋል።

ከዚህ በፊት በተናገርኳቸው ቪድዮዎች እንዳልኩት መንግሥት አንድ አድላዊና ወገንተኛ የሆነ ወይም ሁሉን በእኩል የሚያይ ትክክለኛ አዋጅ ሊያወጣ ይችላል። መንግሥት ሲቀየር ደግሞ የቀድሞ አዋጆችን በተረዳባቸው፥ በተገነዘበባቸው ትክክለኛ እይታ ወይ ሊያጸና ወይ ሊሽር ይችላል። ርዕዮተ ዓለሙ ከቀድሞው የተለየ ከሆነ ሥርዓተ መንግሥቱም አዲስ ስለሚሆን ሥርዓተ መንግሥቱ የቀደሙትን በሙሉ በጥቅሉ ይሽራቸዋል። ደርግ ከዐጼያዊው መንግሥት የተለየ ርዕዮት ተከትሏልና በሙሉ አፍርሶታል። ኢሕአዴግ ከደርግ የተለየ ነውና አፍርሶታል። ሃይማኖትን በተመለከተም ሁሉም የየራሳቸውን አሠራሮች በሕገ መንግሥቱ ውስጥ አስፍረዋል።

መንግሥት ማድረግ ያለበት ሃይማኖቶችን በየፊናው በማደራጀት ለየብቻ አዋጅ በማወጅ መያዝ ሳይሆን መሠረታዊውን የሃይማኖትና የእምነት ትርጉም አስቀምጦ ያንን ያሟላ በነጠላና በአጥቢያም ይሁን፥ በማኅበርና በቤተ እምነትም ይሁን፥ በማኅበሮች ማኅበርም ይሁን መሰባሰብ የራሳቸው የእምነት መጽሐፍና የእምነት አንቀጽ ጉዳይ ሆኖ፥ ለነሱ ተትቶ መንግሥት ግን እዚያ የውስጥ አሠራራቸው ውስጥ ጣቱንም ሳያስገባ አንዱም ሃይማኖት የበላይ ሳይሆንና እንዳይሆን፥ ሁሉም እንደ ዜጋ፥ እንደ ሃይማኖተኛ ጸጥና ዝግ ብለው የሚኖሩበትን የሚያመልኩበትን ሁኔታ ነው ማመቻቸት ያለበት። ለዚያም ነው በ1ጢሞ. 2፥1-2 *እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።* የተባልነው። ስለ ሰዎች ሁሉ፥ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንት ሁሉ *ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም* እንዲደረግ የተነገረን።

ጤናማውና የተደላደለው መሆንም የነበረበት መንግሥት መንግሥታዊውን ነገር ቢሠራ ነው። በሃይማኖት ስም የሚያጭበረብሩትን፥ ዜጎችን ለጉዳት የሚዳርጉትን በሕገ መንግሥቱ መሠረት ጣልቃ ይግባና ያግድ፥ ይያዝ፥ ለፍርድ ያቅርብ፥ ይቅጣ፤ ይገድብ፤ አንቀጽ 27፥5 ያንን ደንግጓል። እዝባር 5 የሚለው ይህንን ነው፤

*አንቀጽ 27 የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነጻነት*

*ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነጻነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡ ፡*

*በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡*

*ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነጻነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡*

*ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡*

*ሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜችን መሰረታዊ መብቶች፣ ነጻነቶች እና መንግስት ከሃይማኖት ነጻ መሆኑን ለማረጋረገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል፡፡*

ይላል። እስካሁን ስንቶች ተጎድተው፥ ስንቶች ተቀጥፈው፥ ኡ ኡ! እያልን ምን ተደረገ? ባሰባቸው እንጂ። ይህ መደረግ ያለበት ነገር ዝም ተብሎ፥ በሌላ በኩል መሪ ሰዎች ተሰብስበው፥ 'እናንተ ራሳችሁ ሕመምተኞች ናችሁ፤ ራሳችሁን ፈውሱ' ማለት ስላቅ ነው። ይብሱን ደግሞ ጎጂዎቹን ከጤናማዎቹ ጋር አጉሮ ተሰባሰቡና ኑና እንስማችሁ ማለት ሌላ ስላቅ ነው።

ዛሬ ሜይ 7፥ 2020 የተነበበው ዜና የሚንስትሮች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ሕጋዊ ዕውቅና ለመስጠት የወጣውን ረቂቅ አዋጅ እንደተቀበለና ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጁን ለሕዝብ ተወካዮች እንደመራ ነው። መንግሥት የተበጣጠቁ ለየሃይማኖቱ የሚሆኑ አዋጆችን ሳይሆን ሁሉንም በአንድ ዓይን የሚያይ አዋጅ ነው ማወጅ ያለበት። የዚህ ለተለያዩ ሃይማኖቶች የተለያዩ አዋጆችና ድንጋጌዎች ማቅረብ ችግሩ አንድ ቀን አንዱ የበላይ የሆነ ቀን የራሱን አስቀርቶ ሌሎቹን አዋጆች መሻር መቻሉ ነው። ስሕተቱና ችግሩ ይህ ከሆነ መፍትሔውስ?

መፍትሔው፤

መፍትሔው መንግሥት ሃይማኖቶችን ለአዋጅ በሚመች መልክ የሚያሰባስብበት ሳይሆን በእኩል ዓይን የሚያይበት ሕገ መንግሥት እና አዋጅ ሊኖረው ይገባል። ከሕግ በታች ሁሉም ዜጋ ሳይሳቀቅ፥ አንዱ ከሌላው እኩል መሆኑ የሚታወቅበትና የሚረጋገጥበት፥ አንዱ ሕጋዊ ሃይማኖት፥ ሌላው ሕጋዊ ማኅበር ሳይሆን ሁሉም፥ ማንም ከማንም ሳይለይ በሕግ ዓይን ፊት እኩል የሚሆኑበት፥ መብታቸው እኩል፥ ግዴታቸው እኩል የሚሆኑበት፥ በአንቀጽ 27/5 መሠረት ሊገደቡ የሚችሉባቸው ማኅበረ ሰቡንና የዜጋውን መሠረታዊ መብቶች የማይጎዱበት ነገር የሚታይበት፥ ሌሎች ሃይማኖታዊ ጥቅሞችም፥ (ለምሳሌ፥ ከቀረጥ ነጻ መሆን፥ ሕጋዊ ማጋባት፥ ወዘተ፥) በንጹሕና ዘላቂነትና ቋሚነት ባለው መልኩ መደንገግ ነው።

ኢትዮጵያ በጣም ሃይማኖታዊ አገር መሆኗ ታሳቢ ሆኖ፥ የአገሪቱ 97% በላይ ሕዝብ ሃይማኖታዊ መሆኑ ታሳቢ ሆኖ ይህ አዋጅ ሁሉን አቀፍ እንደመሆኑ መጠን ልዩ ትኩረትም ሊሰጠው የተገባ መሆኑ መጤን አለበት።

ስጀምር የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አመሠራረት በሁለት ትልልቅ ምክንያቶች ስሕተት እና ለኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና አደገኛ እርምጃ ነው። ብያለሁ። ችግሮቹን ወይም ስሕተቶቹን ብቻ ሳይሆን መፍትሔዎቹንም ጭምር አካፍያለሁ።

ይህ የቆንስላው ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን ከተጀመረበት ከሰኔ ፲፫ 2011 (ጁን 20፥ 2019) ጀምሮ ነው ልጽፍና ልናገርበት የጀመርኩት። በሌላ አንድ ዝግጅት ከመጀመሪያው ጀምሮ፥ ከጅምሩ አንሥቶ ያቀረብኳቸውን አሳቦች በማጋራት ይህንን ስጋቴን በማካፈል እደመድማለሁ። ልብ እንበል፤ ሐሰት አንድ ከሚያደርገን፥ እውነት ቢለየን ይሻላል። በሐሰት አንድ ላይ ከምንሆን፥ ከምንሸነጋገል፥ እውነትን ተነጋግረን በእውነት ብንለያይ ይሻላል።

## የተቋቋመበት አዋጅ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| ፳፮ኛ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፱<br>አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 26th Year No.59<br>ADDIS ABABA 4th July, 2020 |

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፰/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስልን እና አባላቱን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ ........................................ገጽ ፲፪ሺ፮፻፲፮

**Content**

Proclamation No. 1208/2020

A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Council of Gospel Believers' Churches and Members..........................................Page 12,616

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፰/፪ሺ፲፪**

**የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እና አባላቱን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፳፯(፪) በዜጎች የሃይማኖት አስተዳደር ተቋማት የማቋቋም መብት በመጠቀም የኢትዮጵያ የወንጌላዊያን አብያተ-ክርስቲያናትና የአብያተክርስቲያናት ህብረቶች ያቋቋሙትን ሀገር አቀፍ ተቋም የህግ ሰውነት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ-ክርስቲያናት ካውንስል በርካታ የህዝብ ቁጥር ያለውን የወንጌል አማኞች ማህበረሰብ በመንግስት ዘንድ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል ተቋም ስለሆነ ህጋዊ ሰውነትና እውቅና በአዋጅ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No 1208/2020**

**A PROCLAMATION TO PROVIDE LEGAL PERSONALITY FOR ETHIOPIAN COUNCIL OF GOSPEL BELIEVERS' CHURCHES AND MEMBERS**

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality of the national institution established by Ethiopian Evangelical Churches and Evangelical Churches Unions in accordance with citizens' rights to establish religious administration institutions based on Article 27(2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality to Council of Ethiopian Evangelical Churches that represents large number of Evangelical Christian community in relation to the government as well as international level;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እና አባላቱን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፰/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "ሚኒስትሪዎች" ማለት የቤተክርስቲያን አጋዥ ድርጅት ማለት ነው፤

2/ "አባላት" ማለት የካውንስሉን መስራቾችና በቀጣይም በካውንስሉ ተመዝግበው አባል የሚሆኑ ቤተክርስቲያናት፣ ሚኒስትሪዎችና የቤተክርስቲያን ህብረቶች ናቸው፡፡

**፫. ህጋዊ ሰውነት**

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስልና አባላቱ በስሩ የተቋቋሙና የሚቋቋሙ የሃይማኖት ተቋማት፣ ድርጅቶችና ማህበራት የተለየ ምዝገባ ሳያስፈልጋቸው በዚህ አዋጅ መሰረት የህግ ሰውነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

**፬. ስያሜ**

ካውንስሉ በሙሉ ስሙ "የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለአርማ ፣ ለማህተምና ለቲተሮች አጠቃቀም አመቺነት እንደአስፈላጊነቱ በአጭር ስም ሊጠራ ይችላል፡፡

**፭. ስለበጀት**

፩/ የካውንስሉ እና የአባላቱ በጀት ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በሚገኙ ስጦታዎች፣ ከሃይማኖት ተቋማት እና ከህብረተሰቡ በሚሰበሰቡ መዋጮዎች፣ በሃይማኖቱ ከተፈቀዱ የአገልግሎት ክፍያዎች እና እርዳታዎች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Council of Gospel Believers' Churches and Members No. 1208/2020".

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "ministries" means Organizations which support church ;

2/ "members" means churches, ministries and church unions which are founders of the council and others registered after.

**3. Legal Personality**

In accordance with this proclamation Ethiopian Council of Gospel Believers' Churches and members, religious institutions, organizations and societies established and to be established under it shall have legal personality without requirements of especial registration.

**4. Heading**

The Council may be cited with its full name "Ethiopian Council of Gospel Believers' Churches" and may also be called by abbreviation for convenience of emblem or stamp as may be necessary.

**5. Budget**

1/ The budget of the Council shall be covered by gifts obtained from in and out of the country, contributions collected from religious institutions and Gospel Believers community; service fees and aids allowed by the religion.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች በሀገሪቱ ተፈፃሚነት ያላቸውን የታክስ እና የንግድ አስተዳደር ህጎች መሰረት አድርጎ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ እና የልማት ስራዎችን ይሰራል፡፡

፫/ ካውንስሉ እና አባላቱ ግልፅ የፋይናንስና የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

፮. <u>የስራ ቋንቋ</u>

የካውንስሉ የስራ ቋንቋ የፌደራልና የየክልሉ የሥራ ቋንቋዎችን መሰረት አድርጎ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡

፯. <u>መተዳደሪያ ደንብ ስለማውጣት</u>

ካውንስሉ የውስጥ አሰራርና አደረጃጀቱን ለመወሰን መተዳደሪያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል

፰. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እና አባላቱ ከዚህ አዋጅ በፊትም ሆነ በኋላ ያፈሯቸውና የሚያፈሩዋቸው ንብረቶች፣ መብትና ግዴታዎቻቸው በሙሉ እንደተጠበቁ ይቆያሉ፡፡

፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article the Council can engage in additional income generating and development activities pursuant to other tax and commercial administration laws of the country.

3/ The Council and its members shall establish transparent finance and money administration system.

6. <u>Working Language</u>

The working language of the Council shall be determined by the memorandum based on the Federal and Regional working languages.

7. <u>Enactment of Law</u>

The Council may issue Regulation for its internal activity and organization.

8. <u>Transitory Provisions</u>

All properties, duties and responsibilities obtained by the Ethiopian Council of Gospel Believers' Churches and members before or after the effective date of this Proclamation shall be maintained.

9. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Ababa, on this 4th day of July, 2020.**

**SAHELWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

በዚህ ሰሞን አሳየኸኝ ለገሠ፥ ፍጹማን ግርማ፥ እና ሳሚ ቱራ የካውንስሉ ግራጫ ዞን በሚል ርእስ ተቀርጾ የተላለፈ የጋራ ውይይት አካሂደው ብዙዎቻችን አደመጥነው አጋራነው። እኔም አጋርቼዋለሁ።

ክፍል አንድ

https://www.youtube.com/watch?v=Xh6zZeyDNnc

እና ክፍል ሁለት

https://www.youtube.com/watch?v=MRxtuXuUHgI

ቆንስላው በተመሠረተ በዓመቱ ሰሞን፥ ባዕድ፤ ቅይጡ ወንጌል የተሰኘው ዶክሜንተሪ ቪድዮ ተለቀቀ። በቆንስላው የታቀፉ ብዙ ሐሰተኞች የተገለጡበት ሥራ ነው።

ሊንኩ፤ https://www.youtube.com/watch?v=Mm-AHXeXrcc ነው።

June 21, 2020

አሁን ቆንስላው ከተመሠረተ ወራት ተቆጠሩ። ከተጸነሰ ደግሞ አንድ ዓመት ሆነው። እኔም፥ ‘ጥንሳመት ዘቆንስላ’ በማለት ቪድዮ አጋራሁ። በዚህ ቪድዮ ካውንስሉን ለምን ቆንስላ እንደምልም ግልጽ አድርጌአለሁ። በፌስቡክ ገጼ የቪድዮው አጭር ማስተዋወቂያ ይህ ነበር፤

ካውንስል ወይስ ቆንስላ?

. . . ትናንት ቆንስላውን የወለደው ወይም ያስወለደው አዋላጅ ኮሚቴ 1ኛ ዓመቱ ነበር። ቆንስላው ሕጋዊ ሰውነቱን ማግኘቱ የተከበረውም በትናንቱ ዕለት ነው፤ ልክ በትክክል፥ በዓመቱ መከበሩ ድንገተኛ ግጥምጥሞሽ አይመስለኝም።

ይህ በዚህ ያካፈልኩት ልክ የትናንትና ዓመት የ400ዎቹ ተጋባዦች ስብሰባ ተጠርቶ የ15ቶቹ ኮሚቴ በተዋቀረ ቀን የጻፍኩት ነው። ገና በመጀመሪያው ቀን! ገና አሐዱ በተባለ ቀን።

ቆንስላው፥ በነገራችን ላይ ካውንስሉን ለምን ቆንስላ እንደምለው በተደጋጋሚ ተጠይቄአለሁ፤ መልሴንም በቪድዮው መጨረሻ ላይ በግልጽ አስቀምጫለሁ። እና፥ ቆንስላው በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ላይ ጥቁር ነጥብ ነው።

ዘላለም ነኝ።

የቪድዮው ሊንክ፤ https://www.youtube.com/watch?v=h66p81KjsjA

የቪድዮው ቃል በጽሑፍ የተለወጠው፤



ቤተ ክርስቲያን በምድር መንግሥት ላይ እንድትሠለጥን ቃሉ አያስተምርም። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የምትገኝና እስክትነጠቅ ድረስ የሰማዩ መንግሥት አስተዋዋቂም፥ ማስተዋወቂያ መድረክም ናት። ምድራዊ መንግሥት ደግሞ በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የአደራ ሥልጣን በዜጎች ላይ መለማመድ አለበት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።

ጤናይስጥልኝ ዘላለም ነኝ። ዛሬም ስለ ቆንስላው የምናገረው አለኝ። ዛሬ ቆንስላውን የወለደው ኮሚቴ ወይም የቆንስላው እናት የተመሰረተበት 1ኛ ዓመት ነው።

ይህ በመጀመሪያው የ400ው ስብሰባ ቀን (ለምን 400 እንደተደረጉም አልገባኝም።) ብቻ በመጀመሪያው ስብሰባ ቀን - ሰኔ 13፥ 2011 (June 20, 2019) ቆንስላው የተረገዘበት ቀን ማለት ነው የለጠፍኩት ነው። ከስዕሉ ጋር የጻፍኳትን አንዷት አንቀጽ ላንብባት።

ቤተ ክርስቲያን በምድር መንግሥት ላይ እንድትሠለጥን ቃሉ አያስተምርም። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የምትገኝና እስክትነጠቅ ድረስ የሰማዩ መንግሥት አስተዋዋቂም፥ ማስተዋወቂያ መድረክም ናት። ምድራዊ መንግሥት ደግሞ በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የአደራ ሥልጣን በዜጎች ላይ መለማመድ አለበት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።

ስለ ቆንስላው ወይም ካውንስሉ ወይም ካውንስሉን ስለፈጠረው አዋላጅ ኮሚቴ መጻፍ የጀመርኩት፥ ወይም መንግሥታዊ ጣልቃ መግባትን በተመለከተ መጻፍ የጀመርኩት ቆንስላው ሲመሠረት አለመሆኑን፥ ገና ሲጸነስም መሆኑን ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። ገና ባለ 15 ሰዎቹ ኮሚቴ በቤተ መንግሥቱ በተመሠረተ ቀን፥ በመጀመሪያው ቀን፥ በቀን አንድ፥ አሐዱ ሲባል ነው ይህን የጻፍኩት። ካውንስሉን ለምን ቆንስላ እንደምለው ኋላ መጨረሻ ላይ እናገራለሁ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ባለፈው ወር ባቀረብኩት ቪድዮ እንዳልኩት ሜይ 7፥ 2020 በተነበበው ዜና የሚንስትሮች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ሕጋዊ ዕውቅና ለመስጠት የወጣውን ረቂቅ አዋጅ እንደተቀበለና ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጁን ለሕዝብ ተወካዮች እንደመራ ነው። እዚያ ያልኩት መንግሥት የተበጣጠቁ ለየሃይማኖቱ የሚሆኑ አዋጆችን ሳይሆን ሁሉንም በአንድ ዓይን የሚያይ አዋጅ ነው ማወጅ ያለበት። ይህ ነገር አድሮ ችግር ሊኖረው ይችላል፤ የዚህ ለተለያዩ ሃይማኖቶች የተለያዩ አዋጆችና ድንጋጌዎች ማቅረብ ችግሩ አንድ ቀን አንዱ የበላይ የሆነ ቀን የራሱን አስቀርቶ ሌሎቹን አዋጆች መሻር መቻሉ ነው። በማለት መፍትሔ የምላቸውን አሳቦች አካፍያለሁ። 22 ወይም 23 ያህል ሚሊየን ቁጥር የአገሪቱ ሕዝብ ሩብ ማለት ነው። ቀላል ቁጥር አይደለም። ያንን የሚያህል ሕዝብ የልብ ትርታ መስማት ወይም ነርቭ መንካት ቀላል አይደለም።

ባለፈው ሳምንት ሰኔ 4 (ጁን 11) ካውንስሉ ሕጋዊ አካል ማግኘቱ ተነገረ። ይህ የሚጠበቅም ነበር። ዛሬ ደግሞ በሼራተን ሆቴል የሕጋዊ እውቅናው በዓል ተከብሮ ውሏል። አዋጁ መብት ያስጠብቅ ይሆናል። ግን መብት ያስጠብቅ ይሆናል ሲባል መብቱ አልነበረም ማለት ነው? ወይስ አዋጁ ጥቅም ያስጠብቅ ይሆናል ነው የሚባለው? ወይስ አዋጁ አሠራሮችን ያሳልጣል ነው የሚባለው? አሁንም አስምሬ ለመናገር የምፈልገው ነጥብ በሰለጠኑት እና ነጻና ዲሞክራሲያዊ በሆኑት አገሮች እንደሚደረገው፥ መንግሥት የተበጣጠቁ ለየሃይማኖቱ የሚሆኑ የመብት አዋጆችን ሳይሆን ሁሉንም በአንድ ዓይን የሚያይ አዋጅ ነው ማወጅ ያለበት። ለተለያዩ ለመንግሥት የሚመቹ ፖሊሲዎችን ማርቀቅና ማወጅ ከሆነ ያ የመንግሥት የውስጥ ሥራና አሠራር ነው። መብት ግን መብት ነው።

ቀጥሎ ለካቶሊክ አዋጅ ሊታወጅ ነው ማለት ነው? ቀጥሎስ? ለይሆዋ ምስክሮች እና ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና ለሞርሞኖችና ለሌሎቹም ለየብቻ የመብት አዋጅ ሊታወጅ ነው? ለኢሬቻስ? ለኦርቶዶክስ ተሐድሶስ? ጠንቋዮች በማኅበር ተደራጅተው ሃይማኖት ሆነው ቢመጡስ? ለየብቻ የመብት አዋጅ ይታወጃል? የለም፤ የሃይማኖት፥ የእምነት፥ የሕሊና ነጻነት አዋጅ ማንንም ከማንም በማይለይ መልኩ ነው መቅረብ ያለበት። የቀድሞ መንግሥታት ከተሳሳቱ፥ ስሕተቱ ይስተካከላል እንጂ፥ ያ በድንጋይ ላይ የተቀረጸ፥ የማይሻሻል፥ የማይገሠስ ሕግ ተደርጎ ሌላ አይቀረጽም። ይብሱን በስመ ወንጌላዊ ሁሉን አግበስብሶ አንድ ጎተራ ውስጥ መክተት ከመንግሥት ግፊት ሲመጣ ትክክልና ጤናማ አይሆንም።

አንዳንድ ሰዎች ኅብረት አለማድረግን የጥላቻ ብዛት እና የፍቅር እጦት አድርገው ያዩታል። አይደለም። ፍቅር እኮ፥ *ስለ እውነት ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመጻ ደስ አይለውም* ነው የተባለው፤ ቆሮ. 13፥6። ፍቅር ከእውነት ጋር ተባባሪ ናት። ከእውነት ጋር መተባበር ደግሞ ከሐሰት ጋር አለመተባበር ነው። ፍቅር አሳማሚ ነገርንም ትናገራለች። ፍቅር እውነትን ትናገራለች። ኤፌ. 4፥15 እውነትን በፍቅር እየያዝን ነው እኮ የሚለው። እውነትና ፍቅር የተያያዙ ናቸው። ፍቅር እውነትን ትናገራለች እንጂ ሽንገላን አትናገርም። ከስሕተት ጋር ኅብረት አለማድረግ የጥላቻ ብዛት እና የፍቅር እጦት አይደለም። እንወቅ፤ አይደለም።

በክርስቲያኖች ጤናማ ፖለቲካዊ ተሣትፎና ሰልፈኝነት አምናለሁ። ቤተ ክርስቲያን ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን ፖለቲከኛ መሆን የለባትም። ክርስቲያኖች ቢፈልጉ መሆን ይችላሉ፤ ቢሆኑም ይጠቅማሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን ፖለቲከኛ መሆን የለባትም። መንግሥትም እንደ መንግሥት ሃይማኖተኛ መሆን የለበትም። ሃይማኖተኛ መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ሃይማኖት መኖር የለበትም። ጥሩው ነገር፥ ሕገ መንግሥቱም ይህንን ይቀበላል። አንቀጽ 11፥1-3 ይህን ይደነግጋል።

*መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።*

*መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።*

*መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።*

እዝባር ሁለት ላይ መንግሥታዊ ሃይማኖት እንደማይኖር እንደተጻፈው ሁሉ፥ ባይጻፍም፥ ሃይማኖታዊ መንግሥትም አለመኖሩ ታሳቢ የሆነ ይመስለኛል። ሃይማኖታዊ መንግሥት ማለት ራሱ ሃይማኖቱ የፈጠረውና ለሃይማኖቱ ተገዢ የሆነ መንግሥት ማለት ነው።

ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይህንን የመንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጣልቃ መግባት ስጽፍበትና ሳወግዝ ቆይቻለሁ። በዚህ ጉዳይ አንዳንዶች አጥብቀው ነቅፈውኛል፤ አንዳንዶች የግል በሆነ ጥላቻም ጠልተውኛል። የኅብረት ጠር አድርገው አይተውኛል። ልክ ነው፤ ጤናማ ያልሆነ ኅብረት፥ ስንዴና እንክርዳድ አብረው የሚከኩበት ኅብረት፥ የሚዝዘርሩበት ሳይሆን የሚፍፈጭጩበት ኅብረት ለማንም መኮስኮስ አለበት። ለዚህ ነው ከጅምሩ ጤናማ አይደለም ብዬ መጻፍ የጀመርኩት።

ይህን የመጀመሪያውን አጭር ጽሑፍ፥ በዚያው ቀን ስለጥፍ የተሰነዘሩ አሳቦችና አስተያየቶች ነበሩ። አንዳንዶቹ ተስፋ የመቁረጥና የማስቆረጥ፥ አንዳንዶቹ ተስፋ የመሰነቅና የማስጨበጥ አሳቦች ናቸው። ከነዚያ አስተያየቶች የአንድ የሁለቱንና አስተማሪ የሚሆኑትን ብቻ በትንሹ አነሳለሁ። ለአሳቦቹ የሰጧኋቸው መልሶችም እዚያ አስተያየቶቹ በተሰጡበት የመለስኳቸው ናቸው በተለጠፈበት ቀን ማየት ይቻላል። እዚህ የምጠቅሰው ጥቂቱን ብቻ ስለሆነ ጠቅላላውን አስተያየቶች በስፍራው ማየት ይቻላል። ቀኑም ቆንስላው የተረገዘበት ቀን ነው።

'ወዳጄ ምንም መመለስ አይጠበቅብህም ምንም ስለማይለወጥ።' ብሏል ከመጀመሪያ ጠያቂዎች አንዱ። 'ለመመለስ ሳይሆን ጮክ ብዬ ማሰቤ ነው።' ነበር ያልኩት። በእርግጥም ጮክ ብዬ ማሰቤ ነበር፤ እንጂ ጥያቄም አልተጠየቀም፤ መልስም አልመለስኩም። ምላሹ እንደ መልስ ካልተቆጠረ በቀር። አንዳንዶች ይህንን መንግሥት ቤቱ ስለተበላሸ ከእግዚአብሔር ለቅጣት የተላከ በትር፥ ወይም ቤቱን ለማጽዳትና ለማስተካከል የተላከ መጥረጊያ አድርገው ወስደውታል። ለኔ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመግባቱ ጠቅላላው አካሄድ ጤናማ አይደለም፤ መንግሥት አስቀድሞ ማድረግ ያለበትን የራሱን የቤት ሥራውን ሳይሠራ ሌላ ነገር እያደረገ ነው ባይ ነኝ።

ምድራዊ መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም ስላልኩት አሳብ ገማልያ ዘዲማ ሲጠይቅ እንዲህ ብሏል፤ 'መሰልጠን ምንድን ነው? በምን ይገለጣል? አንድ መንግስት ቤ/ክ ላይ ሰለጠነ ለማለት የሚቻለው ምን ምን ሲያደርግ ነው? እንድንግባባ መጀመሪያ እሱን በቃሉ አስደግፈህ ማብራራት አለብህ።' ብሏል።

ለGemalia Z Dima መሰልጠን ምን እንደሆነ የመለስኩለት እንዲህ ብዬ ነው፤ መሰልጠን፥ 'ባለ ሥልጣን መሆን፥ ሥልጣንን ማሳየት፥ የበላይ መሆን፥ መግዛት፥ መቆጣጠር ነው። ከቃሉ ላሳይህ የማልችለው [ይህን ያልኩት ከቃሉ አሳየኝ ስላለ ነው] በቃሉ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በምድራዊ መንግሥት ላይ ስትሠለጥን ስላልታየች እና ምድራዊ መንግሥትም ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድድ እንጂ ሲሠለጥንባት ስላልታየ ነው። ያኔ ያልነበረው ዛሬም ያ መሆን የለበትም ነው ነጥቤ። ቤተ ክርስቲያን እና መሪዎቿ በመንግሥታዊ መዘውር ውስጥ ገብተው መሽከርከር የለባቸውም። መንግሥት ቀድሞውኑ ሃይማኖቶችን የተመለከተ ያልወገነ ሕግ ደንግጓል፤ ያ በቂነት

አልጎደለውም።' ነበር ያልኩት። አንዱ በሌላው ላይ አይሰልጥን ስል ያንን ማለቴ ነው። ባለ ሥልጣን አይሁን፤ አለቃና አዛዥ አይሁን፤ አስተያየትም፥ አሳብም አስመስሎ፥ በተለይ መንግሥት፥ ቀጭን ትእዛዝ ሰጪ አይሁን።

ሌላ ሰፋ ያለ ምልልስ ያደረግሁት ዱም ዱም ከተባለ/ከተባለች አስተያየተኛ ጋር ነበር። ዱም ዱም ያንን ጽሑፌን ተገትሮ፥ ተወጥሮ እንዲያዝ የሞከረ ሰው ነው፤ ወይም ሴት ናት። ዱም ዱም ወንድ ይሁን ሴት ትሁን አላውቅም። አንዳንድ ፌስቡከኞች ስምና መልክና ፆታ ደብቀው ነው የሚጽፉትና፥ ይህችኛዋ ሴት ስለመሰለችኝ በሴት ነው የለመለስኩላት። የመጀመሪያው ጥያቄዋ ይህ ነው፤

Dum Dum 1) ክርስትያን በመንግስት ጉዳይ የሚገባበት አግባብ ካለ እና ሲገባም በመግስት ላይ ሰለጠነ ካላስባለው መንግስትስ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ የሚገባበት አግባብ እንዴት ሊኖረው አይችልም? ሲገባስ በቤተክርስትያን ላይ ሰለጠነ እንዴት ያስብላል?

2) በላይኛው ከንፈርህ ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ያለውን ጤነኛ ተሳትፎ እደግፋለሁ እያልክ በታችኛው ከንፈርህ ደግሞ በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ የመንግስት መሪ ለመሆን የበቃውን ወንድምህን በጎ ተግሳፅ እንደ ክርስትያን ወንድም መቀበል ሲገባህ እንደ አንድ አላማኝ አምባገነን ቆጥረህ "ሰለጠነብኝ?" እንዴት ትለዋለህ? ይሄ እርስ በርሱ የሚጣረስ አይሆንም ወይ? ደግሞስ በእኛ ላይ ገዢ ማን አደረገህ ብሎ ሙሴን እንደተቃወመው አመፀኛ ተራ ምቀኝነት አያስመስልህም ወይ?

3) ምናልባት እነዛ የምትጠላቸውና በነጋ በጠባ ቁጥር እኝኝኝ የምትልባቸው ፓስተሮች "ጤነኛ" ከምትላቸው ጋር ባንድ አዳራሽ መታጨቃቸው አንገብግቦህ ነው? እንደዛ ከሆነ እርምህን አውጣ - ጠቅላዩ ብቻ ሳይሆንም መላው አለም በአንድ (የጥላቻና የስግብግብነት) ጉድጓድ ተቀርቅራችሁ ነው የሚያያችሁ። አለም የክርስቶስ ደቀመዛሙርት የሆኑትን የምታውቃቸው በፍቅራቸው ብቻ ነው። አንተና መሰል የክርስትና ጠባቆች (ጠባቂዎች ማለቴ አይደለም) ያለመታከት በምትዘሩት ጥላቻና መለያየት በአለም ፊት ቤተክርስትያን መሳለቂያ እንድትሆን ግማሽ በግማሽ አበርካቾች ናችሁ። በስህተት ትምህርት የተታለሉትን በፍቅርና በፀሎት እንዲሁም በእውነተኛ ክርስትያናዊ ኑሮና ባህርይ የሚመልሱና የሚያቀኑ ሳይሆን በርቱዓዊነት (orthodoxy) የደነዘዙና በፌዝ በስላቅና በጥላቻ እውነተኛውን አስተምህሮ ለማስጠበቅ የሚጋጋጡ ፍቅር-አልባ ተከታዮችን አፍርታችኃልና!!!

የሚል ጥያቄና አሳብ አቅርባ ነበር። ሦስተኛው ጥያቄ የለበትም፤ እርምህን አውጣ፤ አፍህን ዝጋ ነው። ለዱም ዱም መልሴን ሰጥቼ ነበር።

Dum Dum ለሦስቱም ነጥቦችሽ አጫጭር ምላሽ። ሁለት ጥሩ ነጥቦች አንሥተሻልና ለሁለቱም አጨብጭቤልሻለሁ።

1) መንግሥት ሕገ መንግሥት አለው። በዚያ ውስጥ ሃይማኖቶችን በተመለከተ ያወጣው አንቀጽ አለ። በምን ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዳለበት የሚናገር ግልጽ ንዑስ

ክፍልም አለ። በዚያ መሠረት መተግበሩ አግባብ ነው እስማማለሁ። ተግባራዊ ያላደረገባቸው ነገሮች መኖራቸውም ሳይካድ ማለት ነው። ለምሳሌ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ከአንቀጽ ፳፯ ማለቴ ነው) መኖሩ የተረሳ ይመስላል። ሰው በሁለንተናው እየተጎዳና እየሞተ ዝም ተብሏልና።

ክርስቲያን በመንግሥት ጉዳይ መግባትንና ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ጉዳይ መግባትን ተመሳሳይ ያደረገው ያንቺ ጽሑፍ ነው የኔ አስተያየት አይደለም። የኔ ጽሑፍ እና አመለካከት የግለ ሰብን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያሸበርቃል። ክርስቲያንና ፖለቲካ በሚለው ቪድዮ ያልኩት ያንን ነው፤ በስፋት። ቤተ ክርስቲያን ግን ይህንን ያደረገችበትን ክፍል ከቃሉ ማሳየት ብትችዪ መልካም ነበር። አትችዪም። ስለዚህ ስሑት ነሽ።

መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጣልቃ አይገባም እና አይሠለጥንም የተለያዩ ናቸው። ሕገ መንግሥቱ በተደነገገለት መስመር የሚገባበት ሁኔታ በግልጽ ተጽፏል። ሲሆን አላየንም እንጂ፤ እስካሁን።

2) 'በላይኛው ከንፈርህ ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ያለውን ጤነኛ ተሳትፎ እደግፋለሁ እያልክ በታችኛው ከንፈርህ ደግሞ . . . ተራ ምቀኝነት አያስመስልህም ወይ? ያልሽውን አንቺ አልሽ። ጠቅላዩ አምባ ገነን ከቶም አይደለም፤ እስካሁን የሄደበትን እልህ ጨራሽ ትእግሥተኛ አካሄድ በማድነቅ እከታተለዋለሁ። አሁንም። ይህ ጥያቄ መሳይ ዝቅተኛ አስተያየት ስለሆነ ከዚህ ያለፈ መልስ አያሻውም።

3) 'እነዛ የምትጠላቸውና በነጋ በጠባ ቁጥር እኝኝኝ የምትልባቸው ፓስተሮች "ጤነኛ" ከምትላቸው ጋር ባንድ አዳራሽ መታጨቃቸው አንገብግቦህ ነው? ላልሽው፥ ስሕተት አንድ፥ እኔ የምጠላው ሰው የለኝም። የምጠላቸው እንደ ቃሉ ያልሆኑ የስሕተት ትምህርቶች እና ልምምዶች አሉ። እነዚያን መፋለሜ እውነት ነው፤ ይህ ደግሞ ጌታ እስካኖረኝ ገና ይቀጥላል። ይህ እኝኝኝኝ ማለት የሚመስላቸው መኖራቸውን ከኔ ይልቅ አንቺ ታውቂዋለሽ፤ አንዷ ስለሆንሽ።

ስሕተት ሁለት፥ ይህ ጉዳይ ምንም የሚያንገበግብ ጉዳይ አይደለም። ሌሎች የሚያንገበግቡ ጉዳዮች አሉ። ለማወቅ ከወደድሽ ጠይቂኝ።

ስሕተት ሦስት፥ 'አንተና መሰል የክርስትና ጠባቆች (ጠባቂዎች ማለቴ አይደለም) ያለመታከት በምትዘሩት ጥላቻና መለያየት በአለም ፊት ቤተክርስትያን መሳለቂያ እንድትሆን ግማሽ በግማሽ አበርካቾች ናችሁ።' ያልሽው ውሸት መሆኑን ነፍስያሽ ታውቀዋለች። ስሕተትን መግለጥ መሳለቂያ ማድረጉ እውነት ነው። እነዚህ ሰዎች እኮ ቀድሞውኑ ሐሰተኞች ባይሆኑ ኖሮ ሐሰታቸውን አንገልጥም ነበር። መግለጣችን ይበልጥ አደባባይ አውጥቶ እንዳሰጣቸው እውነት ነው። ግን እንደ ምዕራቡ ዓለም ጋዜጠኞች ሳያወጧቸው እኛው 'ጠባቆቹ' በቃሉ እየመዘንን ብናወጣቸው እንደ መባረክ ብትቆጥሪው ይቻል ነበር። መቼም አልታደልሽም። በእውነቱ እኛም

አልታደልንም። መግለጡ ግን ይቀጥላል። ክርስቶስ እስኪመጣ። ምክንያቱም ይበዛሉ ነው የተባልነው።

ስሕተት አራት፥ 'የምትዘሩት ጥላቻና መለያየት' ያልሽው ሰነፍ Ecumenical sympathizer (የጅምላ የደቦ አዛኝ አንጓች) አድርጎሻል። ሐሰትን መግለጥና እውነትን ማሳየት እንደሚለያይ (ልዩነትን እንደሚፈጥር) የታመነ ነው። ንጽሕና (purity) ተሠውቶ ዕድር (unity) ከኖረ የለበጣ ነው።

ስሕተት አምስት፥ 'በስህተት ትምህርት የተታለሉትን . . . የሚመልሱና የሚያቀኑ ሳይሆን . . . በፌዝ በስላቅና በጥላቻ እውነተኛውን አስተምህሮ ለማስጠበቅ የሚጋጋጡ ፍቅር-አልባ ተከታዮችን አፍርታችኃልና!' ያልሽው ጭፍን ክስ ነው። በአንድ ወገን የሳቱ ሰዎች መኖራቸውን አምነሽ እንዲመለሱ ትናፍቂያለሽ። በሌላ በኩል ሊመልሱ የሚተጉትን 'እኝኝኝ የምትልባቸው ፓስተሮች "ጤነኛ" ከምትላቸው ጋር ባንድ አዳራሽ መታጨቃቸው' ያልሽው ማንን እውነተኛ ማንን ሐሰተኛ ማድረግሽን ስለሚገልጥ ጎራ ለይተሽ የክስ ፋይልሽን ማውለብለብሽን ያሳያል። ለዚህ ነው ጭፍን ያልኩት። ዓይን ኖሮ አለማየት አለመታደል ነው።

ይህ ለዱም ዱም የሰጠሁት መልሴ ነበር። ዱም ዱም ከዚያ በኋላም ጽፉ ነበር።

<u>Dum Dum</u> እንዴ ፅሁፉን የፃፍከው (ወይም ከገዛ ፅሁፍህ የጠቀስከው) አብይ ከክርስቲያን መሪዎቹ ጋር ባደረገው ውይይት አውድ መስሎኝ? ምድራዊ መንግስት በቤተክርስቲያን ላይ አይሰለጥንም ....ቤተክርስቲያንን ተውአት ስትል አብይ በቤተክርስትያን ላይ እየሰለጠነብን ነው ሊተዋት ይገባል እንዳልክ ተረድቼህ ነው። በስህተት ተረድቼህ ከሆነ ይቅርታ!!!

ብላ ነበር። መልሴ ይህ ነበር። Dum Dum በእርግጥ በዚያ ዐውድ እንጂ ነው! አሁንም ነጥቤ እዚያው ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድር ትኑር እንጂ ምድራዊት አይደለችም። ከመንግሥት ጋር የመዋሸምም፥ በመንግሥት ላይ የመሠልጠንም የሐኪም ትእዛዝ አልተጻፈላትም። ቃሉ አያስተምርም። እርሷ ጌታዋ መጥቶ እስኪወስዳት ድረስ ራሷን ከእድፍ የምትጠብቅ የሰማዩ መንግሥት አንጻባራቂና አስተዋዋቂ ናት።

ምድራዊ መንግሥት ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን መንግሥትም ጨምሮ በአደራ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የአደራ ሥልጣን በዜጎች ላይ መለማመድ አለበት እንጂ በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጠን የለበትም። ይህም ግልጽ ነው። በቤተ እምነት ስም ኢየሱስ ሰየጠነ፥ ሰው መንፈስ ነው፥ ኢየሱስ ለሠላሳ ዓመት ሰው ብቻ ነው፥ የሚሉ አሳቾች እና ስለ ቃሉ ዋጋ ከፋይ አገልጋዮች መደመር አይችሉም። ያንን ነው unity with out purity ያልኩት።

እንዲህ የመሰለ መደመር ለቤተ ክርስቲያን የተገባት አይደለምና፥ ቤተ ክርስቲያንን ይጎዳታል እንጂ አይጠቅማትምና፥ ሊተዋት ይገብባል። 'እርሷ የክርስቶስ ናት፤ ተውአት!' ያልኩት ያንን ነው። መንግሥት ለሃይማኖት ተቋማት ያወጣው ጤናማ

ሕግና ደንብ አለ ያንን በሙሉ ጉልበት ቢተገብረው እንዴት በቂ በነበረ! እና በዚያ ዐውድ ነው የጻፍኩት።

ዱም ዱም ቀጠለች፤

Dum Dum አመሠግናለሁ ጋሽ ዘሌ፤ ነገሮችን ለማጥራት ያህል ለአንተ እንደመሠልኩህ ልቅ የወጣ ኢኪዩሜኒዝም ደጋፊ አይደለሁም። መጀመርያ በሰጠሁህ አስተያየት ላይ "በስህተት ትምህርት የተታለሉትን..." የሚሉ ቃላቶችን መጠቀሜን ብታስተውል ልክ እና ልክ ያልሆነ የሚል ግልፅ ወሰን በአስተምህሮቶች መካከል እንዳለ እንደማምን ይገባህ ነበር። በዚህ ጉዳይ እኔን ለማስተማርም ባልደከምክ ነበር። አብይ አንተ እንዳልከው በአስተምህሮ ስተትና ልክ በሆኑ የወንጌላውያን ቤተዕምነቶች መካከል መንፈሳዊ አንድነት እንዲፈጥሩ ግልፅ ጫና እያሳደረ ቢሆን እኔም ካንተ ባልተናነሰ የምቃወመው ነኝ!! ግን አብይ እንዲህ አይነት በእውነት ላይ ብቻ ሊመሠሰረት የሚችል መንፈሳዊ አንድነትና ህብረት እየጠየቀ ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለህ? ማስረጃ ካለህ አምጣውና አሳምነን። ቸኩለህ አለማስረጃ እንደደነገጥክ እገምታለሁ። ብዙ የህብረት አይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉም ዘንግተሃል። ሙስሊሞቹን ሲያስታርቃቸው በመካከላቸው ያለው ጥላቻና መወጋገድ ለሀገር የሚተርፍ መዘዝ ስላለው አስተምህሯቸውን በየጎራቸው ይዘው በመቻቻል እምነታቸውን እንዲያራምዱ በማሰብ ነው እንጂ አስገዳጅ የአስተምህሮ ጭፍለቃ አስደርጎ አይደለም። በፕሮቴስታንቱም በኩል በአለም ፊት መሳቂያ ያደረገን ግልፅ የሆነ ጥላቻ ስድብ ዛቻ እና ጥል አለ። በሁለቱም በኩል ያሉ መሪዎችና ተከታዮቻቸው ከእንደዚህ አይነት የክርስትናን ስም ከሚያጎድፍ አሳፋሪ ሃይማኖተኝነት መታቀብ እና መፅዳት እንዲችሉ የሚመካከሩበት እና የሚነጋገሩበት መድረክ ወይም ኮሚቴ ቢፈጠር ክፋት የለውም። ገና ለገና ከነ ሞክሼህ ጋር ህብረት ሲባል ደንግጠህ እረሳኸው እንጂ እንኳን ጴንጤ ለጴንጤ ቀርቶ ከእስልምና ወይም ከኦርቶዶክስ ጋርስ አስተምህሮን አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ የሚደረግ ህብረት አለኮ አይደል ጋሽ ዘሌ!! በዛ ላይ የለመድነው የመጠላላት የመገላለጥ የመሰዳደብ እና የመበሻሸቅ አፖሎጄቲክሳችን የባሰ ገፍቶ ወገንና ጠርዝ ያስያዛቸውን "የስህተት አስተምህሮና ልምምድ" ሰለባዎች በፍቅርና በክርስትያናዊ ባህርይ መልሰን ገንዘብ ማድረግ የምንችልበት ዕድልም ሊሰጠን ይችላል። ....አብይ በአስተምህሮ ጉዳይ ኢኪውሜኒስት አይደለም። ዩቲዩብ ላይ የሰማሁት አንድ ስብከቱ ሰው መንፈስ ነው ብለው የሚያስተምሩ አስተማሪዎችን በጣም ይነቅፋቸዋል። በዶክትሪን ጉዳይ ሲሪየስ ነው። እና የህብረቱን አላማ በግልፅ ሳታውቅ ቸኩለህ ደነገጥክ ብዬ ያሰብኩት ለዚህ ነው።

ለዚህ ጥያቄ ቀጥሎ የመለስኩት ይህ ነው።

Dum Dum፥ 'ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።' [ማለት] ይህ ምንም የሚያስደነግጥ ነገር የፈጠረው አይደለም። ይህን ያልኩትም ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። ይህ በገጼ የተደጋገመ አሳብ ነው። በእውነቱ 'ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ተውአት።' ለሚለው ለዚህ ጉዳይ ማስረጃ አያሻም። ፪ሺህ ዓመት ያስቆጠረ ሰነድ በእጃችን አለና ይህ ከማስረጃና ከአስረጂ ይበልጣል። ኢየሱስ ሰይጣን ነው ከሚል ሰው ጋር ኅብረት ማድረግ ከቶም አያስደነግጥም፤ ሲጀመር፥ መደረግ ስለማይችል።

'ብዙ የህብረት አይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉም ዘንግተሃል።' ላልሽው፤ የለም አልዘነጋሁም። ቡናና ወተትም፥ ውኃና ዘይትም ኅብረት ሊያደርጉ ይችላሉ። ላለፉት በርካታ ዓመታት የሠራሁት የኢንስፔክሽን ሥራ ሦስት ነገሮች (ውኃ፥ ጋዝ ነዳጅ፥ እና ፈሳሽ ነዳጅ) የሚለዩበት separators ላይ ነበር። እነዚህ ኋላ በየፊናቸው አንዱ ወደ ላይ አንዱ ወደ ታች፥ አንዱ ወደ ጎን እስኪሄዱ ለትንሽ ጊዜ አብረው በጋኑ ውስጥ ይቆያሉ። ያም ኅብረት ነው።

እና ቸኩዬም ዘግይቼም አልደነገጥኩም። ይህ ምንም አስደንጋጭነት የለበትም። እንደ ወትሮው ፊሽካ ነው የነፋሁት። ትንሽ ፊሽካ።

ከDum Dum ጋር በመጨረሻ የተለያየነው በዚህ ነው፤

Dum Dum Haha ትንሽ ፊሽካ ያቀራርበናል ጋሽ ዘሌ !! ግን ገና አላማው ጥርት ብሎ ባልለየ ኮሚቴ እና ለህብረት ሲባል እውነትን መሰዊያ ላይ ለማጋደም የቋመጠ ወፍራም የገዢ እጅ ከቤተመንግስት ባልተመዘዘበት ሁኔታ ሰለጠኑብን ብሎ እሪ ማለት ፊሽካ ቀርቶ ትንሽ ፉጨትም ይበዛበታል ባይ ነኝ።

ላለችው፥ ምናልባት። በማለት ነው መጨረሻ የተለያየነው። ትንሽ ፊሽካ ስላልኩት ነገር ለብቻ የጻፍኳት ትንሽ አሳብ አለች እሷን ለብቻ አቀርባለሁ። ትንሽ ፊሽካ ቀርቶ ፉጨትም ይበዛበታል ማለት ምንም ነገር አትናገር ነው። ካድሬ ጋዜጠኞች (ዛጌጠኞች ብሏል አንዱ) የምትሉት ድጋፍ ከሌላችሁ ዝም በሉ እንጂ አትቃወሙ እንዳሉት ማለት ነው።

ይህ እንግዲህ ገና በመጀመሪያው ቀን የለጠፍኩት አጭር ጽሑፍ ነው። በዚያ ላይ ከተሰጡት አስተያየቶች አንዱ ላይ፥ ሊያስተምር ይችላል ብዬ በገመትኩት፥ ከአንድ ሰው ጋር የተለዋወጥነው አሳብ ነው። እውነተኛ የሚመስሉኝ ጥያቄዎች ላይ ነው የማተኩረው እንጂ ተረብና ስድብ የሚጽፉም አሉ። ስለማያውቁት ነገር ለአቅመ አስተያየት ጸሐፊነት ስለበቁ ብቻ የሚጽፉም አሉ እነዚያ ያስታውቃሉና መልስ የተገባቸው አይደሉም። እንደ Dum Dum ያሉት ግን አሳቡን በማዳበር ሌሎችንም ያስተምራሉና ለዚያ ነው የመለስኩላት።

በነገራችን ላይ ለመንግሥት እንድንታዘዝ ይህ በእጃችን ያለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እዚያ ጽሑፍ ስር አንድ ሰው፥ 'ያኔ በደርግ ዘመን ነበርክ፤ ለምን ያኔ ዝም አልክ?' ብሎም ነበር። ጥሩ ጥያቄ ነው።

አዎን በደርግ መንግሥት ዘመን ነው ጌታ ያገኘኝና ማምለክ የጀመርኩት። ደርግንም ሆነ ማንንም መንግሥት በአገርና በሕዝብ ላይ እንዲሰለጥን ይሁንታ የሚሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ቃሉ በግልጽ ያስተምራል። ጨቋኙንም ሆነ መልካሙን መንግሥት ሥልጣን ፈቃድ የሚፈቅደው እግዚአብሔር ነው። ያኔ በደርግ ዘመን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ማለት እስኪቻል ተዘግተው ስለነበረ በዚያ ዘመን ክርስቲያን ለሆንን ሰዎች እውነተኛ ክርስትና ያንን ነው የመሰለን። ከዚያ በፊትም እኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥ በስደት ነው የኖረው።

እና ምን እንዲባል ነበር የተፈለገው? በደርግ ዘመን መብቴን ጠብቁልኝ እንዲባል ነበር፥ 'ያኔ ዝም ለምን አልክ?' የሚባለው? እኔን በግል ከሆነ እኔ በዚያ ጊዜ አዲስ አማኝ ስለሆንኩ ምንም አላውቅም። የሚያውቁትና ሲያገለግሉ የነበሩት ለምን ዝም እንዳሉና ለምን መፈክር እያሰሙ፥ ወይም ገጀራ ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ወደ አደባባይ እንዳልወጡ በእርግጥ መናገር እችላለሁ። ይህ ደግሞ ምንም ሳይሉና ሳያደርጉ በግፍ የታሰሩና የተገደሉም መኖራቸው ሳይረሳ ነው።

የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን እና በዘመኑ የነበረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይመሳሰሉ ነበር። ስለዚህ የስደት ክርስትና እና የአዲስ ኪዳን ክርስትና ስለሚመሳሰሉና ጤናማው ክርስትና ያንን ስለሆነ ወይም ያንን ስለሚመስል ነው የዘመኑ ቅዱሳን በጸጋ ስደቱን የተቀበሉት። ደርግ ደግሞ አምባ ገነን ወታደራዊ መንግሥት ነው። አምባ ገነንም፥ ወታደራዊም። እንዲያም ሆኖ በሮሜ 13 መሠረት በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥልጣን ያገኘ መንግሥት ነው።

አሁን መንግሥት ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣቱን አያስገባ የምንለው ይህኛው መንግሥት አምባ ገነን ስለሆነ ሳይሆን፥ ወይም ለስለስ ያለ ስለሆነ ሳይሆን፥ እንዲያውም በተቃራኒው፥ ዲሞክራሲያዊ ነኝ ስላለና መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም በመንግሥት ውስጥ ጣልቃ አይገቡም ብሎ ስለጻፈና ያንን ስለጣሰ ነው። ይህንን እንድጽፍ ያደረገኝም ይኸው ነው። በቃ ይኸው ነው።

ይህ እንግዲህ የቆንስላው አዋላጅ በተመሠረተ፥ 15ቱ በተመረጡበት በመጀመሪያው ቀን የጻፍኩት ጽሑፍ እና በዚያ ላይ የተመላልሰነው ነው።

የቆንስላው አካሄድ ትክክል አይደለም ማለት የጀመርኩት ቆንስላው በተመሠረተና ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠ ቀን አይደለም።

ቆንስላው ትክክል አይደለም ማለት የጀመርኩት ካድሬ ጋዜጠኞች ወግነው አንድ ቃል የሚናገሩ፥ አንድ መልክ ያላቸው ሰዎችን አሰልፈው፥ ኮልኩለው መገበዝ ሲጀምሩ አይደለም።

ቆንስላው ትክክል አይደለም ማለት የጀመርኩት፥ 'ለአቅመ አሳችነት የደረሱ የስሕተት አስተማሪዎች በአገራችን የሉም' የተባለ ቀን አይደለም። የመንግሥት እጅ መግባቱንና፣ ያ እጅ ንጹህ እጅ አለመሆኑን መናገር የጀመርኩት ቆንስላው የተመሠረተ ዕለት ሳይሆን ገና በተጸነሰ ቀን ሰኔ 13፥ 2011 ነው።

ካውንስሉን ለምን ካውንስል ሳይሆን ቆንስላ እንደምለው እናገራለሁ ብዬ ነበር። ካውንስሉን ቆንስላ የምለው ለምን እንደሆነ ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች ጠይቀውኛል። የምልበትን ምክንያት ልናገር። ቆንስላ ገና ሲጀመር ካውንስል ለሚባለው ስያሜ የሰጠሁት ቃል ነው። ያኔ ካውንስል ወይም ፌዴሬሽን ሊባል ገና ምርጫ ላይ ነበረ። ፌዴሬሽን ደረቅ ፖለቲካ ስለሚያስመስለው ካውንስል እንደሚሆን ይጠበቅ ነበር። ካውንስል በአጭር ቃል ጉባኤ ማለት ነው። ቆንስላ ደግሞ የመንግሥት ወኪል የሆነና የመንግሥትን ውክልና በሌላ ግዛት ውስጥ ለዚያ መንግሥት የሚሠራ ቢሮ ማለት

ነው። ልብ በሉ፤ የመንግሥት ወኪል ነው፤ የመንግሥትን ውክልና በሌላ ግዛት ውስጥ ለዚያ መንግሥት የሚሠራ ነው።

የቆንስላው መልክ በአንድ ጎኑ እንደዚያ ነው። ጉባኤ ነው ለሚሉት ጉባኤ ነው። ነገር ግን በቤተ መንግሥት ውስጥ የተረገዘና የተወለደ ስለሆነ፥ የመንግሥት ይሁንታና እውቅና የተቸረው ስለሆነ፥ ወኪልና መንግሥታዊ አደራ የተሰጠው አካልም ነው። ያደርጋል ተብሎ ከሚጠበቅበት ሥራዎች አንዱ፥ ለምሳሌ፥ በኅብረቱ ክንፍ ውስጥ ለሚታቀፉቱ ፈቃድ መስጠት ነው። ይህ ፈቃድ ሰጪነት እኮ መንግሥታዊ ሥራ ነው። አንርሳው፤ መንግሥታዊ ሥራ ነው። ከዚህ በፊት በጻፍኳት አንዲት አጭር ጽሑፍ፥ 'መንግሥት መንፈሳዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሥራዎቹን outsource ያደርጋል ማለት ነው? ብዬ ጠይቄ ነበር። ስለዚህ ከመንግሥት ተቀብሎ የመንግሥት ሥራ የሆነ ፈቃድ የመስጠት የውክልና ሥራ ይሠራል ማለት ነው። የመንግሥት ወኪል ሆኖ በሌላ ግዛት፥ በእግዚአብሔር ግዛት፥ በእግዚአብሔር መንግሥት፥ በቤተክርስቲያን የመንግሥትን ሥራ ከሠራ ቆንስላ ሊባል ይቻላል። ለዚህ ነው ቆንስላ የምለው። ቀጣዩን በቀጣይ ዝግጅት አቀርባለሁ።

በየጊዜው የማካፍላቸውን ዝግጅቶች ተካፈሉ፤ አካፍሉ። ይህ ዝግጅት ማስታወቂያ የማይለጠፍበትና ገንዘብ የማይሠራበት ነው። ይህንን አገልግሎት ለመርዳትና ለመደገፍ የምትፈልጉ በፔትሪዮን ገጼ በመግባት የአቅማችሁን ወርሃዊ ድጋፍ ማድረግ ትችላላችሁ። የፔትሪዮን ገጼ https://www.patreon.com/zelalemmengistu ነው።

እስከዚያው፥ ቃሉ ይህንን አያስተምርምና፥ ከአሳቾች ራቁ እንጂ ኅብረት አታድርጉ። ከሐሰት አስተማሪዎች ጋር በሸንገላ አንድ ከምንሆን በእውነት ብንለያይ ይሻላል። እያልኩ እሰናበታችኋለሁ።

. . . . .

ከJune 2020 በኋላ፥ (ከጥንሳመት ከቆንስላ በኋላ) በዚህ ጉዳይ በቂ ያልኩ ስለመሰለኝ መጻፌን ጋብ አደረግሁት።

ቆንስላውን ቆንስላ የምለው፥ ቆንስላ ደግሞ የመንግሥት ወኪል የሆነና የመንግሥትን ውክልና በሌላ ግዛት ውስጥ ለዚያ መንግሥት የሚሠራ ቢሮ ማለት ነው። ልብ በሉ፤ የመንግሥት ወኪል ነው፤ የመንግሥትን ውክልና በሌላ ግዛት ውስጥ ለዚያ መንግሥት የሚሠራ ነው። በቤተ መንግሥት ውስጥ የተረገዘና የተወለደ ስለሆነ፥ የመንግሥት ይሁንታና እውቅና የተቸረው ስለሆነ፥ ወኪልና መንግሥታዊ አደራ የተሰጠው አካልም ነው። ፈቃድ ሰጪነት እኮ መንግሥታዊ ሥራ ነው። የመንግሥት ወኪል ሆኖ በሌላ ግዛት፥ በእግዚአብሔር ግዛት፥ በእግዚአብሔር መንግሥት፥ በቤተ ክርስቲያን የመንግሥትን ሥራ ከሠራ ቆንስላ ሊባል ይቻላልና ካውንስሉ ቆንስላ ነው።

August 18, 2020

> ከቆንስላ በፊት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ነበረ። ከዚያ በፊት ደግሞ ሌላ ነበረ።
>
> ምን? የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር።
>
> መቼ? 1948!
>
> ማሰሪያው ምን ነበር? የትምህርተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) መመሳሰል።
>
> ቆንስላውን ስቃወም ከመቃወሚያ ነጥቦቼ አንዱ፥ 'የሐሰት አስተማሪዎችም አብረው ጀማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ መሥራቾችም ናቸው፤' የሚል ነው። ለትምህርተ ሃይማኖት ደንታቢስ በመሆን የተጀመረ ካውንስል (ማኅበር፥ ኅብረት፥ አንድነት፥ ፌዴሬሽን) በመንፈሳዊነት እና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ላይ ሳይሆን በሌሎች ማሰሪያዎች የታሰረና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች የታወረ መሆኑ ግልጽ ነው።
>
> ዛሬም የሚያስፈልገን አማራጭ እንዲህ ያለው ማኅበር ነው። በትምህርተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) መመሳሰል ላይ የተመሠረተ።
>
> ዘላለም ነኝ።

ከቆንስላ በፊት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ነበረ። ከዚያ በፊት ደግሞ ሌላ ነበረ።

ምን? የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር።

መቼ? 1948!

ማሰሪያው ምን ነበር? የትምህርተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) መመሳሰል።

ቆንስላውን ስቃወም ከመቃወሚያ ነጥቦቼ አንዱ፥ 'የሐሰት አስተማሪዎችም አብረው ጀማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ መሥራቾችም ናቸው፤' የሚል ነው። ለትምህርተ ሃይማኖት ደንታቢስ በመሆን የተጀመረ ካውንስል (ማኅበር፥ ኅብረት፥ አንድነት፥ ፌዴሬሽን) በመንፈሳዊነት እና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ላይ ሳይሆን በሌሎች ማሰሪያዎች የታሰረና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች የታወረ መሆኑ ግልጽ ነው።

ዛሬም የሚያስፈልገን አማራጭ እንዲህ ያለው ማኅበር ነው። በትምህርተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) መመሳሰል ላይ የተመሠረተ።

ዘላለም ነኝ።

**የወንጌል አማኞች አንድነት መመሥረት**

የወንጌል ሥራ እየተስፋፋ፥ የምእመናን ቁጥር እየበዛ በመሄዱ አንዳንድ የሃይማኖት ክፍሎችና ባለሥልጣኖች የወንጌል ስርጭትና ማኅበራዊ የልማት ሥራዎች በየቦታው መስፋፋትና የሕዝቡም የመማሩ ጉዳይ የግል ጥቅማቸውን የሚነካ ሆኖ ስላገኙት ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በመፍጠርና ከመንግሥት ፈቃድ የላችሁን በማለት ችግር፥ መከራ፥ እሥራትና ስደት በምእመናን ላይ ከማድረሳቸውም ሌላ የልማቱን ሥራ በማደናቀፋቸው ‘‘ሀገር የጋራ፥ ሃይማኖት የግል ነው’’ በሚለው መርህ በመደገፍ የየአውራጃዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ማለትም፥

1/ አዲስ አበባ 2/ የሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ 3/ የሲዳማ 4/ የደራሳ 5/ የነገሌ 6/ የከምባታ

7/ የወላሞ 8/ የጋሙ 9/ የጎፋ 10/ የጋርዱላ 11/ የኩሎ 12/ የጃንጀሮ 13/ የግዮን/ የጨቦና ጉራጌ

ወኪሎቻቸውን አዲስ አበባ ድረስ በመላክ የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበርን በ1948 ዓ.ም. መሠረቱ።

(የስም አጠራር የቀድሞው መሆኑን ልብ ይሏል።)

ከዚያም የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ አውጥተው በጊዜው ለነበረው የአገር ግዛት ሚኒስቴር ለሕዝብ ደኅንነት ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት አቅርበው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የማኅበሩ ሕጋዊ ህልውና ማግኘት ታምኖበት በ1955 ዓ.ም. በመንግሥት ታውቆ በቁጥር ፀ/925/55 28/10/55 በተጻፈ ደብዳቤ ‘‘የወንጌል አማኞች አንድነት’’ በሚል ስያሜ ፈቃድ አገኘ። ይህም በመፈጸሙ ከሞላ ጎደል የአባላትን መብት በሕግ ለማስከበር ረድቷል።

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የወንጌል አማኞች አንድነት ህልውና እንዲያገኝ በግምባር ቀደምነት አጥብቃ የታገለች እንደመሆንዋ መጠን፥ በትምህርተ ሃይማኖት /ዶክትሪን/ ተመሳሳይነት፥ የእምነት እህትዋ ከሆነችው ከመጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብራ አንድነቱ በሕግ እንዲታወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጋ ሕጋዊ ፈቃዱ ሲገኝ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ዓ.ም. በአንድነቱ ማኅበር ውስጥ መሥራች አባል /አካል/ ሆና ልትታቀፍ ችላለች።

(በቀጥታ ከማኅበሩ ጋር ያልተያያዘ አንድ አንቀጽ ተቀንሷል።)

ሌሎች የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር አባላትም "የክርስቶስ አንድነት ቤተ ክርስቲያን" እና "የወንድማማች ቤተ ክርስቲያን" ናቸው። በዚህም መሠረት በአንድነቱ ውስጥ የሚገኙት፥ በትምህርተ ሃይማኖት /ዶክትሪን/ ተመሳሳይ የሆኑ ከመጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን ጋር አራት አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

ምንጭ፥ በወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ ገጽ 5።

September 2, 2020

ከረቂቅ ከበደ ጋር ከነበረን የቃለ ምልልስ ቆይታ ውስጥ ዋናው ጉዳያችን ስለ ዘፈናምነት ቢሆንም ከቀረቡልኝ ጥያቄዎች አንዱ፥ ካውንስሉን ትቃወማለህ ወይ? ለምን? የሚል ነበር።




መልሱን እዚህ አካፍያለሁ።

https://www.facebook.com/100009781051944/videos/pcb.1300206306982059/1300205330315490

በ2021 በአገራችን ምርጫም ይደረግ ነበርና ቆንስላው የፖለቲካ መልኩ እየታየ መጣ። ይህችን አካፈልኩ።

March 21, 2021

ሃይማቲካ ዘቆንስላ

ቆንስላ ማለት የመንግሥት ወኪል ሆኖ መንግሥታዊ ተግባርን በሌላ ግዛት የሚተገብር ማለት ነው። በአዋጅ ቁጥር 1208/2012 የተቋቋመ የአገራችን የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስትያናት ካውንስል መንግሥታዊ ሥራን በሌላ ግዛት፥ በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ በቅልጥፍና በመተግበር ላይ የሚገኝ መሥሪያ ቤት ሆኖአል።

መንግሥት አገር በመምራት፥ ውስጣዊ ጸጥታን በመጠበቅ፥ ውጪያዊ ጥቃትን በመከላከል፥ ሕግን በማስከበር ተግባር ተወጥሮ በሚገኝበት በዚህ ጊዜ ቆንስላውም ሐሰተኞች የወንጌል ቦርቧሪዎችን፥ አጥቂዎችን፥ ረባሾችን፥ በካዮችን በመመከትና በማጥቃት በኩል ዓይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። ኢየሱስ ሰየጠነ የሚሉትን፥ ሰው መንፈስ ነው ባዮችን፥ ከቆንስላው አስወገደ። 13 ሐሰተኛ ነቢያትን ፈቃዳቸውን በመሰረዝ አዳራሾቻቸውን ዘጋባቸው። በቅዱሳን ላይ አካላዊና ንዋያዊ ጉዳት ያደረሱት የክስ ማዘዣ ወጣባቸው። በገንዘብ ብዝበዛ የተሰማሩ፥ በተለይም በምንጣፍ ስርና የሰዎች ቦርሳ ውስጥ ያልታተመና ብሔራዊ ባንክ የማያውቀውን፥ በቁጥርም ያልተመዘገበ ገንዘብ በመፍጠር የአገር ኢኮኖሚ በማግሸብ በግልጽ 'ገንዘብ ፈጠርን' ያሉት ኢዩ ጩፋ እና ጆይ ጪሮ ብሔራዊ ባንክ ክስ እንዲከፍትባቸው ጉዳያቸው ወደዚያ ተላልፏል። መድኃኒት በማስጣል ሰዎች እንዲታመሙና እንዲሞቱ ምክንያት

የሆኑት የኤርምያስ ሁሴን እና የእስራኤል ዳንሳ ድርጅቶች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲዘጉ ተወስኗል። ገስት ሃውስ በማለት የንግድ ፈቃድ ሳያወጡ እስከ ስድስት ዓመታት ሲነግዱ የቆዩ 16 ድርጅቶች እንዲወረሱ ጥያቄ ቀርቧል። የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ሳያወጡ ከዘይትና ውኃ እስከ አልባሳት ድረስ ሲሸጡ የተገኙ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች የገቢ ሰነዶቻቸውን እያሳዩ የ5 ዓመት ግብር እንዲከፍሉና ከግብር ነጻ የሆኑበት ፈቃዳቸው እንዲታገድ ተወኗል። ብዙ ሚሊየን ብር በጥቂት ዓመታት በተለያዩ ባንኮች ያከማቹት 27 'ልማታውያን ነቢያት' በማለት ራሳቸው የሚጠሩ ሰዎች የባንክ አካውንቶች እንዲፈርዙ ተደርጓል።

ተምኔታዊ ዜና ነው። ይህ ሁሉ አልተደረገም። ቆንስላው እንዲህ ያሉ አስተምህሮአዊ ጥሰቶችን እና አገራዊና ሕዝባዊ ወንጀሎችን ይጋፈጣል ብለው የጠበቁ የዋሃን አልጠፉም። መሥራች አብያተ ክርስቲያናት ከአንደኛው በኩል ቃለ ሕይወት እና እና መካነ የሱስ ነበሩ። የኢወአክን ሌላው 'ወንጌላዊ' ክንፍ ነው። ከሌላኛው በኩል ጴንጤቆስጣዊው እና ራእያሙ ይገኛሉ። ከሁሉም የለንበትም ያሉቱ አዲሶቹ የፍቅር ወንጌል ማኅበር መሥርተው ተቀላቅለዋል። ለመሥራችነት ምንም የተለየ ጥያቄ የለም፤ ቁመና በቂ ነው። እነዚህም መሥራች ተብለዋል። የመጨረሻው ሲመሠረት ያልነበረ ቢሆንም 'መሥራች አባል' ሆኗል። ሌሎች አራት ደግሞ፥ ገነት፥ መሠረተ ክርስቶስ፥ ሙሉ ወንጌል እና ሕይወት ብርሃን እነዚህ አራቱም 'መሥራች አባላት' ሆነው ተቆጥረዋል። ነገሩ እንዴት ነው? ተመሥርቶም እንዴት ነው ገና አሁንም መሥራች አባላት የሚቀበሉት? ወይስ በተመሠረተው ላይ እየተመሠረተ ነው? እነዚህ አራቱ መሥራቾችስ ቀድሞውኑ የኢወአክን አባላት ሳሉ መሥራች አልነበሩም? አሁንስ ሁለቱም ውስጥ ሆነው ድርብ መሥራቾች ናቸው?

በቅርብ የሚደረገው የግዮን ሆቴል (ካልተለወጠ) ወጣቶች እና የምንድነው የሚባለው? አባቶችና እናቶች? ወይም ጠቅላላ በእስቴዲየም (ካልተለወጠ) የሚደረጉት ዝግጅቶች እውን ከላይ ከተባለው ተምኔታዊ ዜና ጋር ግንኙነት ያለው ነገር ሊደረግ ነው ይሆን? እውነት ወንጌላዊ ክርስትና በማንነቱ ሊታወቅ ይሆን? ወይስ ተኩላና በበጎች አብረው ጥቂት ሳርና ብዙ ሥጋ የሚበሉበት ይሆን? ወይስ በአዋጅ 'የወንጌላዊ ክርስትና ቀን' ንድፍ ለማስመረቅ የሚደረግ ጥረት ይሆን? ወይስ መንግሥት ሃይማኖቶችን ሁሉ በእኩል ዓይን በማየት ፈንታ በተለያዩ ኮምፕሌክስ ዓይኖች ያየበትን የሃይማኖትና ፖለቲካን ጋብቻ ለማጽደቅ የመሠረት ድንጋይ ለመጣል?

ጠባሳን መግረፍ ያሳምማል። ሃይማቲካ ያሳምማል።

ዘላለም ነኝ።

March 3, 2021

ዶ/ር ምሕረት አምና የማደንዘዣ መርፌ ሲወጋን በአገራችን ውስጥ አሳቾች እንደሌሉ ሲገልጥ፥ "ኀበዝ የስሕተት አስተማሪ አለ ብዬ አላስብም።" ብሎ ነበር።

ከደነዘዝን፥ በመርፌም ይሁን በሌላ፥ ከዚያ በኋላ የሚሆነው ነገር አይሰምማንም፤ ወይም ብዙም አያሳምመንም። ዘንድሮ ደግሞ፥ ምንም በሉ፥ ተከታይና ተቀባይ በደርዘንም በጣቃም፥ በቁጭ በሉም በጣሳም፥ በነጠላም በጅምላም ነው።

"እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ያህል የጎላ የስሕተት ትምህርት ተፈጥሯል ብዬ አላስብም። . . . የስሕተት ትምህርት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመፍጠር አቅም ያለው አእምሮ እስካሁን አላየሁም።" ዘማሪ ይስሐቅ ሰዲቅ።

ይህኛው በእውነቱ በአገራችን የተፈለፈሉት ሐሳውያን ነቢያትና ሐሳውያን ሐዋርያት ወይም የሉም (አልተፈጠሩም) ማለቱ ነው፤ ወይም አቅም ያለው አእምሮ ከሌላቸው ነፈዝ፥ አእምሮቢስ፥ ፉዞ፥ ፉርሽ ናቸው ማለቱ ነው። የትኛው ይሆኑ?

2 ደቂቃ ብቻ ናት፤ ተመልከቷት።

https://www.facebook.com/100009781051944/videos/1450990185237003

ዘላለም ነኝ።

March 9, 2021




# የማልስማማው ወይም የምቃወመው በምክንያት ነው፤ በምክንያቶች ።

ቆንስላውን የማልስማማው ወይም የምቃወመው ያለ ምክንያት ሳይሆን በምክንያት ነው፤ በምክንያቶች። በበቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች።

ቆንስላው ከተጸነሰበት ቀን (ሰኔ 13፥ 2011) ጀምሮ የጻፍኳቸውና በቪድዮዎች ያካፈልኳቸው ምክንያቶች ናቸው ምክንያቶቼ።

March 21, 2021

መንበር እና ወንበር




ክርስቲያን እንደ ግለ ሰብ በፖለቲካ ቢሳተፍ እና ሲሳተፍ ልንቀበል ሊከብደን የተገባ አይደለም።

የቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ እምነት መሪ ቤተክርስቲያንን ወይም ቤተ እምነትን እየመራ ሳለ፥ ወይም እየመራ ባለበት የመሪነቱ ወቅት በፖለቲካ ውስጥ ሊሳተፍ ቢወድድ ግን ከመሳተፉ አስቀድሞ በአክብሮት እና በጨዋነት መንበሩን ሊለቅቅ የተገባው ነው።

ቆንስላው (የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብ/ክናት ካውንስል) የፖለቲካ ተወዳዳሪነትን እና እጩነትን የሚከለክል አይመስለኝም። ቀድሞኑም ቆንስላ ስለሆነ። ከእጩነት

እንደሚያግድ የምታውቁ ካላችሁ አሳውቁኝ። እንዲያም ሆኖ ግን፥ 'ወንጌል'፥ 'አማኞች'፥ እና 'አብያተ ክርስቲያናት' የሚሉ ቃላት ስላሉበት ቢያንስ ይህንን መከልከል ያለበት ይመስለኛል። የአገሪቱ ሕግም የሃይማኖት መሪዎች የሃይማኖት መሪነት መንበር ላይ ሳሉ ወደ ፖለቲካ ውስጥ የማስረግ እና ወንበር ላይ የማስቀመጥ ሥልጣን እንዳለው በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተደነገገ አይደለም። የሃይማኖት መሪዎችን ለመጠምዘዝ ወደ ኋላ የማይሉ መንግሥታት ቢኖሩም ማለት ነው። ቆንስላው የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ሰንበርና ጠባሳ ሆኖ የሚኖር እንደሆነ እንደገና ማሳሰብ ለኔ አይከብደኝም።

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአመራር ምርጫ ደንብ እና የእስካሁን ድረስ ወግም ይኸው ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ እንደነበረ/እንደሆነ ሰው ነው ይህንን የምጽፈው። ይሁን እንጂ የአሁኑ የቆንስላው ዋና መሪ ዶ/ር ኢያሱ ኤልያስ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪም ነው። ቃለ ሕይወት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። የዚህች ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነ ሰው የመሪነት መንበሩን ሳይለቅ የአንድ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ሲቀርብ ይህ ጠቅላላዋን ቤተ ክርስቲያን እና ቤተ እምነቱን በመላው የሚያጠይም፥ የሚያጠቁር፥ የሚያጠለሽ፥ እና የሚያጨቀይ እርምጃ ነው።

ዶ/ር ኢያሱ ኤልያስ፥ ለምርጫ መወዳደሩ ምርጫው ቢሆንም ቢያንስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እና ለመተዳደሪያ ደንቧ አክብሮት ሲል እስካሁንም ወንበሩን ሳይለቅቅ ለእጩነት በመቅረቡ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ በመጠየቅ ከአመራር መንበሩ በፍጥነት መነሣት አለበት፤ በደንቡም በወጉም መሠረት። መንበሩን እንደያዘና ሳይለቅ ለወንበር መወዳደሩ፥ ኋላ ካልተመረጠ ወደ መንበሩ መመለስን እንደ አማራጭ መያዙ ከሆነም ደንቡን እየጣሰ መሆኑ የታወቀ ሆኖ ያንን ማሳወቅ ያለበት ይመስለኛል።

ከመንበር እና ከወንበር መምረጥ የግድ ይላል።

ዘላለም ነኝ።

March 26, 2021

## የመንበር እና ወንበር ውጥረት




ባለፈው መንበር እና ወንበር በሚል ርእስ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብ/ክናት ካውንስል (ቆንስላው) መሪ የፓርቲ ተወዳዳሪ ከመሆኑ በፊት ወንበሩን ይልቀቅ ብዬ ነበር። ይህንን ጉዳይ ያያያዝኩት የቆንስላው መሪ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚደንትም ሆኖ ለፓርቲ ተመራጭነት በመወዳደር ሂደት ላይ በመገኘቱ ነው። ይህንን ያልኩት በስሜት ሳይሆን ከልቤ ነው። ከልቤ ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያኒቱ መርህ አንጻርም ነው።

በግልጽ ለመናገር ማንም ክርስቲያን ግለ ሰብ በፖለቲካ ንቁ ተሳታፊ ቢሆን ደጋፊ ነኝ። ቤተ ክርስቲያን ግን ፓርቲያዊ ወገንተኛ መሆን የለባትም። Nonpartisan መሆን አለባት ያልኩት ያንን ነው። ይህ የአለመወገን ጉዳይ በምዕራባውያኑ አብያተ ክርስቲያናት መተዳደሪያ ደንቦች እና የአሠራር መርሆዎች (working policies) ውስጥም የተደነገገ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪ ወካይ እንደ መሆኑ መጠን መሪ ሆኖ ሳለ ወገንተኛ መሆኑ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ወገንተኛ እንደሚያደርጋት ምንም ምርምር አያሻውም።

እንዳልኩት የቆንስላው መሪ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚደንትም ነው። ስለ ቆንስላው የውስጥ አሠራር ስለማላውቅ በመሪነቱና በምርጫ ውድድሩ ምንም ችግር ላይፈጠርበት ይችል ይሆናል። እንዲያውም፥ በቆንስላው እንዲወዳደርም ሊደፋፈር ሁሉ ይችል ይሆናል፤ ደንባቸውን አላውቅም። አንዳንድ ሃይማኖቶችም የሃይማኖት አባቶች ወይም መሪዎች ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆኑ የሚያደፋፍሩ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ፓርቲዎችም የአብያተ ክርስቲያናትና እና አብያተ እምነቶች መሪዎች ተጋቦትና ተጽዕኖ ፈጣሪና ድምጽ ሰብሳቢ ሊሆኑ ስለሚችሉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ሊያበረታቱም ይችላሉ። እንዲህ ያለው የብልጠት አካሄድ የውስጥ አሠራራቸው

ቢሆንም፥ በኔ እምነት ያ አካሄድ የተሳሳተ ነው፤ ምክንያቱም፥ አካሄዱ ሃይማኖታዊ ድርጅቱን ወይም ተቋሙን እና መንግሥታዊ ተቋምን ወይም መንግሥትን ራሱን የሚያሻርክ ወይም የሚያላትም ይሆናል።

የቆንስላው መሪ እንደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪነቱ የፓርቲ ወይም ድርጅት ተሿሚ ሆኖ በመሪነቱ መቀጠል አይችልም። ይህ የኔ ምኞት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቱ ደንብ ነው። የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአገልጋይ መሪዎች ምርጫ የአፈጻጸም መመሪያ፤ የተባለው፥ ሚያዝያ 2007 ዓ. ም. እንደገና ተሻሽሎ ጸድቆ የታተመው ሰነድ (Copyright © 2007 Ethiopian Kale Heywet Church) በየዕርከኑ ያሉ የተለያዩ ዘርፎች ተመራጭ አገልጋዮች መሥፈርት የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ተሿሚነትን ይከለክላል። ለምሳሌ፥ 15.1.14፤ 15.2.1.7፤ 15.2.2.7፤ 15.2.3.11፤ 15.2.4.11፤ 15.2.5.11፤ 15.2.6.11፤ 15.2.7.11፤ 15.2.8.11፤ 15.2.9.10፤ 15.2.10.9፤ 15.2.11.9፤ 15.2.12.10፤ 15.2.13.9፤ 15.2.14.9 15.2.15.10፤ 15.2.16.10፤ ወዘተርፈ፥ (ሌሎች ብዙ አንቀጾች አሉ፤ ሁሉንም አላስቀመጥኩም።) ሁሉም በየዕርከኑ ያሉ የተለያዩ ዘርፎች ተመራጭ አገልጋዮች መሥፈርት የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ተሿሚነትን ይከለክላል። 'የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ተሿሚ ያልሆነ፤' ብሎ በግልጽ ያስቀምጣል።

አንቀጽ 15.2.35 የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት መመዘኛዎችን ይዘረዝራል። እዚህም፥ 15.2.35.19 'የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ተሿሚ ያልሆነ፤' ይላል።

ተሿሚ መሆኑ ከምርጫ የሚያግደው ከሆነ በተመሳሳይ መልኩ ለሹመት መወዳደሩንም ሊያግደው ይችላል። 'የለም፤ ገና ስላልተሾመ ለምርጫ ለመወዳደር ይችላል፤' ሊባል ይቻል ይሆናል። ይህ ጉዳይ የቃላት ስንጠቃ ከሆነ ሊወዳደር ይችል ይሆናል። ነገር ግን እየተነጋገርን ያለነው መንፈሳዊ አካልን ስለመምራት ስለሆነ የውስጠ-ውጭ ማንነት ጉዳይ ነው ፍተሻው።

የቃላት ብድርና ድርድር ውስጥ ካልገባን አንድ ሰው ለፓርቲ ምርጫ ሲወዳደር ቀድሞውኑ የፓርቲው አባልና የምርጫ ቀጣናው ተጠሪ ነው። ተጠሪነት ተሿሚነት ነው። ምርጫ አሸንፎ ለአገሪቱ መንግሥት ሥልጣን እርከን ማለፊያው እርካብ ላይ ሆኖ፥ 'ኮርቻው ላይ አልተቀመጥኩም፤ ገና እርካቡን ብቻ ረግጬ ነው ያለሁት' ማለት ይቻል ይሆናል፤ በቃላት ከተጫወትን። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ደንብ በግልጽ፥ 'የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ተሿሚ ያልሆነ፤' ካለ፥ እንዳላለ መቁጠር ወይም ያለውን መታዘዝ የምርጫ ጉዳይ ነው። ቤተ ክርስቲያን ወጋኝ መሆን የሌለባት ጥሪዋና ተልእኮዋ ወንጌልና ወንጌል ብቻ ስለሆነ ነው። ይህንን የፓርቲ አለመወገን ጉዳይ የምለው ለቃለ ሕይወት መሪዎች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችም ጭምር ነው።

ያለዚያ የመንበር እና ወንበር ውጥረት ከመንግሥት ወይም ከማኅበረ ሰቡ ብቻ ሳይሆን ከራሳቸው ከአብያተ እምነቶቹ የተለያዩ አጥቢያዎች ጋርም ቅራኔና መሸርሸር፥ ብሎም መፈረካከስ ውስጥ ሊከትታቸው ይችላል። ይህ ደግሞ አሳማሚና ቤተ ክርስቲያን ታላቁን ተልእኮዋን እንድትነጠቅ የሚያደርጋት ሰላቢ አካሄድ ይሆናል።

ነቢይ አለመሆኔ ይታወቅልኝ።

ዘላለም ነኝ።

April 25, 2021

በአንድ ጊዜ የሃይማኖትም የፖለቲካም መሪ መሆን ይቻላል ወይ?




ጉዳዩ ጉዳይ ነው፤ የምስክርነት ጉዳይ።

ባለፈው ወር ማርች 21 እና 26 ‘መንበር እና ወንበር’ በሚል ርእስ ስለ አሁኑ የኢትዮጵያ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚደንት እና የቆንስላውም ፕሬዚደንት ዶ/ር ኢያሱ ኤልያስ የፓርቲ ምርጫ ውድድር ጉዳይ እና ስለ ቤተ እምነቷ አቋም ሁለት አጫጭር ጽሑፎች ለጥፌ ነበር። (በዚሁ ገጽ ማየት ይቻላል።)

በዚያ የጻፍኩት እና ለማሳየት የሞከርኩት ጉዳዩ በቀጣዮቹ ወራትና ዓመታት ሊደጋገም የሚችል ሊሆን ስለሚችል፥ በዚህ ጉዳይ አቅጣጫ ጠቋሚ እንዲሆን እና ወንጌላውያን አብያተ እምነቶች ግልጽ መስመር እንዲያበጁ ለማሳሰብም ነው። ይህ ጉዳይ እንደ ጉዳይ ሊታይ የምፈልገው ጉዳዩ የቃለ ሕይወት ብቻ ሳይሆን የማናቸውም ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እንደሚሆን በማሰብ ከቃሉም አንጻር አንድ መሪ የቤተ ክርስቲያን መሪም የፖለቲካ መሪም መሆን ተገቢው አለመሆኑን ለማሳየት ነው።

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ያላት አቋም ግልጽ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ የምርጫ ደንብ የአሠራር ዝርዝር (manual) በግልጽ ያስቀመጠው መሆኑን በማሳየት ነበር በነዚያ ጽሑፎች ይህ የመሪው አካሄድ ትክክል ያለመሆኑን ያመለከትኩት። መፍትሔው ብዬ የጠቆምኩትም ፕሬዚደንቱ በምርጫ መወዳደር የዜግነት መብቱ ስለሆነ መወዳደር መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተወዳደረ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪነት መሰናበት እንዳለበት ነው። በጽሑፎቹ ያሳሰብኩት አንድ የቤተ

ክርስቲያን መሪ መሪነቱን እንደጨበጠ ለፖለቲካ ፓርቲ መወዳደር እንደሌለበት ለማሳየት ነበር።

ለምሳሌ፥ አንድ መጋቢ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢ ሲሆን ኃላፊነት ያለው አገልጋይ መሪ ነው። በዚያች አጥቢያ ውስጥ ደግሞ የአንድ ፓርቲ አባል ወይም የዚያ ድርጅት ተቃዋሚ ፓርቲ አባል ሊኖር ይችላል። ሁለቱም የሁለት የተራራቁ ፖለቲካዊ አመለካከት እና የፖለቲካ ቡድን አባላትና ተሳታፍያን ወይም መሪዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነው አንዱን ጌታ ያመልካሉ፤ ከአንድ ጽዋ ይጠጣሉ፤ አንድ ኅብስት ይቆርሳሉ። ይህ ሲሆን ታዲያ መጋቢው የአንዱ ደጋፊ ቢሆንና ሌላውን ቢኮንን፥ ወይም ተቃራኒውን ቢያደርግና አንዱን አውግዞ ሌላውን ቢክብ ወይም በሌሎችም ላይ ይህንን ጫና ቢያሳድር በአካሉ ላይ (ማለትም፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ) ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ጠቢብነት አይጠይቅም። ለዚህ ነው የቤተ ክርስቲያን መሪ የመሪነት ኃላፊነት ላይ ሆኖ የፓርቲ ወይም የፖለቲካ ቡድን ተወዳዳሪ፥ ተመራጭ፥ ወይም ተሿሚ መሆን የሌለበት።

ክርስቲያን ፖለቲከኛ ሲሆን ወይም ቢሆን የዜግነት መብቱ ነው። ሽክሙ፥ ተሰጥዖው ወይም ዝንባሌው፥ እና ስልጠናውና ልምምዱ ካለው እንዲያውም እንዲሆን የተገባው ነው። ነገር ግን መሆን ያለበትና የሌለበት ሁኔታዎች በግልጽ ጥቁርና ነጭ ሆነው ከተጻፉ በግልጽ መራመድ ያለበት መስመር አለ። ማንሳት እና መጣል ያለበት ነገር አለ። መምረጥና መተው ያለበት ነገርም አለ። ባለፈው ወር ጽሑፍ ዶ/ር ኢያሱ በምርጫው መስመር የሚገፋ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን መሪነቱን ማስረከብ የተገባው መሆኑን አሳስቤ ነበር። ጉዳዩም ወደ መሪዎች ቀርቦ ነበር፤ ነገር ግን ተፈጻሚ አልሆነም። ጉዳዩን ለመፍታት ስለተሄደበት መንገድ ማብራራት አይጠበቅብኝም። ጉዳቱን ማሳወቅ ግን ተገቢ ነው።

እዚህ ላይ ቆም ብለን መጠየቅ ያለብን ነገር አለ፤ ይህ እኔ በግሌ የምጠይቀው ጥያቄም ነው። ይህም የምስክርነት ጉዳይ ነው። ዶ/ር ኢያሱ የቤተ ክርስቲያንን ደንብ በመጻረር እና በመጣስ ለፓርቲ ተመራጭነት ቢወዳደር፥ እና ብሎም ቢያሸንፍ፥ እና የሕዝብ መሪ ቢሆን፥ ከዚያ ኋላ የዚያን ፓርቲ ደንብ ያከብራል ወይስ ይንቃል? ለሕግ የተገዛ ይሆናል? ወይስ ራሱን ከሕግ በላይ አድርጎ ያቀርባል?

ይህ ጉዳይ ጉዳይ ነው፤ የምስክርነት ጉዳይ። የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት።

ዘላለም ነኝ።

(videoዋ የ3 ደቂቃ ብቻ ናት፤ ይመልከቷት።)

https://www.youtube.com/watch?v=wnGXMEA-ud0

August 18, 2021




የተሰመረ መስመር።

ከዚህ በፊት በሁለት ጽሑፎች በገጼ እንዳካፈልኩት በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የምርጫ አከናወን መመሪያ (manual) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ጽሕፈት ቤት ድረስ መሪዎች በአንድ ጊዜ የፓርቲ ተመራጭና ተሿሚ ሆነው፥ በተመሳሳይ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪም መሆን አይችሉም። የተበጀ ግልጽ፥

ገሀድ፥ ደማቅ፥ የሚታይ መስመር አለ። በጣም ግልጽ። አንቀጾቹንም በመጥቀስ አሳይቻለሁ።

ይህ ትክክለኛ ደንብ፥ ጥበብ ያለበት ውሳኔና ግልጽ መስመር ነው። ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ሊሆኑ ይችላሉ። በመሪነት ላይ ከሆኑ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንንም በቀላሉ ፖለቲከኛ ሊያደርጉ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሰማያዊ አጀንዳ የተሰጣት የክርስቶስ አካል ናትና፥ በውስጧ ደግሞ የፖለቲካ ሰዎች ከኖሩ የአንድም፥ የሌላም ፓርቲ ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፥ የገዥው ፓርቲ ደጋፊም ነቃፊም የሆኑ ሰዎችም ስለሚኖሩ፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሁለቱም በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ የአካል ተሳታፊ የሚሆኑባት አካል ናትና መወገን አትችልም፤ መወገንም የለባትም።

ስለዚህ ይህ የቃለ ሕይወት የመሪዎች ምርጫ የአከናወን መመሪያ በጣም ጤናማና ትክክለኛ መመሪያ ነው። ይሁንና የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና መሪ ዶ/ር ኢያሱ ኤልያስ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገር አቀፍ አመራር አካል መሪ ሆኖ፥ (በተመሳሳይ ጊዜ የቀንስላውም መሪ ሆኖ) ለፓርቲ ተወዳዳሪነት እጩ ሆኖ ሲቀርብ፥ ለምርጫ ሲሮጥ እና ሲወዳደርም የድንጋጤ ጩኸት የጮኽን ነበርን።

ጩኸቱ፥ 'ለምን ተወዳደረ?' አይደለም። ከላይ እንዳልኩት ማንም ክርስቲያን ፖለቲከኛ ወይም መሪና መልካምም መሪ መሆን ይችላል። ጩኸቱ፥ 'የቤተ ክርስቲያኒቱ ደንብ ለምን አልተከበረም?' ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ 'ደንቡ ለምን ተጣሰ?' ነው።

ይህ ጉዳይ የቃለ ሕይወት ብቻ ሳይሆን የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ጉዳይ መሆን አለበት ባይ ነኝ። ቤተ ክርስቲያን ፖለቲከኛ እንዳትሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአደባባይ ፖለቲከኛ ሲሆኑ፥ ይልቁንም የፓርቲ እጩዎች፥ ተወዳዳሪዎችና ተመራጮች ሲሆኑ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለመረጣቸው አካል ደንብ ተገዢ በመሆን፥ ወጉንም ሕጉንም በማክበር ስፍራቸውን መልቀቅ አለባቸው። ካልሆነ የተሰመረውን መስመር በላጺስ እየፋቁት ነው። ወግና ሕጉንም እየደለዙት ነው። ይህ ደግሞ ተከሏቸው ሄዶ እዚያም እመንግሥት ቤትም ተመሳሳይ ነገር እንዳያደርጉ ሊያስፈራ ይችላል።

ሌሎች መሪዎችም መስመሩን በማድመቅ ፈንታ መስመሩ ሲፋቅ፥ ደንቡም ሲደለዝ ዝም ማለታቸው የወጉና የሕጉ መፋቅ ንቁ ተሳታፍያን ወይም ተባባሪዎች መሆናቸው ነው። የተሰመረ መስመር ይከበር።

ለፕሮፌሰር ኢያሱ የምለው ይህንን ጥቅስ ነው፤

አባቶችህ የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ። ምሳ. 22፥28።

ዘላለም ነኝ።

September 30, 2021

## ኢዮብ ጨርሮ ሚራክል መኒ ብሎ አቧራ ያስነሣበት ሰሞን ነበረና ቆንስላው ባለ ሁለት ገጽ መግለጫ ጻፈ።



ከኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስልየተሰጠመግለጫ

መስከረም 20/2014 ዓ.ም

አዲስአበባ

<u>ኢትዮጵያ</u>

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስያናት ካውስል በአዋጅ ቁጥር 1208 2012በኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቋቋመ ተቋም መሆኑ ይታወቃል ።

ካውንስም በህግ ከተቋቋመ በኋላ በርካታ ስራዎችን እየሰራ የቆየ ሲሆን ከዚህምመካከል የካውንስሉ አባላት የተለያዩ አስተምህሮዎች ያላቸው በመሆናቸው ከአባል s ቤተ- እምነቶች የተውጣጡ የስነ -መለኮት ምሁራንን በማደራጀት በአስተምህሮ ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀውን አዕማድ እምነትለውይይት በማቅረብ መድረኮችን በማዘጋጀት ቤተ እምነቶችን የሚወክሉ አገልጋዮች በተገኙበት ሰፊ ውይይቶች ተደርገዋል ።

የስነ- መለኮት ግብረ ኃይሉም ከውይይቱ የተነሱ ሃሳቦችን በማቀናጀትና በማደራጀት በመመሪያ መልክ በማዘጋጀት ለውሳኔ አቅርቦ ሁሉም የካውንስሉ አባላት አዕማደ እምነቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ አሰራር እንዲበጅለት እየተሰራ ሲሆን ከዚህ አሰራር ውጪ በመሆን የስህተት ትምህርቶችንና ልምምዶችን በሚያራምዱአካላት ላይ የካውንስሉ ቦርድ በተቀመጠው የእርምት እርምጃ መሰረት እርምጃ እንደሚወስድ እየተሰራ ይገኛል ።

ከዚህም ጋር ተያይዞካውንስሉ አሰራሮችን እያበጀ ባለበት በዚህ ወቅት በአንዳንድ አገልጋዮች ዘንድ እየተስተዋለ የሚገኘው የስህተት ትምህርቶችና ልምምዶች በወንጌል አማኞች ዘንድ ከፍተኛ ጥያቄ ፈጥሮ ምዕመናንን እያወዛገበ የሚገኝ ሲሆን በቅርቡ ሚራክል መኒ የሚል ስያሜ በመስጠት የATM ካርድ እናሳትማለን ይህንን ካርድ ከ10 ሺህ ብር እስከ 100 ሺህ ብር በመግዛት ወደ ፕሮግራሙ መግባት ይቻላል ነገር ግን ይህንን ካርድበተጠቀሰው ገንዘብ መግዛት የማይችሉ አካላት ወደ ፕሮግራሙ መግባት እንደማይቻልና በተጣይም በግለሰቡ በተያዙ ፕሮግራሞች መሰረት ሰዎች


የባንክ ደብተር ይዘው እንዲሄዱ እና የባንክ ደብተራቸው ላይ ተጽልዮ ከማይታወቅበት ስፍራ ገንዘብ ገቢ እንደሚሆንላቸው ማስታወቂያዎች ሲነገሩ ተሰምቶአል ::

ይህ ጉዳይ እንደ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮ ያፈነገጠ እና ከካውንስሉ አዕማደ እምነት ውጭ በመሆኑ ካውንስሉበመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የእርምት እርምጃዎችን የሚወስድ ሲሆን ATM ማሳተም እና ማሰራጨትበህግ የተፈቀደላቸው ባንኮች በመሆናቸው የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አስፈላጊውን ክትትል እያደረጉ በመሆኑ በራሳቸው አካሄድ እርምጃ የሚወስዱሲሆን

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል አባል ቤተ እምነቶችናሕብረቶች ሁላችሁ ምዕመናን ከዚህ አይነት የስህተት ጎዳና እንዲጠበቁ ጥብቅማስታወቂያ እንድታስተላልፉመልዕክታችንን እያስተላለፍን ካውንስሉ በዚህ ጉዳይ የሚወሰደውን የእርምት ማስተካከያዎች በሂደት እየተከታተልን ለሁሉም ሚዲያዎች የምናሳውቅይሆናል ::

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
አዲስአበባ
ኢትዮጵያ

ይህንን ያደረገው ኢዮብ ጪሮ ቢሆንም የእርሱ ስም አልተጠቀሰም። ጉዳዩን ገልጠውና አውግዘው ሰውየውን አለመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ አሠራር ነው። በዚያው ቀን ራሱ ኢዮብ ጪሮም እዚያው እካውንስሉ ቢሮ ሕንጻ ውስጥ ነበረ፤ ጉዳይ እያስፈጸመ። ሲነገረው፥ ‘ምን ይቀልዳሉ? እኔ ራሴ የኅብረቱ አባል እኮ ነኝ።’ ብሎም ነበር።

ኢዮብ ጪሮ ዛሬም የቆንስላው አባል ነው።

October 3, 2021

ቆንስላው ስለ ሚራክል መኒ መግለጫ ሲያወጣ፥ ይህንን ያደረገው ኢዮብ ጪሮ ቢሆንም የእርሱ ስም አልተጠቀሰም። ጉዳዩን ገልጠውና አውግዘው ሰውየውን አለመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ አሠራር ነው።

በዚያው ቀን ራሱ ኢዮብ ጪሮም እዚያው እካውንስሉ ቢሮ ሕንጻ ውስጥ ነበረ፤ ጉዳይ እያስፈጸመ። ሲነገረው፥ 'ምን ይቀልዳሉ? እኔ ራሴ የኅብረቱ አባል እኮ ነኝ።' ብሎም ነበር።

ኢዮብ ጪሮ ዛሬም የቆንስላው አባል ነው።




አሁንም ለአቅመ ሐሰት ትምህርት አልደረስንም፤ አይደል? ወይስ ደርሰናል?

ቆንስላው መግለጫ ሲሰጥ መድረሳችንን ማብሰሩ መስሎ ስለታየኝ ነው።

ወይስ ዶ/ር ምሕረት ደበበ ማብራሪያ እስኪሰጥ ጥቂት ወይም ብዙ እንቆይ?

የሚመጡት ሐሰተኞች እነዚህ ናቸው? ወይስ ሌሎች እንጠብቅ?

October 29, 2021

ተረኛ ጠያቂ ነኝ። የምታውቁ መልሱልኝ።




በእርግጥ በዲፕሎማሲያዊ ፓስፖርት የሚንቀሳቀሱ መኖራቸው የታወቀ ሆኗልና ነገሩ (ካውንስሉ) ቆንስላ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

November 21, 2021




አይነኬው ቆንስላ!

ቆንስላው (ወይም የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ወይም ወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን (በነጠላ ልጥራት) የተገረፈችበት ሰንበር ነው፤ ሰንበሩ ሲሽር ጠባሳው ጠቁሮ ይኖራል። ቆንስላው የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ጥቁር ነጥብ ነው።

ይህን የምለው በምክንያቶች ነው። አንደኛው፥ በቤተ መንግሥት መረገዙና መወለዱ ነው።

ሁለተኛው፥ ጭልጥ ያሉ የኑፋቄዎች አራማጆችን እና መናፍቃንን እቅፍ ድግፍ አድርጎ በመያዙ ነው።

ሦስተኛም አለ። ቆንስላ ብዬ የዳቦ ስም ያወጣሁለት የመንግሥትን ሥራ ተቀብሎ በእግዚአብሔር ስምና በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ስለሚተገብር ነው። በዚህ ረገድ የመንግሥት መንፈሳዊ ክንፍ መምሰሉ እውነት ነው። መምሰል ብቻ አይደለም። አሁን ፈቃድ ሰጪ አካል በመሆኑ የሃይማኖታዊ (ለጊዜው የክርስትና እንበለው) መንግሥታዊ ሥራን በውክልና እየሠራ መሆኑ ግልጽ ነው።

አራተኛም አለ። ከቅርብ ወራትና ሳምንታትና ቀናት ወዲህ ደግሞ በእርግጥም ቆንስላዊ ሥራውን በገሃድ እየፈጸመ ብቻ ሳይሆን አትንኩኝ እያለም ይገኛል።

የንግግርና የጽሑፍ፥ የሕሊናም ነጻነት በሚከበርበት አገር መንግሥትንም በጨዋነት መቃወም ይቻላል። መንግሥትንም። ቆንስላው መናገርና ቆንስላውን መንቀፍ ግን አይነኬ እየሆነ ነው። አንድ ነገር አይነኬ ከሆነ፥ ወይ በጣም ቆሻሻ ሆኖ የማይነኩት ነው ማለት ነው፤ ወይም ጉልቤ ሆኖ የማይደፈር ነው ማለት ነው። ሁለቱም መጥፎ ነው።

ስመለስ።

ዘላለም ነኝ።

ስመለስ እያልኩ የማካፍለው ሰፋ ያለ ነገር ወይም በቪድዮ የሚቀርብ ነገር ሲኖር ነው። ይህ በቪድዮ የቀረበ ነው። ሊንኩም፤

https://www.youtube.com/watch?v=ueWgCeK7u30

አይነኬው ቆንስላ . . .

የዛዲግ ብርሃኑ ቪድዮ እንዲወርድ መደረጉ የምን ፍርሃት ነው? የቄስ ግርማ ቪድዮስ? እነዚህ ስለ ቆንስላው ስነ መለኮታዊና አስተዳደራዊ ነገሮች ሒስ በማቅረባቸው ብቻ መታገድ ነበረባቸው?

የቢሮ ሠራተኞቹ ከ50 እና 60 እስከ 90 ሺህ ብር የሚከፈላቸው ናቸው፤ በወር። ለዚህ ነው ማስፈራራቱ?

ጤናማ ድርጅት የሒስ የሚድያ ግብዓቶችን አስፈራርቶና ዝቶ በማስነሣትና በማሸማቀቅ ነው ንጽሕናን መግለጥ የሚችለው? ወይስ ፈትሹኝ ንጹሕ ነኝ ብሎ በመፍፈተሽ? ሰሞኑን እንደሚደረገው መንገድ ወይም ኬላ ላይ መቆምና መፍፈተሽ የሚፈራው ማን ነው? ጤናማ ሰው? ወይስ ወንጀለኛ?

የዘንድሮው የቆንስላው ምርጫ ስብሰባ፥ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ኅብረት እና ሌሎች አራት ያህል ቤተ እምነቶችም፥ 'አመኔታ የሌለው ነው።' ብለው ያልተገኙበትና አሳውቀው የወጡበት ስብሰባ ነው።

በጽ/ቤት ኃላፊው፥ '"ሂሳብህን በቅርቡ ስለምታወራርድ ተረጋጋ' ተብሎ የታገደው የአማኑኤል አሰግድ ጽሑፍ የቆንስላው ፕሬዚደንት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪነትንና የፖለቲከኛነትን ሁለት ማሊያ አይልበሱ የሚል አሳብ ነው። ይህንን እኔም ከቃለ ሕይወት መተዳደሪያ በመጥቀስ ብዬዋለሁ። ይህ ጽሑፍ እውነት ዛቻ መጥራት ነበረበት?

ይህ ጉዳይ ፖለቲካ አይደለም እንጂ፥ ፖለቲካ እንኳ ቢሆን በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት አይቻልም ወይም አይፈቀድም ማለት ነው?

ቪድዮው እነሆ፤

ቪድዮው ወደ ጽሑፍ የተመለሰው ቀጥሎ ይገኛል፤

December 4, 2021




አይነኬው ቆንስላ!

ቆንስላው (ወይም የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ወይም ወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን (በነጠላ ልጥራት፤ ወንጌላዊ የክርስትና እምነትን ማለቴ ነው።) ቆንስላው ያቺ ቤተ ክርስቲያን የተገረፈችበት ሰንበር ነው፤ ሰንበሩ በጊዜ ሂደት ሊሽር ይችላል፤ ይሽር ይሆናል፤ ግን ጠባሳው ጠቁሮ ይኖራል። ስለቆንስላው ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ተናግሬአለሁ። ቆንስላው የኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ግራጫ ሳይሆን ጥቁር ነጥብ።

ይህን የምለው በምክንያቶች ነው። ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንደኛው፥ በቤተ መንግሥት መረገዙና መወለዱ ነው። ቤተ መንግሥታዊ ድርጅት ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው፥ ጭልጥ ያሉ የኑፋቄዎች አራማጆችን እና መናፍቃንን እቅፍ ድግፍ አድርጎ በመያዙ ነው።

ሦስተኛ፥ ቆንስላ ብዬ የዳቦ ስም ያወጣሁለት፥ ቆንስላ የአገር ሥራን በሌላ መንግሥት የሚተገብር በመሆኑ፥ ይህም በእግዚአብሔር ስም በተጠራ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ የመንግሥትን ሥራ ተቀብሎ ስለሚተገብር ነው። በዚህ ረገድ የመንግሥት መንፈሳዊ ክንፍ መምሰሉ እውነት ነው። መምሰል ብቻ ሳይሆን ከመምሰልም ያለፈ ነው። አሁን ፈቃድ ሰጪ አካል በመሆኑ የሃይማኖታዊ (ለጊዜው የክርስትና እንበለው) መንግሥታዊ ሥራን በውክልና እየሠራ መሆኑ ግልጽ ነው። ቁርኝቱ ከገዥው ፓርቲ ጋር ከሆነም ሌላ ፓርቲ ገዥ ሲሆን ከመንግሥት ጋር ያለው ቁርኝት ምን እንደሚመስል በሂደት የሚታይ ይሆናል።

አራተኛ፥ ከቅርብ ወራትና ሳምንታትና ቀናት ወዲህ ደግሞ በእርግጥም ቆንስላዊ ሥራውን በገሃድ እየፈጸመ ብቻ ሳይሆን አትንኩኝ፥ ራቁኝ፥ አትድረሱብኝ እያለም ይገኛል። በዚህ ዝግጅት የማተኩርበት ጉዳይ ይህኛው ነጥብ ነው።

የንግግርና የጽሑፍ፥ የሕሊናም ነጻነት በሚከበርበት አገር ማንም ሰው ምንም ነገር የመጻፍና አሳቡን ዛቻና መታሰርን ሳይፈራ የመግለጥ መብት አለው። በአምባ ገነናዊ መሪዎች አገር ካልሆነ በቀር፥ መንግሥትንም እንኳ በጨዋነት ማሔስና መቃወም ይቻላል፤ መንግሥትንም እንኳ። ኢትዮጵያ ውስጥ ቆንስላውን መናገርና ቆንስላውን መንቀፍ ግን የማይታሰብ እየሆነ ነው። ቆንስላው (ወይም የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) አይነኬ እየሆነ እየመጣ ነው።

አንድ ነገር ደግሞ አይነኬ ከሆነ፥ ወይ በጣም ቆሻሻ ሆኖ እንደ ኩስ የማይነኩት ነው፤ ወይም ጉልቤ (ወይም በእንግሊዝኛ bully ይባላል) ያንን ሆኖ የማይደፈር አስፈራሪ ነው ማለት ነው። ሁለቱም፥ መቆሸሹም፥ ጉልቤነቱም መጥፎ ነው።

እምነትና ሃይማኖት የሕሊና ነጻነት ገጽታ ስለሆነ (በአንዳንድ አገሮች ሊከለከል ቢችልም) የሕሊና ነጻነት ወይም ተፈጥሮአዊ መብት ስለሆነ ፈቃድ ባያስፈልገውም፥ ለሃይማኖታዊ ልዩ ልዩ አሠራሮች ፈቃድና ድንጋጌ ካስፈለገ፥ ያንን መስጠት ያለበት መንግሥት ነው፤ ሃይማኖታዊ ስብሰባዎቹ ሕዝባውያን ስብሰባዎች ስለሆኑ። መሰብሰብ ካለ ደግሞ መሰብሰቢያ ቦታ ያስፈልጋል፤ ዛፍ ስርም እንኳ ቢሆን፥ 'ያ ስፍራ ለአካላዊ ጉዳት ይዳርጋል ወይ? በማለት፥ ሕንጻ ከሆነም ያ ቦታ ሕጋዊ ነው ወይ? ስፍራው የከተማውን ዞን የመጠነ ነው ወይ? ሕንጻው የሕንጻ መስፈርቶችን፥ ለምሳሌ፥ ጠንካራ መሠረትን፥ ለአደጋ ጊዜ መውጫዎችና ሌሎች ነገሮችን ያሟላ ነው ወይ? ወዘተ፥ ያሉት ደግሞ በከተማው አስተዳደር ወይም የሚመለከተው ክፍል ፈቃድ የሚከናወን ነው። ከሁለት ዓመት በፊት የቲቢ ጆሹዋ ሕንጻ በውስጡ ካሉት ሰዎች ጋር ተደርምሶ ከመቶ በላይ ሰዎች መሞታቸውን እናስታውሳለን። ሲመረመር ችግሩ ምን ሆኖ ተገኘ? መስፈርቶችን ያላሟላ ግንባታ ሆኖ ነበር የተገኘው። ይህ ሁሉ ይታያል ከፈቃድ ጋር።

እንደ ኢትዮጵያ ባለ በጎሳ በተከፈለ አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ ይህ አሠራር ችግር የሌለበት ሊሆን አይችልም። ሆኖም የነጻነት ፈቃዱ መንግሥታዊ፥ ተግባራዊ አሠራሩ ደግሞ የመንግሥት እርከን አንዱ ክፍል መሆን አለበት፤ ለምሳሌ የከተማ አስተዳደር።

ቆንስላው ግን የፈቃድ ሰርቲፊኬቶች እየሰጠ ይገኛል። ሰዎችም በማኅበራዊ ሚድያ ሁሉ ላይ የፈቃድ ምስክር ወረቀታችውን እየለጠፉ ያሳዩናል። ችግር የሚፈጠረው ቆንስላውን የሚቃወም የወንጌላዊ እምነት አካል ፈቃድ ቢጠይቅስ? ይሰጣል? ይሰጥ ይሆናል፤ ይህም በሂደት የሚታይ ይሆናል። ፈቃዱ ቢቀር እንኳ ስለ ካውንስሉ የሚጽፉና በግልጽ የሚቃወሙ ሰዎችንስ እንዴት ነው የሚያስተናግደው? የሚያስደነግጠውና የምናገርበት ጉዳይ ይህኛው ጉዳይ ነው።

ዛዲግ ብርሃኑ November 19, 2021 (ከ2 ሳምንት በፊት?) በፌስቡክ ገጹ ይህንን ጽፎ ነበር።

ካውንስሉ አትናገሩኝ እያለ ነው!!! አይ ካውንስሉ? ደግ ደጉን ብቻ ስለእኔ ተናገሩ የሚለው ይህ ቢሮ መንፈሳዊ ተቋም የሚመስላችሁ ተታላችኋል የምለው በምክንያት ነው እኮ!!?? በውስጡ የተሰገሰጉትን ደግሞ አትጠይቁኝ። በተለይ አንደኛው የወንጌላዊያኑን ህብረት ከድሮ ጀምሮ የሚጠላና ለማፍረስ ተልእኮ ያለው ነው። ቃለ-መጠይቁ ላይ ስላነሳሁት ተበሳጭተቷል መሰለኝ። [ዛዲግ ቃለ ምልልስ ተደርጎለት ነበረ። ብዙ ጊዜ በቆንስላው ላይ እንደጻፈና እንደተናገረ ሰው እኔም ሰምቼዋለሁ። የዛዲግ ጽሑፍ ይቀጥላል፤]

በቅርቡ ከክርስቲያን ኒውስ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ያልተደሰተው ካውንስሉ እኔን የሚመለከት ምንም አሉታዊ ነገር ማንም ማውራት አይችልም በሚል ራስን የመከላከል ዘዴ ቃለ መጠይቁን ከዩትዩብ ላይ በብዙ ማስፈራራትና ግብ ግብ እንዲወርድ አስደርጓል። ካውንስሉን በተመለከተ የተሰሩ ብዙ ስራዎች ዩትዩብ ላይ እንዳለ ረስተውት ይሆን? ወይስ ማፈን የሚችሉትን ብቻ ነው አስፈራርተው የሚያፍኑት?

ካውንስሉ የራሱን ድምጽ ብቻ እያሰማ ያለተቀናቃኝ አካል መግዛት ይፈልጋል መሰለኝ በተቃራኒ የሚናገሩትን ድምጽ ማፈን የጀመረ ይመስላል። ለማንኛውም ጊዜው የእነሱ ስለሆነ የሚያደርጉት ነገር አይታወቅምና መዘጋጀቱ አይከፋም ለማለት ነው።

ጽሑፉ ይህ ነው። ብዙ ጊዜ ቪድዮ አስወራጆች ቪድዮዎቻቸው ቀድሞውኑ ወርደው የሚፈልጓቸው ሰዎች ዲጂታል ቋት ውስጥ እንደሚቀመጡ የሚያውቁ አይመስሉም። ሕዝባዊ የግንኙነት መርህ ጥሶአል ብሎ ራሱ ዩቲዩብ ቢያስወርድ በምክንያት ነው፤ ሂደት አለው፤ ማን እንዳስወረደ ይታወቃል፤ ይግባኝ መጠየቅም ይቻላል። ረባሹ ነገር፦ ቆንስላው ግን እያደረገ ያለው ወደ ፌስ ቡክ ስሞታ አቅርቦ በፌስቡክ ማስዘጋት አይመስልም፤ አይደለምም።

ከዚህ በፊት ጥቁሩ ብዕር በሚል ርእስ ስለ ቆንስላው የተሠራ ቪድዮ ዩቲዩብ ላይ ይገኛል። ያንን ተከትሎ አንድ ወንድም በቆንስላው ላይ የጻፈው ጽሑፍ ነበረ። ያንን ጽሑፍ በማስፈራራት ከጸሐፊው ገጽ እንዲነሣ አድርጓል፤ ወይም አስደርጎአል፤ ማን? ቆንስላው ራሱ። እጁ እየረዘመ መጣ፤ የማን? የቆንስላው።

ከዚያ እንዲነሣ የተደረገ ጽሑፍ ጥቂት ላካፍል። ከዚያ በፊት አንድ ነገር ልናገር። ይህንን የምናገረው የቃለ ሕይወትን ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ራሴን ወክዬ ቢሆንም ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ በመመልከት ነው የምናገረው። ከዚህ እይታዬ አቅጣጫ ከዚህ በፊት ተናግሬአለሁም ጽፌአለሁም። የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ወደ ቆንስላው እንዳትቀላቀልና ቢቻል ቀድሞ ለሦስት ሆነው በንጉሡ

ዘመን መሥርተውት የነበረውንና ኋላ ሟሙቶ የጠፋውን፥ 'የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር' የተባለውን ማኅበር መልሰው እንዲመሠርቱ ጥያቄ አቅርቤ ነበር። ይህን ያቀረብኩት ራሴም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምዕመንም አገልጋይም እንደመሆኔ መጠን ነው። ጌታን የመቀበል ውሳኔ ያደረግሁት በወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በ5ኪሎ ቅርንጫፍ ቢሆንም፥ የእምነት ማጽኛ እንደጨረስኩ በውኃ ባለመጠመቄ ጥያቄ ተፈጥሮብኝ፥ ቅርም ብሎኝ ወዲያው በኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ ውስጥ ሆንኩ። ከ4 እና 5 ዓመታት በኋላ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በደብረ ዘይት ቃለ ሕይወት ቤ/ክ ወንጌላዊ በመሆን፥ ከዚያም የሴሚነሪ ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ዋናው ጽ/ቤት የስነ ጽሑፍ ክፍል ውስጥ አገልግያለሁ። ለቃለ ሕይወት ከቆንስላው እንድትርቅ ልመና ሳቀርብ ግድ እንደሚሰማው እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመንም አገልጋይም ነው። ይህ ልመናዬ ባለመሰማቱና ቃለ ሕይወት የቆንስላው መሥራች አባል በመሆኗ አዝኛለሁ።

ይሁንና ቆንስላው ሲረገዝና ሲወለድ፥ ኋላም ሲዋቀር እንደ ትልቅነቷ መጠን የምታገኘው የድምጽ ተሰሚነትና የመሪነት ስፍራ ይሁን፥ ወይም መሪዎቹ ለሥልጣን ያላቸው የተለየ ጥማት ይሁን፥ ወይም የውጪና የውስጥ ግፊት ይሁን አላውቅም፤ መሥራች አባል ሆነች። እንደ ትልቅ ወንጌላዊ ቤተ እምነትነቷ መሪነቱንም፥ የቦርድ መሪነቱን ተቀዳጀች። የመጀመሪያው ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ኢያሱ የቃለ ሕይወትም፥ የቆንስላውም መሪ ሆኖ እያለ ለፓርቲ ተመራጭነትም ሮጠ። ይህ የቃለ ሕይወትን ደንብ የጣሰ አካሄድ ነበርና ይህንን ጉዳይም ወደ አደባባይ አቅርቤው ነበር። ደንቡን ቢያከብር ለምርጫ ከመወዳደሩ በፊት ስፍራውን ማስረከብ ነበረበት። ምንድነው እየታየ ያለው? ቢባል፥ ከደንብ በላይ፥ ከሕግ በላይ የመሆን አዝማሚያ ነው። አዝማሚያ ብቻ ሳይሆን መሆን ራሱም ነው። ነገ ሌላው ደንቡን ቢረግጥ፥ ሃይ ማለት ወይም ለምን? ብሎ መጠየቅ አይቻልም።

ወደታገደው ጽሑፍ እመለሳለሁ። . . .

ፕሮፌሰር ኢያሱ የፓርላማ ምርጫውን ከፈጸመና የፓርላማ አባልና የግብርና ሚኒስቴር ደኤታ ሆኖ ከተሾመ በኋላ በቅርብ በተደረገው በአዲሱ የቆንስላው ምርጫ ወንበሩን ሲለቅቅ የቆንስላውን ፕሬዚደንትነት በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት የፕሮፌሰር ኢያሱ ምክትል የሆነው የዶ/ር ጣሰው ገብሬ ሆኗል። ሌሎችም በየእርከናቸው ተመርጠዋል። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም፥ ተቀጣሪ ሠራተኞችም ቦታቸውን ይዘዋል። የተቀጣሪ የጽ/ቤት ኃላፊም ቦታ የቃለ ሕይወት ሰው ሆነ። የጽ/ቤት ኃላፊ ማለት የቢሮውን የቀን ተቀን ሥራ ተግባሪ ሰው ማለት ነው፤ ያ የኃላፊነት ስፍራም የቃለ ሕይወት ቤ/ክ ሰው የሆነው የፓ/ር ጌትነት ለማ ቢሮ ነው። [በነገራችን ላይ፥ የቢሮ ሠራተኞቹ ከ50 እና 60 እስከ 90 ሺህ ብር የሚከፈላቸው ናቸው፤ በወር።]

ከቢሮው ተግባራት አንዱ በቆንስላው ላይ የሚቃጡትን ሒሶች የማፈን ሥራም ይመስላል። የተጻፉ ነገሮች ማስነሣት፥ የተለጠፉ ቪድዮዎች ማስወረድ፥ ያንን ለማድረግ መንፈሳዊም ምድራዊም፥ መንግሥታዊም ተቋማዊን ጉልበት መጠቀም ይቻላል፤ እንደሚመስለው። ይህ የጽ/ቤት ኃላፊው ተግባር ነው።

የዘንድሮው የምርጫ ስብሰባ፥ በነገራችን ላይ፥ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ኅብረት እና ሌሎች አራት ያህል ቤተ እምነቶችም፥ 'አመኔታ የሌለው ነው።' ብለው ያልተገኙበትና አንዳንዶቹም ~~ረግጠው~~ አሳውቀው የወጡት ስብሰባ ነው። ኅብረቱን (ማለትም፥ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ኅብረትን) አጥብቀው የሚንቁና የሚጠሉም ተመርጠውበታል። ገና ከአሁኑ፥ ገና በዓመቱ፥ ንቀትና ጥላቻ በወንጌላውያን አማኞች መካከል መከሰቱ ወደ ምን እየሄድን እንደሆነ አመላካች ነው። በውስጡ የተሰገሰጉትን መናፍቃንና የኑፋቄ አስተማሪዎች ሳንነካ ማለት ነው።

ወደ የታገደ ቪድዮ ልምጣ። ነጻነት በሚደነቅበትና ሕግ በሚከበርበት ማኅበረ ሰብ፥ ማንም ሰው የመናገርና የመጻፍ መብቱ ሊከለከልና የጻፍከውን አንሣ ያለዚያ የሚከተልህን አሳውቅሃለሁ እየተባለ ተሸማቅቆ የጻፈውን መሰብሰብ የለበትም። በኢትዮጵያ ይህ ነጻነትና መብት በሕግ የተደነገገ በመሆኑ ሰዎች መንግሥትን እንኳ ሳይቀር በብዕራቸውና በአሳባቸው አጋድመው ማረድ ይችላሉ፤ በብዕራቸውና በቀለማቸው፤ በአሳባቸውና በአመለካከታቸው፤ በመናገሪያ አንደበታቸውና በኪነ ጥበባቸው። ይህ የተከበረና የሚከበር መብታቸው መሆኑ የታወቀ ነው። መንግሥት አምባ ገነን ሲሆን፥ አምባ ገነን መንግሥት ፈሪ መንግሥት ነውና፥ ምንም እና ማንም ተቃዋሚ ብቅ ሲል አናቱን ማለት ልማዱና መታወቂያው ነው። በተለይ የሚጽፉና የሚያሔሱ ሰዎችን ይጠላል፤ ያስፈራራል፤ ያስራል፤ ያስወግዳል።

ሒስን የሚጠላ ማንም ሰው እና ማንም አካል ችግረኛ ነው። ይሳሳታል፤ መሳሳቱ እንዲነገረው አይፈልግም። ይዋሻል፤ ውሸታም ነው ማለት ነው። ያልሆነውን መስሎ ለመታየት የሚፈልግ ግብዝ ነው ማለት ነው።

ወደታገደው ጽሑፍ ልምጣ፤ በጽ/ቤት ኃላፊው የታገደው የአማኑኤል አሰግድ ጽሑፍ

ብልፅግናን ክርስትና ስለማንሳት ዛሬ የሁለት ሰአት ዜና ላይ የብልጽግና ፓርቲው ተመራጭ የሃይማኖት አባት በሚለው ካባ ቀርበው ነበር። የፖለቲካ ወገንተኝነታቸውን በ2013 ምርጫ ያተሙት ሰው የሃይማኖት አባት ተብለው ረዘም ያለውን የዜና ጊዜ ተቆጣጥረውት ታይቷል። በሃይማኖት አባት ስም መቅረባቸው ለቤተክርስቲያን የሚሰጠው መጥፎ መልእክት ብዙ ያላሳሰባቸው "ፕሬዝዳንቱ" ፖለቲከኝነታቸውን ክርስትና ለማንሳት ሲጥሩ ነበር።

ፕሮፌሰሩ ከተናገሩት ነገር ፀብ የለኝም። በብዙ ሃሳባቸውም እስማማለሁ። በዚያ ላይ ማንም ሰው የወደደውን ፖለቲካዊ አመለካከት መያዝ መብቱ ነው። የፈለገውን ፖለቲካዊ ቡድን መቀላቀልም ሰብአዊ መብቱ ነው። ነገር ግን ፕሮፌሰር እያሱ ወይ ፖለቲካቸውን ወይ ቤተ እምነታቸውን ለመምረጥ የከበዳቸው ይመስላሉ። የፓርቲውን የቤት ስራና የቤተ እምነቱን የቤት ስራ እያምታቱ መመላለሱ አግባብ አይደለም።

የአንድ ትልቅ ቤተ እምነት መሪ ሆኖ በሁለት ማልያ መጫወት ቤተ እምነቱንም ሆነ ወንጌላውያንን ይጎዳል (ግድ የሚሰጠው ከተገኘ)። በአንድ በኩል የሃይማኖት መሪ




በሌላ በኩል ተመራጭ የፖለቲካ ወገንተኛ መሆን ቤተ እምነቱንና መተዳደሪያ ደንቡን ማናናቅ ነው። ደግሞም it doesn't fit the profile for neither.

"ቤተክርስቲያን መራሔ እሴቷ ከመንግስት ፍጹም የተለየ በመሆኑ ጉርብትናው ሰላማዊ አይደለም።" ይላል ሚኒሊክ አስፋው በክርስቲያናዊ ስነ ምግባር መጽሐፉ (ገጽ 95)። ከመንግስት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር መንግስታት ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ፕሮፌሰሩ አይነት ሰዎች ማኖራቸው የተለመደ ነው። ምንም እንኳን እንደ ብልጽግና ፓርቲ አይን አውጥተው የቤተ እምነት መሪን የፓርቲ ተመራጭ ለማድረግ ድፍረት የላቸውም። ከሁለት አንዱን መጣል ይገባቸው። ቤተክርስቲያን ያለመራሔ እሴቷ በጦርነት መኸል ሚናዋን የማትወጣበት ምክንያት አንዱ ይሄ ነው።

ቤተክርስቲያን በገለልተኝነት የማንም መጠቀሚያ ከመሆን መላቀቅ ይኖርባታል። በፍርሃት ቆፈን ከማያዝ እኩል በፍቅር እፍ ብሎ ከመክነፍ መስከን መሰረታዊ መርህ ይመስላል። በዚህ ውሉ በጠፋው ምስቅልቅል ነብያዊ ተልእኳዋን ገለልተኛ በመሆን መወጣት ይኖርባታል።

ፕሬዝዳንቱ ከሁለት አንዱን ማልያቸው ብቻ እንዲጠቀሙ የሚመክራቸው ሰው ቢኖር ደግ ነው። አለበለዚያ ፖለቲካቸውን ክርስትና ለማንሳት የሚያደርጉት ሙከራ ለፖለቲካቸውም ለእምነታቸውም አይበጅም!

ይህ የታገደው የአማኑኤል አሰግድ ጽሑፍ ነው። ከመታገዱ በፊት ራሱ የጽ/ቤት ኃላፊው ፓስተር ጌቱ ለማ ከጽሑፉ ስር አስተያየት ጽፎ ነበር፤ ይህ ነበር አስተያየቱ፤

‘ሂሳብህን በቅርቡ ስለምታወራርድ ተረጋጋ’ ማለት ጥሬ ዛቻ ነው። ምንም ነገር ስለ ቆንስላው ወይም ካውንስሉ መጻፍና መናገር አይቻልም ማለት ነው፤ ሂሳብ ሳያሰሉ።

አፍ ለማስዘጋት የሚደረገው ርብርብ ስለሚከፈላቸው ብዙ ሺህ ብር ዘብ ለመቆም ነው? ወይስ እውነት ቆንስላው ሕጻጽ አልባ በመሆኑ ነው? ሕጸጽ አልባ ከሆነስ መናገርንና መጻፍን በማገድና በማስፈራራትና የተለጠፉ የሚድያ ግብዓቶችን አስፈራርቶ አንሡ በማለትና፥ ሂሳብ ስለምታወራርዱ ተረጋጉ ብሎ በማሸማቀቅ ነው ንጽሕናን መግለጥ የሚቻለው? ወይስ ፈትሹኝ ንጹሕ ነኝ ብሎ በመፍፈተሽ? ንጹህ ሰው መፍፈተሽ አይፈራም፤ ኬላ ላይ መቆም አይፈራም። ሰሞኑን እንደሚደረገው መንገድ ላይ ቆሞ መፈተሽ አይፈራም። የሚፈራው ጤናማ ያልሆነው ነው።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልበል፤ በፖለቲካዊ አመለካከት ከአማኑኤል አሰግድ ጋር አልስማማ ይሆናል። ክርስቲያኖች ፖለቲከኞች ሊሆኑ ይችላሉ። ደጋግሜ እንዳልኩት ግን በመጀመሪያ ክርስቲያን ሲቀጥል ፖለቲከኛ መሆን አለባቸው። ፖለቲካው ክርስትናውን መዋጥ የለበትም። ግን ታዲያ ድፍን ኢትዮጵያ በፖለቲካ አመለካከት አንድ መሆን አለበት ወይ? ተቃዋሚ ወይም ተፎካካሪ መሆን አይቻልም ወይ? ተቃዋሚ ወይም ተገዳዳሪ የመሰለ ሰውን፥ 'ሂሳብህን ታወራርዳታለህ ወይም ስለምታወራርድ ተረጋጋ' የሚል የቆንስላ የጽ/ቤት ኃላፊ ፓ/ር ጌቱ ለማ ለፓርቲ ወይም ለመንግሥት ነው የቆመው? ወይስ ለሃይማኖት? ለወንጌላዊ ክርስትና? ጥያቄ ነው፤ መልስ ከኖረው። ለፓርቲ ወይም ለመንግሥት ወግኖ ከቆመ እንደ ኤልዛቤል ነቢያት ከመሆን ምን ይለየዋል? ጥያቄ ነው፤ መልስ ከኖረ።

ከታገዱት ቪድዮዎች ጥቂት ላቅርብና ወደ መደምደሚያው አልፋለሁ።

. . . . .




ስደመድም የምለው አጭር ነገር ነው።

የንግግርና የጽሑፍ፥ የሕሊናም ነጻነት በሚከበርበት አገር አንድ ዜጋ ምንም ነገር የመጻፍና አሳቡን ዛቻና መታሰርን ሳይፈራ የመግለጥ መብት እንዳይኖረው የሚፈልግ መንፈሳዊ ነኝ የሚል ድርጅት ወይም ቆንስላ (ማለትም፥ የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) አይነኬ እየሆነ እየመጣው ለምን ይሆን? አለመነካትንና ማስፈራራትን፥ ዛቻንና ማሸማቀቅን የሚወነጭፍ፥ 'የጻፍከውንና የለጠፍከውን አውርድ ያለዚያ ሂሳብህን ታወራርዳለህ!' የሚል ቆንስላ (ማለትም፥ የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል) ለምንድር ነው መነካትና ሒስን አምርሮ የፈራው? ጉልቤነት ነው? በመንግሥት ተገን ማስደንገጥ ነው? ፈቃድ መስጠትና መከልከል ብቻ ሳይሆን የምንጽፈውን መፍቀድና መከልከል፥ የምንቀርጸውን ማገድና ማስወረድና ማጨናገፍ የመፈጸም ሃይማኖታዊ አምባ ገነንነት ነው?

ጥያቄ ነው፤ መልስ ከኖረው።

March 24, 2022

ቆንስላውና ኅብረቱ አንዳንዴ ታንጎ ሲደንሱ አንዳንዴ ጀርባ ለጀርባ ሲቆሙ ታይቶአል። በሂደት የታዘብኩት ነገር ለአስተምህሮና ለስነ መለኮት ጥራት ሳይሆን ለወንበርና ጥቅማ ጥቅም ብቻ የሚደረግ ድርድር መሆኑን ነው።



March 26, 2022

በዚሁ ሰሞን ከአክሊለ ሽመልስ ጋር በዚሁ ጉዳይ ዙሪያም ቆይታ አድርገን ነበር። በቆንስላውና በኅብረቱ ግንኙነትም ዙሪያ ተነጋግረን ነበር።




ቪድዮው እዚህ ይገኛል።

https://www.youtube.com/watch?v=Ue1J1PWh4VU

ይህኛው ንግግር ወደ ጽሑፍ አልተመለሰም።

October 8, 2022

በOctober መጀመሪያ ሳምንት 2022 ባዕድ፤ ሌላ ኢየሱስ የተባለውና፥ ባዕድ፤ ቅይጡ ወንጌል የተባለው ዶክሜንተሪ ቪድዮ ቀጣይ ተለቀቀ። በሳምንቱ ቆንስላው አይነኬ ብቻ ሳይሆን አስፈራሪና ዛቻን የሚጠቀምም ሆነ። ባዕድ - ሌላ ኢየሱስ ስለተባለው ዘጋቢ ፊልም የቆንስላው ባለ ሥልጣን፥ የጽ/ቤት ኃላፊ መጋቢ ጌቱ ለማ Pastor Binyam Shitaye Official Channel በተባለው የብንያም ሽታዬ (የአሁኑን አያድርገውና) ዝግጅት ላይ ነው ዛቻም ተናገረ። በዚያ ዘጋቢ ቪድዮ የተሳተፉ፥ 'ሒሳብ ያወራርዳሉ።' አለ።




የቆንስላው ጭምብል ሲላጥ በሚል ባለ ሥልጣኑ ለተናገረው ማስፈራሮና ዛቻ ምላሽ ሰጠሁ። ቪድዮው እዚህ ይገኛል፤

https://www.youtube.com/watch?v=zlgO8Nt4r3E

የቪድዮው ጽሑፉ ከታች ይገኛል።

. . . . .

ለባዕድ 2 - ሌላ ኢየሱስ ዘጋቢ ፊልም የቆንስላው ባለ ሥልጣን ምላሽ

ባዕድ ሌላ ኢየሱስ ከወጣ ዛሬ ሳምንቱ ነው።

በአንድ ሳምንት ውስጥ ስንት ሰዎች አዩት? በሚገርም መልኩ ከፌስቡክም፥ ከቲክቶክ፥ ከቴሌግራም፥ ያለፈው ባዕድ ቅይጡ ወንጌል እንደገና የታየው ተጨምሮ ወደ 200 ሺህ ሰው አይቶታል። ይህ ገራሚ ቁጥር ነው።

አስተያየተኞች በጣም ገንቢ አሳቦችን ለአዘጋጆቹ ልከዋል። አበረታች የምስጋና ቃላት ናቸው። ብዙ ሰዎች፥ ከሌሎች ሃይማኖቶችም ጭምር ስለ ሐሰተኞቹ ማንነትና ስለ ወንጌሉ ቀላል ያልሆነ መረዳትን አግኝተዋል።

የተናደዱና የተቆጡም አሉ። ይህ ዘጋቢ ቪድዮ ለማሟሟቅ የተሠራ አይደለም። እውነተኛው ወንጌል ሰዎችን ያስቆጣል። እውነት ይረብሻል። እውነት ራሷ ታስቆጣለች። ውሸታሞችን ታስቆጣለች፤ ትረብሻለች። ስንድን የተነገረን ወንጌል እኮ ከብዙ ነገሮቻችን ጋር አጣልቶናል። አቀያይሞናል። ከብዙ ኃጢአቶቻችን ጋር አለያይቶናል። ብዙዎቻችን አልወደድነውም ነበር። ቆይቶ ሲገባን ወንጌሉን ወደድነው።

ላልወደዱት ደግሞ ሌላ ወንጌል ተሰበከላቸው። ልዩ ወንጌል። መስቀል አልባ ወንጌል፤ ከኃጢአት ጋር፥ 'እዘለኝ ልዘልህ' የሚጫወት ሌላ ወንጌል። ቅድስናን የሚንቅ ሌላ ወንጌል፤ 'አንዴ ድነሃል፤ መጨቅየት ትችላለህ፤ ቱታህ ነው ጭቃ የነካው እንጂ ሰውነትህ አይደለም' የሚል ኃጢአትን በርካሽ ዋጋ የሚሸጥ ልዩ ወንጌል። ይህንን ሌላ ኢየሱስ ቪድዮ ያዘጋጁልን ወንድሞች በመጀመሪያው ሥራቸው፥ ባዕድ- ቅይጡ ወንጌል ያሉት ይህንን ነው። ባለፈው ዝግጅታቸው ስለ ቅይጥ ወንጌል በዝርዝር ነግረውናል። ልዩ ወንጌል። አሁን ሌላ ኢየሱስን አቅርበውልናል። ይህ መርዝ ሐዋርያው ጳውሎስ ያስጠነቀቀው ስሕተት ነው፤ በ2ቆሮ. ፲፩፥1-4 እንዲህ አለ፤

*በጥቂቱ ሞኝነቴ ብትታገሡኝ መልካም ይሆን ነበር፤ ቢሆንም በእርግጥ ታገሡኝ። በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፥ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።*

እዚህ ክፍል ውስጥ ሌላ ኢየሱስ፥ ልዩ መንፈስ፥ ልዩ ወንጌል የተባሉ ሦስት መርዞች ተጠቅሰዋል። ባይኖሩ ኖሮ ጳውሎስ እነዚህን ባልጠቀሰም ነበር። በሌለ ነገር ሰውን ለምን ያስፈራራል? ለምን ያስደነግጣል? ለምን ያስቆጣል? ጳውሎስ የማስቆጣት ተልእኮ አልተሰጠውም፤ አስፈራሪ ተደርጎ አልተላከም። ወንጌል ሰባኪ ነው። ልዩ ወንጌል ሲሰበክ ግን ዝም አላለም።

ይህም ዘጋቢ ሥራ እንዲያው ለማስቆጣት ሀራራ ያላቸው ወጣቶች የሠሩት አይደለም። ግን አስቆጥቷል። በቪድዮው የተጠቀሱት እና አጃቢዎቻቸውና አንጋቢዎቻቸው ተቆጥተዋል። በዚህ አንድ ሳምንት ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎች አካኪ ዘራፍ ብለዋል። ወደ ፲፰ እና ፲፱ ያህል። ቁጥራቸው ሊጨምር ይችላል። አንዳንዶቹ በበሉበት የሚጮሁ ናቸው። በበሉበትም የጮኹ ናቸው። አንዳንዶቹ የሐሰተኞቹ

ተከፋዮች ናቸው። ይከፈላቸውም አይከፈላቸውም፤ ወዳጆቻቸው ግን አይደሉም። ቢሆኑ ከጥብቅና ይልቅ ጉዳዩን ለባለ ጉዳዩ አቅርበው፥ 'በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ ካልሰጠህ እንደሚሉት ነህ ማለት ነው' ብለው ይሞግቷቸው ነበር።

ለነዚህ ቁጡዎች ለሁሉም መልስ መስጠት አይቻልም። አስፈላጊም አይደለም። አንዳንዶቹ ሐሰተኞች፥ ንስሐ በመግባት ፈንታ፤ 'ስቻለሁ፤ አስቻለሁ' በማለት ፈንታ የጭቃ ጅራፋቸውን የሚያጮሁ ናቸው። ሌላ አይደለም። እነዚህ ተንቀው ወደ ጎን የሚትተዉ ናቸው። አንድ ቀን ወደ ልባቸው እንደሚመለሱና ያሳቱትን ሕዝብ ይቅርታ እንደሚጠይቁ ተስፋ አደርጋለሁ። እነዚህ ልባቸውና ትከሻቸው በብር ያበጠ፥ የኢየሱስ እኩያዎች፥ እነዚህ የወንጌልና የኢየሱስ አሰዳቢዎች፥ እነዚህ መርዝ ጋቺዎች አንድ ቀን ወደ ቀልባቸው ይመለሱ ይሆናል። ያሳቱትን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቁ ይሆናል። ማስጠንቀቃችን ግን ይቀጥላል።

መረሳት የሌለበት ነገር፥ ይህ ዘጋቢ ቪድዮም ሆነ ሌሎች መሰል ነገሮች በሰዎቹ ትምህርቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው እንጂ የሰዎቹ ስብእና ላይ የተነጣጠሩ አይደሉም። የስሕተቱ ትምህርት ላይ ነው ትኩረቱ እንጂ የሰዎቹ ጓዳ አይደለም። ሆኖም አያውቅም። አንዳንድ አላዋቂ ሰነፎች፥ 'እነሱን ከመስበክ ወንጌል ለምን አትሰብኩም? እገሌን፥ እንትናን ከመስበክ ኢየሱስን ለምን አትሰብክም? ምናምን ይላሉ። ሰዎች፥ ወንጌል ነው እየተሰበከ ያለው። ልዩ ወንጌል ልዩ ወንጌል ነው ማለት ወንጌልን መስበክ ነው። ሌላ ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ነው ማለት ኢየሱስን መስበክ ነው። ለነገሩ እነዚህ፥ 'ወንጌል ለምን አትሰብክም? ኢየሱስን ለምን አትሰብክም? የሚሉ ሰዎች ስለ ኢየሱስና ስለ ወንጌል ግድ ተሰምቷቸው ሳይሆን እንቶኔ ስለተነካባቸው ብቻ ነው። እነዚህ ተበሳጭተዋል።

አንዱ ብቻ ላይ ላተኩር እፈልጋለሁ። የቆንስላው የጽ/ቤት ኃላፊ መጋቢ ጌቱ ለማ በተናገረው ላይ ምላሽ እሰጣለሁ። ዝግጅቱን ያቀረበው Pastor Binyam Shitaye Official Channel የተባለው ነው። ከቻላችሁ ተመልከቱት። ከቻላችሁ ያልኩት የ4 ሰዓት ከሩብ ዝግጅት ስለሆነ ነው። 4 ሰዓት ሙሉ ቁጭ ብሎ ስርጭት መሥራት እንኳን ሰውየውን ወንበሩንም የሚያደነዝዝ ይመስለኛል። ከቻላችሁ ቻነሉ ያ ነውና ተመልከቱት። ሁለቱም 'መጋቢ' ተብለው ነው የተጠሩት። በባህላችን፥ በወንጌላውያን አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ወግ መጋቢ የሚባል ሰው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የሚመግብ ሰው ነው። እዚህ የምናያቸው ሁለቱም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሙሉ ጊዜ መጋብያን አይደሉምና መጋቢ የሚለውን ቃል የተጠቀሙት እንደ ማዕረግ ነው ማለት ነው። አንድ ሰው ሻለቃ ወይም ፕሮፌሰር ከተባለ ሁሌም እንደሚጠራበት ማዕረግ ወይም ዱሮ በአገራችን፥ ባላምባራስ፥ ደጃዝማች ወዘተ፥ እንደሚባለው መጋቢንም የዕድሜ ልክ ማዕረግ አድርገውታል ማለት ነው። 'እረኛ የሌለው መንጋና መንጋ የሌለው እረኛ' አለ ጳውሎስ ፈቃዱ። እውነት እኮ ነው። አንዳንድ መጋቢዎች መጋቢዎች ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ መጋቢ ሳይሆኑ ተመጋቢዎች ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ መጋቢም ተመጋቢም ሳይሆኑ ደላላዎች ናቸው። የነዚህን ራሳቸው እስኪነግሩን እንጠብቃለን።

እና እዚህ ላቀርብ የፈለግሁት የ'መጋቢ' ጌቱ ለማን አጸፋ ነው። በእርሱ ምላሽ ላይ መናገር ያስፈለገው አንደኛ፥ ወካይ ስለሆነ ነው። የቆንስላውም በውስጡ የታቀፉት አሳቾችም ወኪል ነው። ሁለተኛ፥ ብዙ ማስፈራሪያዎችንና ዛቻዎችንም የተናገረበት በመሆኑ ነው። እርሱ የተናገረው ክፍል ከጠቅላላው 4 ሰዓት በላይ ውስጥ ወደ 30 ደቂቃ ነው፤ አሁንም ከ30ው ደቂቃም (ሙሉውን 30ውንም ደቂቃ በዚያ ስሙት) ከውስጡ ጥቂት ነገሮችን ብቻ አካፍላለሁ። 5 ወይ ስድስት ነጥቦችን አካፍላለሁ።

1. በመጀመሪያ ይህ ሰው ዘጋቢውን ቪድዮ በሙሉ አላየውም። በተወሰነ መልኩ ብቻ ነው ያየው፤ ይህንንም ራሱ ተናግሮታል።

. . .

እንዳላየው ወይም ስለ ቆንስላው የተነገረውን ጥቂት ደቂቃ ብቻ ያየ በመሆኑ ጠቅላላው አስተያየቱ በቆንስላው ብቻ ላይ ያጠነጠነ ሆኖአል። (ቆንስላው የምለው የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል የሚባለውን ተቋም ነው።) ስለዚህ ቆንስላ ስለምለው ካውንስል ብዙ ቪድዮዎች እና ጽሑፎች አካፍያለሁ፤ በሁሉም ቆንስላ እያልኩ ነው የምጠራው። ለምን እንደዚያ እንደምለውም ከቪድዮዎቹ በአንዱ አብራርቻለሁ። በአጭሩ ቆንስላ የምለው ቆንስላ የአንድ አገር መንግሥት ወኪል ሆኖ በሌላ ግዛት ውስጥ የሚሠራ እንደራሴ በመሆኑ ይህም ቆንስላ በቤተ መንግሥት ውስጥ ተረግዞ ተወልዶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንግሥታዊ የውክልና ሥራ የሚሠራ በመሆኑ ነው። ይህ ቆንስላ በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ታሪክ ውስጥ ጠባሳ ሆኖ የሚኖር ባዕድ አካል ነው።

እና ይህ ሰው ስለ ወንጌሉ ወይም ስለ ሌላው ወንጌል፥ ወይም በቪድዮው ስለቀረበው ስለ ኢየሱስ ወይም ስለ ሌላው ኢየሱስ ሳይሆን ለጥቂት ደቂቃ የተወሳው የቆንስላው ጉዳይ አንገብግቦት የተናገረበት አነጋገር አስተዛዛቢ ስለሆነ ነው የማቀርበው። ምላሽ የሰጠውም በዚህ ዘጋቢ ቪድዮ ውስጥ የተጠቀሱትን የስሕተት ትምህርቶች ያስተማሩት ሰዎች በቆንስላው ውስጥ የታቀፉ በመሆናቸው የውክልና ምላሽ ለመስጠት ይመስላል።

አንድ ጉዳዩ እኔን የተመለከተ ነው የሚል ሰው፥ በወግ እንኳ ስላላየው፥ ስላልሰማው ነገር መልስና አስተያየት ሲሰጥ ያሳፍራል። ለዚያውም የቆንስላው የጽ/ቤት ኃላፊ የሆነ ሰው፥ በዚያ ማዕረግ የሚገኝ ባለ ሥልጣን፥ ስላላየው ነገር መናገሩ ነውር ነው። ቢያንስ እስኪያይ ድረስ እንኳ ዝም ቢል መልካም ነበር። ስላላየው ነገር ሐተታና ፍቺና ማብራሪያና ትችት ከሚያቀርብ። ይህ ምን እንደሚያሳይ አላውቅም። ደንታቢስነት? አላዋቂነት? ንቀት? ምናልባት ሁሉም። ብቻ ያሳፍራል።

2. ጠቅላላው ንግግር ስለ ቆንስላው ነው። ዘጋቢው ቪድዮ ደግሞ ትኩረቱ ቆንስላው አይደለም፤ ከርእሱ ጀምሮ ቆንስላው አይደለም። ከሁለት ሰዓት በላይ የፈጀው ቪድዮ ውስጥ ስለ ቆንስላው የተነገረው በጣም ጥቂት ደቂቃዎች ነው። ለዚያውም በቪድዮው

ውስጥ የተጠቀሱት የስሕተት ትምህርቶች በቆንስላው በታቀፉት ሰዎች የተነገሩ ስሕተቶች በመሆናቸው ነው።

ስለ ቆንስላው መናገር የሚያስቀጣ፥ የሚያስወነጅል ሆኖ ቀርቧል። መቸም በዘመናዊው የዜግነት ፖለቲካ በሚቀነቀንበት አገር የአፈና ድንፋታ መደንፋት ያሳፍራል። የቆንስላውን ሎጎ ማሳየት ወይም ቆንስላውን ይወክላሉ የተባሉ ሰዎችን ምስል ለማሳየት ማስፈቀድ የኖረበት በየትኛው ሕግ መሆኑን ቢጠቅስ ጥሩ ነበር። በአምባ ገነን አገር ካልሆነ በቀር፥ እንኳን አንድ ድርጅት እና የድርጅት መሪዎች፥ የአገር መሪዎችም እኮ በዜናች ሊጠየቁ፥ ፎቶአቸው ተለጥፎ ሊነገርባቸው፥ ሊጻፍባቸው ይቻላል። ውሸት ከሆነ ሊጠየቁ ይችላሉ። እውነት ከሆነ ግን ፎቶ ስለለጠፉ፥ ምልክት ስለለጠፉ አይታሰሩም፤ አይቀጡም። ፎቶ ለመለጠፍም ማስፈቀድ የለባቸውም። አሁን እኔ የጌቱ ለማን ፎቶ ልለጥፍ ፍቀድልኝ ብል ይፈቅድልኛል? አይፈቅድም። ከቢንያም ጋር ካደረግኸውን ቃለ ምልልስ ድምጽህን በከፊል ልጠቀም ፍቀድልኝ ብል ይፈቅድልኛል? አይፈቅድልኝም።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ፈቃድ ስላላገኘሁ ምንም ነገር መለጠፍም መናገርም አልችልም ማለት ነው። ስለ ሐሰተኞቹም ሐሰተኛነት ፎቶ መለጠፍም፥ የተናገሩትን ስሕተትም መለጠፍና መግለጥ አልችልም ማለት ነው። ይህንን ነው መጋቢ ጌቱ እያለን ያለው። አፋችሁን ዝጉ፤ አትናገሩ፤ ሳታስፈቅዱና እኛም ሳንፈቅድ ምንም አትለጥፉ።

3. ስለ ራሱ ስምና ድርጅት እጅግ እየተጠነቀቀ ይህንን ያላየውን ዘጋቢ ቪድዮ የሠሩትን ልጆች ግን ዘልዝሏቸዋል። ያውም በዱልዱም ቢላዋ። ልጆቹን የመንደር ልጆች ወይም ወሬኞች ብሏቸዋል፤ ለገንዘብ የሚሠሩ አድርጓቸዋል፤ ከውጪ ገንዘብ ወይም ፈንድ የሚሰበሰብላቸው ብሏቸዋል። ስለ ገንዘቡ አንድ ሁለት ነገር ልበል፤

ከውጪ ያለው ምናልባት ባለፈውና በዚህ ቪድዮ ሁለት ነጭ ወንድሞች ስለታዩ ይሆናል። እነዚህ ወንድሞች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩና የሚያገለግሉ ወንድሞች ናቸው። የወንጌል አገልጋዮች ናቸው። ኑሮአቸው ምን እንደሚመስል ማወቅ ከፈለገ መፈተሽ ይችላል።

ሌላው የተሰበሰበ ገንዘብ ስለተባለው ነገር የሰማውን የተናገረው ነው። ልጆቹ የመጀመሪያውን ቪድዮ (ባዕድ - ቅይጡ ወንጌል የተባለውን ቪድዮ) ከሠሩ በኋላ ለማበረታቻ እንዲሆናቸው ጥቂት የኦዲዮቪዧል ዕቃዎች ለመግዛት የጎፈንድሚ አካውንት ከፍቼ ለምኜላቸው ነበር። እኔው ራሴ ነኝ የለመንኩላቸው። ቪድዮውን ያዩ ወገኖች አዋጡና ዕቃውን የሚገዛላቸው ጥቂት ገንዘብ ተገኘላቸው፤ ገዙበት። ገንዘቡ ደግሞ የመጋቢ ጌቱ ለማ የአንድ ወር ወይም የአንድ ወር ተኩል ደመወዝና አበል ነው። ከዚያ አይበልጥም። የላክሁበት ደረሰኝ አጠገቤ ቢኖር መጠኑን በትክክል እናገር ነበር።

እነዚህን ልጆች አውቃቸዋለሁ፤ ገንዘብ አጀንዳቸው አይደለም። ይህንን ወይም የቀደመውን ቪድዮም የሠሩት ተከፍሏቸው አይደለም። ሌላው ቀርቶ ይህንን አሁን

የለቀቁትን ቪድዮ ራሱን 'monetize አድርጉት፤ ካስፈለገ፥ በኔ ገጽ ልለጥፈውና ከማስታወቂያ የሚገኘው ገንዘብ ወደናንተ ይላክላችሁ፤' ብያቸው ነበር። ፈቃደኛ አልነበሩም። መጋቢ ጌቱ ለማ እንደገመታቸው እነዚህ ልጆች እና ቃለ ምልልስ ያደረጉላቸው ወጣት አገልጋዮች በገንዘብ የተገዙ ርካሽ ካድሬዎች አይደሉም። ምናልባት መጋቢው አገልግሎትንና ሥራን በአንድ መስፈሪያ ስለሚሰፍረው ነው መሰለኝ ልጆቹን በዚህ መልክ የሰፈራቸው። የለካቸው በገንዘብ ነው። ገንዘብ ገንዘብ የሚሉ ሰዎች ከራሳቸው ምኞት አንጻር ነገሮችን የሚመለከቱ ሰዎች ናቸው። መለኪያቸውና ግምታቸው ይህ ብቻ ነው። ይህ አስቀያሚ ግምት ነው። ስገምተው እርሱም ራሱ የሚሠራውን የሚሠራው ረብጣ ብር ስለሚከፈለው ብቻ ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ የአገልጋይ ሳይሆን የሞያተኛ ባህርይ ነው።

4. የኔ ድርጅት ስም ተጠራ ብሎ፥ በአንድ ወቅት መሪ የነበረ ሰው ፎቶ ተለጠፈ ብሎ፥ የድርጅቱ ዓርማ ተለጠፈ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ያለው ይህ ሰው፥ ኤግስት የተባለውን ትልቅ ሴሚነሪ በዚህ መልኩ፥ ለአንድ መንፈሳዊ ተቋም በማይመጥን ቋንቋ ሲያዋርደው የራሱን ትምህርት እንድጠይቅ ግድ ሆኖብኛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን ዋጋና ክብር ያውቃል? ዓላማና ተግባራቸውንስ ያውቃል? የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች መሪዎቻቸውን መውቀስ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? ስሕተት ሲያዩ በይሉኝታ ዝም ብለው ያልፋሉ ወይስ ይጋፈጣሉ? ለመሆኑ ይህ ሰው ራሱ መጋቢ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ተምሯል? ይመስለኛል ተምሯል። ታዲያ ያስተማሩት ሰዎች የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች የሚሉትን ነገር ነው ያስተማሩት? ወይስ ቃሉን? ከኤግስትስ ምንድር ነው የጠበቀው?

በተቀረው ይህ ሰው መጋቢ ጌቱ ከተናገራቸው ነገሮች ውስጥ አንድም የቪድዮውን ዋና አሳብ ወይም ይዘት የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ነገር አልተናገረም። የቪድዮው ዋና ይዘት ቆንስላው 3ሌላ ኢየሱስ የሚሰብኩ ሰዎችና የስብከታቸው ምንጭና አካሄድ ነው። እርሱ የተናገረው ደግሞ እንደ ነገረ ፈጅ ጠበቃ ስለ ቆንስላውና ቆንስላው ብቻ ነው። እንዳላየ ባይናገርም እንኳ አለማየቱን ይህ ብቻውን ይገልጠዋል። ይህንን እንዲናገር የጎተጎተው ደግሞ ጠያቂው ነው። የጠያቂው አጀንዳ ምን መሆኑን አላውቅም፤ አስፈላጊም አይመስለኝም።

በነገራችን ላይ፥ ይህ ሥራ ከኤግስት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ምናልባት እዚያ የሚያስተምር ወይም የሚሠራ አንድ ሰው ይኖር ይሆናል። እንዲያው ቢኖሩስ? እዚያ ቢሠሩስ? እነዚህን ሰዎች፥ 'እንደዚህ አትበሉ፤ እንደዚህ በሉ፤ እንደዚህ አታስቡ፤ እንደዚህ ብቻ አስቡ' የሚል ደፋር ከወዴት ተገኘ? እንኳን የምሑራን መንደር፥ 'ካፌ ተቀምጠው፥ ምናምን' ያላቸው ሰዎችም፥ 'እንደዚህ አስቡ' አይባሉም። ነውር ነው።

ይህንን ቪድዮ ካዘጋጁት ልጆች ውስጥ አንዳቸውም ኤግስት ገብተው አልተማሩም። ይህንን ጉዳይ አንሥቼ ከአዘጋጆቹ አንዱን ወንድም ጠይቄው የመለሰልኝ ይህ ነው፤ ላንብበው፤ "ያዘጋጀነው 5 ተራ ሰዎች ነን። ማናችንም EGST አልተማርንም። የተሳተፉት ሰዎች፣ ከመሳተፍ (INTERVIEW ከመደረግ)፣ አይቶ አስተያየት

ከመስጠት እና ከማስተዋወቅ የዘለለ አንዳችም ተሳትፎ የላቸውም።" ብሏል። ይኸው ነው። የኤግስትን ስም እንደ ተቋም ለማጥፋት ሌላ አጀንዳ ካልኖረ በቀር ምንም ትርጉም የለውም።

5. ዛቻው ነው። በቅርብ እናወራርዳለን ነው ያለው። በቅርብ እናወራርዳለን የሚል የዛቻ ቃል የሰማሁት ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ በተለይም፥ የአማራን ሕዝብ፥ 'ሂሳብ እናወራርዳለን' ያለ ጊዜ ነው። እየዛተ ነው ይህ ሰው? ሐሰት አይገለጥም ማለት ነው? ሌላው ኢየሱስ ሲሰበክ፥ 'ይህ ሌላ ኢየሱስ ነው!' አይባልም ማለት ነው? ካውንስሉ፥ 'ቆንስላ ነው፤ ፈቃድ መስጠት የመንግሥት ኃላፊነት ሲሆን የመንግሥት ሥራ በውክልና ተቀብሎ ፈቃድ ሰጪ ሆኖ እየሠራ ነው!' አይባልም ማለት ነው? በምካቴ ክርስትና ዘርፍ የሚሠሩ አገልጋዮች ፈቃድ ለማውጣት ቢጠይቁ ያለ ጥርጥር አይፈቀድላቸውም ማለት ነው። ሂሳብ እናወራርዳለን የሚል ጉልበተኛ እንዴት አድርጎ ነው ለሚወቅሱት ፈቃድ የሚሰጠው?

ፈቃድ ለመስጠት ራሱ ከቢሮ ውጪ በዋጋ የሚደራደሩ መሰሪዎች ያሉበት ድርጅት ሆኗል እኮ ቆንስላው። ፈቃድ ሊያወጡ የሞከሩ ጓደኞቼ ናቸው የነገሩኝ። አንድ ቀን በግልጽ እናገረዋለሁ። እኔ አሁን ኢትዮጵያ ለማገልገል ፈቃድ ላውጣ ብል መልሱን መገመት እችላለሁ። ምናልባት፥ 'ይኸው ከጠላቶቻችን ለአንዱ ፈቃድ ሰጠን' ሊሉ ያለ ምንም ቢሮክራሲ ሊሰጡኝም ይችላሉ። ፖለቲካ እኮ ጉደኛ ነው። ብቻ ሂሳብ የማወራረዱን የዛቻ ነገር ያዙልኝ። በቅርብ ተብሏልና በቅርብ በቪድዮው አዘጋጆች ወይም በቪድዮው ላይ ቃለ ምልልስ የተደረገላቸው ወገኖች ቢታሠሩ ወይም ቢሰወሩ ማን እንዳደረገው መገመት እንችላለን። ካውንስሉ እኮ ቆንስላ ነው። የመንግሥት ክንፍ ነው። ምናልባት ታጣቂዎችም ሊኖሩት ይችሉ ይሆናል። እንዲህ ያለ ዛቻ መንፈሳዊ ነኝ ከሚል ተቋም ሲወጣ ምን ሊባል ይቻላል?

6. ካውንስል ነን ብለው ድርጅት የሆኑ፥ ስማችንን የወሰዱ፥ ወዘተ ያለው፥ ይህንን ያሉ መኖራቸውን አላውቅም። ምናልባት ተቀናቃኝ አካል መጣ ማለቱ ይሆን አላውቅም። ይህንን ከዘጋቢ ቪድዮው ጋር ለምን እንዳገናኘውም አላውቅም። ሌሎችም ጥቂት ይህን የመሰሉ ነጥቦች አሉ። ስለ ዘጋቢው ቪድዮ ይዘት እንዳልኩት ምንም ነገር አልተናገረም። እርሱን ያሳመመው ቆንስላው ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን መጠቀሱ ነው። ቆንስላውማ ቀደም ሲል እንዳልኩት ነው፤ መጠቀስማ አለበት እንጂ። በሐሰተኞቹ የገንዘብ ድጋፍና ድጎማም ጭምር የቆመ እኮ ነው። ስለዚህ ስለእነርሱ ሲነገር ቢያመው ምን ይደንቃል? ሁሉም የተናገራቸው ነገሮች ስለ ቆንስላውና ቆንስላው ብቻ ነው። እና ይበቃል።

October 10, 2022

ባለፈው ቪድዮ ቆንስላው ሂሳብ ያወራርዳሉ ማለቱን ተናግሬአለሁ። 'ሂሳብ ያወራርዳሉ' ያለውን ባለ ሥልጣን ያቀረበው ቢንያም ሽታዬ ደግሞ የለጠፍኩትን ቪድዮ ካላነሣህ ብሎ ዝቶብኛል። ከጻፈልኝና ከላከልኝ ውስጥ . . .

" . . . እሰከ ነገ 6 ሰዓት ያወራከውን እንቶ ፈንቶ ይቅርታ ጠይቀህ ቪዲዬውን ካላወረድክ ብዙ የአንተ ሰነዶች እጄ ላይ ሰላሉ ለሰብዕናህ ኖረሀቸው ያለፍካቸው ራሰህንም ሆነ ቤተሰብህን ሰለሚጎዱ እድል እሰጥሀለው . . . ዛሬ ግን በአንተ ቪዲዬ ላይ ሰለምሰራ ከቻልክ ገብተህ ማውራት እንችላለን . . . ። ዘሌ ነካኸኝ እንግዲህ ነገ ማታ ቻለው አገልግሎት እና ህይወትህ ብዬ በደንብ እሰራለው ።ቻለው!!!"

ዘላለም ነኝ።




ብንያም ሽታዬም ልክ ባለ ሥልጣኑ እንደዛተው ዓይነት ዛቻና ማስፈራሮ ነው ያቀረበልኝ። ያንን (ከላይ ያካፈልኩትን) እንዳወርድ ነው ሊያስገድደኝ፥ ሊያስፈራራኝና ሊደራደር የሞከረው። እኔ እንዲያውም የራሱን ማስታወቂያም ነው በገጼ የለጠፍኩለት። እኔን ሊያሸማቅቅ የሚችለውን አደረገ። ቪድዮው ግን አልወረደም።

በማሸማቀቅ ሊሠሩ ይችላሉ፤ በመሸማቀቅ ግን የምንሠራ አይደለንም።

October 16, 2022

ታሪካዊ ስሕተታችን።

ቆንስላው ታሪካዊ ስሕተታችን ነው። ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና የሚሟገቱትን የሚያሳድድ ከሆነ በእርግጥም ታሪካዊ ስሕተታችን ሆኖ ይኖራል።

ቆንስላው በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ታሪክ ውስጥ ጥቁር ንቅሳት፥ ጭንቁርና ነቀርሳ ሆኖ ይኖራል።

ሆኖ #ይኖራል።

ዘላለም ነኝ።



November 12, 2022




የቆንስላውን የደቡብ አፍሪቃ ዘመቻ እቃወማለሁ።

ደቡብ አፍሪቃ የሐሰተኞች መጋጫና መፈንጫ ሆና ኖራለች። ቆንስላው በአገር ውስጥ ከገባበት ማጥ ሳይወጣ ቅርጫ ለመቃረጥ ወደ ደቡብ አፍሪቃ መምጣቱን አጥብቀው ከሚቃወሙት ነኝ። የምትቃወሙ ይህንን ለሌሎች አካፍሉ።

ዘላለም ነኝ።

. . . . .

ቆንስላው ወደ ክልሎች እና ወደ አገሮችም መውጣት ጀመረ። መሪዎችም በዲፕሎማቲክ ፓስፖርት መጓጓዝ ጀመሩ። ደቡብ አፍሪቃ በነበሩባቸው ቀናት ደግሞ ከታወቀ ሐሰተኛ ነቢይ ጋር ነበር ተቆራኝተው ይዞሩ የነበሩት።

December 17, 2022

ለካስ አይባልም!

ቆንስላው ሆይ፡ ጥንቃቄ ጥሩ ነው። ነገሩ ማስጠንቀቂያ ሲመስልና የፖለቲካ ጃኬት ሲለብስ ግን ያጠይቃል።



የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Gospel Believer Churches Council

ጥንቃቄ ይደረግ!

በሰሞኑ ወቅታዊ ዜና ሆኖ በማህበራዊ ሚዲያ በሚመላለሱ ጉዳዮች ዙሪያ ጥንቃቄ እንዲደረግ እያልን ሀገራችንን ኢትዮጵያ ከምን ግዜውም በላይ ሕዝቦቿ ለሰላምና አንድነት የሚያስከፍለውን ዋጋ በመክፈል በጋራ መቆም በሚያስፈልግበት በዚህ ወቅት የሁከትና ብጥብጥ አጀንዳ አቀባዮች ከዚህ ቀደም ተሞክሮ ባልተሳካበት የሃይማኖት ተቋማትን እርስ በእርስ የማጋጨት [illegible] እየተስተዋለ ይገኛል ።
ሲጀመር እናት ቤተ ክርስቲያናችን [illegible] ዋህዶ የሁላችንም ናት ።
ቤተ ክርስቲያናችን ኦርቶዶክ ተዋህዶ ፊደል አስቆጥራ [illegible] ምህርትን አስተምራ ሀገር የገነባች ክርስትናን እንደ ሀገር አስጡብቃ የቆየች በመሆ[illegible] ቀዳሚነትና የአንጋፋነት ክብር ይገባታል ። በመሆኑም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ [illegible] ክርስቲያን የሁላችንም ናት ስል በምክንያትነት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ። [illegible] ሁነት እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ግዜ የሐይማኖት አስተማሪዎች በሚያደርጉት [illegible] ውርወራ በሀይማኖት ተቋማቶች መካከል እየፈጠረ ያለው ክፍተት አደ[illegible] ከቀን ወደ ቀን ጥላቻን እያስፋፋ በመሆኑ የማይደገፍ ከመሆኑም በላይ ለቤተ እ[illegible]ም ለሀገርምለምዕመናኑም ከሁከትና ከጸብ ውጭ ምንም አይነት ፋይዳ እንደሌለው [illegible] ወቅ ይገባል ።
ከሰሞኑ በማህበራዊ ሚዲያዎች እየተሰራጨ ባለው ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት እየተነጋገሩበት በመሆኑ ከሁለቱም ወገ[illegible]ት የምታቀጣጥሉና ጸብ እንዲነሳ በማህበራዊ ሚዲያ የምታሰራጩ አካ[illegible]ሁን በፍጥነት ልትሰበስቡ ይገባል እያልኩ መንግስት እንደዚህ አይነት ጸብ ቀስቃሽ [illegible]ት በማሰራጨት በተሰማሩ አካላት ላይ ጥብቅ ክትትል ማድረግ የሚገባው ሲሆን የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ምዕመናንም አገራችን ኢትዮጵያ ከቤተ ክርስቲያን የምትጠብቀው ሁከትና ጸብ ሳይሆን ሰላምንና የሰላምን ቃል ብቻ ስለሆነ ባላችሁበት ቦታ ሁሉ ለሁከተኞች ተባባሪ ባለመሆን ክርስቲያናዊ ተግባራችሁን እንድትወጡ እጠይቃለሁ ።

ፓስተር ጌትነት ለማ -
የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተክርስቲያናት ካውንስል ጽ/ቤት ሃላፊ

1. በመጀመሪያ፥ ለመሆኑ ስለ ገድለ ተክሌ የተጻፈውን አንብበውና ተረድተው ነው?

2. በማኅበራዊ ሚድያ ለሚጽፉት ሰዎች ልምጭ የሚያሳዩት አስቀድሞ የተናገረውን ሰው ተናግረውት ነው? ዮናታንን ይቅርታ እንዲጠይቅ 'ሊያስገድዱ' ማለት ይቻላል ሞክረው ነበር፤ አልተሳካላቸውም። ግን እውነት ይቅርታ እንዲጠይቅ የፈለጉት ለወንጌል ነው? ወይስ ለፖለቲካ ግብይት? ደግሞስ አስቀድሞ ራሱ ዮናታን የቆንስላው አባል ሆኖ ሳለ የሚያስተምራቸውን ኑ'ፋ^ቄ-ዎች ሊያስጥሉትስ ሙከራ አድርገው ኖሯል? ወይስ ያ ችግር የለበትም?

3. ቀጥሎስ፡ ይህን ስበክ፤ ያንን አትስበክ ሊሉ ነው ማለት ነው?

4. ይልቅስ በተባለው መጽሐፍ (ገድለ ተክሌ) ላይ እስኪ ነገሩ እንዲሁ ይሆንን ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን ይመረምሩ የነበሩትን የቀደሙትን የቤርያን ሰዎች ታሪክ ያውቁ ይሆን?

5. ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሁላችንም ናት ማለት ምን ማለት ነው? በምክንያት ነው ተብሏል፤ ምክንያቱስ?

6. በመጨረሻ ስለ ሁከትና ጸብ ተነሥቷል። አንድ ከወንጌል በተቃራኒ የሚሄድ መጽሐፍን አውግዞ መናገር ነገሩ ወደ ጸብና ሁከት እንዲሄድ የሚፈልጉ ፖለቲከኞች ሊኖሩ ይችላሉ። ሃይማኖተኞች አላልኩም፤ ፖለቲከኞች። ፖለቲከኞች ያልኩት ሃይማኖተኞች ከዚህ በፊት በጉዳዮቹ ብዙ ስላሉና ሁከትና ጸብ ስላልተነሣ ነው። ሁከትና ጸብ ፈላጊዎች ደግሞ ምክንያት አይፈልጉም። ደግሞም አንዱ ሌላውን ሲነቅፍ ይህ የመጀመሪያ አይደለም፤ የመጨረሻም አይሆንም።

በጸብና ሁከት ሰበብ ነፃነትን የመገደብ አካሄድ ከሆነ በግልጽ መንገሩ ይሻላል። ገድለ ተክሌንማ ከዚያችው ቤተ ክርስቲያን የሆኑት መምህር ጌታቸው በ1995 በርብረው አሳይተውናል እኮ። ከገጽ 37 ጀምሮ ተመልከቱት። እኔም ገድለ ተክሌን ያወቅሁት ያኔ ነበር። ታዲያ ዛሬ ያንኑ ቢባል ምን ሰማይ ወደቀ? ደግሞስ ለፖለቲካ መቻቻል ሲባል ስሕተትን ስሕተት ማለት ሊከለከል ነው?

7. ቆንስላው በቆንስላው ውስጥ ያሉትን ጉድፎች ቢያጠራ ልል አሰብኩና ለካስ አይባልም።

ዘላለም ነኝ።

December 18, 2022

# ቆንስላውን ቆንስላ የምለው በምክንያት ነው።

ቆንስላውን፥ 'ቆንስላ' የምለው በምክንያት ነው።

ቤተ መንግሥት ውስጥ ተረግዞ በመወለዱ ብቻ አይደለም።

የቆንስላው መሪ የቆንስላውም የቤተ እምነቱም መሪ ሆኖ ከደንብ ውጪ የፓርቲ ተወዳዳሪና ተመራጭ ስለሆነ ብቻም አይደለም።

የመንግሥትን የፈቃድ ሰጪነት ተግባር ተቀብሎ የመንግሥት ወኪል ሆኖ የፈቃድ ሰጪ አካል ስለሆነ ብቻ አይደለም።

የስሕተት ትምህርትን የሚቃወም ቪድዮ ሲወጣ ባዘጋጁት ላይ በመዛቱና በማስፈራራቱ ብቻ አይደለም።

ኤክዩሜኒካዊ በመሆኑም ጭምር ነው።

ቆንስላው አሳቾችን፥ የሐሰት ነቢያትንና የሐሰት ሐዋርያትን ማቀፉ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ፥ አሁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን፥ 'እናት ቤተ 'ክርስቲያናችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሁላችንም ናት። ቤተ ክርስቲያናችን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ . . .' በማለቱ የኢኦተቤ/ክ የቆንስላው አባል መሆኗን ያልነገረን ወይም የደበቀን ይመስላል። ፖለቲካ ካልሆነ፥ እናታችን ማለትስ ምን ለማለት ነው?

‘ጥንቃቄ ይደረግ’ በሚል ርእስ ትናንት የተሰጠው መግለጫ ወይም ማሳሰቢያ በኢኦተቤ/ክ ቅቡል የሆኑ መጻሕፍት (ገድለ ተክለ ሃይማኖት እና ተአምረ ማርያም) ስለተዘለፈ ይቅርታ እንዲጠየቅ የመደራደርና የማስገደድ አካሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ፍጹም ፖለቲካዊ መሆኑ ከግልጽም በላይ ነው።

እነዚህን መጻሕፍት ያወገዙና ስሕተታቸውን የገለጡ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርም የተጣሉ መሆናቸውን ያሳዩ አያሌ ናቸውና እነዚህን ሁሉ ቆንስላው እያደነ ለይቅርታ ሊያስገድዳቸው ነው ማለት ነው? ስለ ሌሎች ኑ*ፋ-ቄዎች መጣጥፎችና መጽሐፎች የጻፉ ወገኖችስ ክስ ሊከፈትባቸው ነውን? በውኑ የሕሊና፥ የመጻፍ፥ የመናገር፥ የመስበክ ነጻነት ሊገደብ ነውን? ቆንስላው ትናንት ይህን ካደረገ፥ ነገስ?

ቆንስላውን፥ 'ቆንስላ' የምለው በምክንያት ነው።

ዘላለም ነኝ።

July 11, 2023

በሉልን።




የመለስ ቀለስ ችግር ነው ይህንን ያስባለኝ።

September 28, 2023

ቆንስላው ቆስሏል።



የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Gospel Believer Churches Council

ለኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተክርስቲያናት ካውንስል አባላት:-

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን እያልን ከገንዘብ ማጭበርበር ልምምድ ጋር ስሙ በከፍተኛ ደረጃ የሚነሳና በአልጀዚራ ዜና አውታር ጭምር ዶክሜንተሪ ፊልም ተሰርቶ በአለም ሁሉ የተሰራጨበት UEBERT ANGLE / PROPHATE ANGLE የተባለ ሀሰተኛ ነቢይ ተጋብዞ ሰሞኑን አዲስ አበባ መግባቱን ከተለያዩ ምንጮች መረዳት ተችሎአል።

ስለዚህ የካውንስሉ አባል ቤተእምነቶች፣ ህብረቶችና አጋር ሚኒስትሪዎች እና የየተቋማቱ አባል ምዕመናን ሁሉ በዚህ ሰው አማካይነት በሚደረገው የስህተት አስተምህሮና ሀሰተኛ ልምምድ እንድትጠበቁና ራሳችሁንና የክርስቶስን መንጋ እንድትታደጉ በአንክሮ እያሳሰብን ስለ ግለሰቡ ስለመጣበት አገልግሎትም ሆነ ስለሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ቢሮ የማያውቅ እና የማይወክል መሆኑን ማሳወቅ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል
Ethiopian Gospel Believer Churches Council

እንዴት ነው፤ 'ተጠንቀቁ! ኤንጅል ኡበርት አጭበርባሪ ነው።' ብሎ መልሶ የለጠፉትን ማስጠንቀቂያ ማንሣት?

እንግሊዝኛ የሚያርምላቸውን ዛሬም አላገኙም። ኤንጅልን ANGLE ፕሮፌትን PROPHATE ብለው ሲጽፉ ያሸማቅቃሉ። ምናልባት ያነሡት ስሜንና ማዕረጌን ካላስተካከላችሁ ብሏቸው ይሆናል።

ይህ ሰው ቱጃር ነው። የቆንስላውን የ3 ዓመት ወጪ በአንድ ጣቱ ፈርሞ መዝጋት ይችላል።

ግን አሳች ነው። በእርግጥ፥ ዓለም አቀፍ አጭበርባሪም ነው። ዓለማውያን የዜና አውታሮችም አውቀውታል። ክርስቲያኖችማ እንዴታ!? በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች ምን እንደሚሉ መስማት ይዘገንናል። ለነገሩ ሁሉም ዘግናኞችና ዘጋኞች ናቸው።

ጋባዡን አቅፈው፥ ተጋባዡን ገፍተው መሥራት ግን ከቆንስላው በቀር ማንም ማድረግ እንደማይችል ቀድሞም የተረጋገጠ ነው፤ አሁን ባሰበት።

ዘላለም ነኝ።

. . . . .

ይህ ተጋባዡን ኡበርትን አውግዞ ጋባዡን የቆንስላውን አባል ሐሰተኛ ነቢይ ሚራክል ተካን ያላወገዘበት አካሄድ በጣም አስገራሚ ነው። ግን የሚጠበቅ ነው።

በዚሁ ሰሞን ጨምሬ ያልኩት አለኝ።

September 29, 2023




ድመት እየመነኮሰች ወይስ መነኩሴዋ ድመት እየሆነች?

ጋባዡ ሳለ ተጋባዡን ማውገዝ ምን ይሉት ፈሊጥ ነው?

'ሰሞኑን አዲስ አበባ መግባቱን ከተለያዩ ምንጮች መረዳት ተችሎአል።' አባላቸው የሆነው ዋናው ምንጭ እና ጋባዡ እያለ ለምን ከተለያዩ ምንጮች መረዳት ተቻለ?

የመግለጫውና የማስጠንቀቂያው ጋጋታ ፋይዳው ምንድር ነው?

ኡብርት ከገንዘብ ማጭበርበር ልምምድ ጋር ስሙ በከፍተኛ ደረጃ መነሣቱን ካወቁ ምነው ወደ በረታቸው ሲገባ ፈቀዱለት?

ከዚህ በፊት ሐሰተኛው ሐዋርያ ነኝ ባይ ቡሺሪ መጥቶ ምን ሠርቶ ነበር የሄደው?

ይህኛውስ ምን እየረጨ ነው?

በእውነቱ ድመት እየመነኮሰች ሳይሆን መነኩሴዋ ድመት እየሆነች ናት!!

ዘላለም ነኝ።

December 26, 2023




ለራሴ ለማስታወስ ነው። አንዳንዴ እረሳለሁ። እኛ ልዩ ሕዝብ ነን።

አቃፊ ከመሆናችን የተነሣ ስንናከስም ተቃቅፈን የምንናከስ ልዩ ሕዝብ ነን።

የአንድና ብቸኛው ጎሰኛ ፌዴራሊዝም ብቸኛ መገኛ ሕዝብ ነን።

በማንም ቅኝ ገዥ ያልተገዛን፥ ራሳችንን ግን ገበያም በሌለበት በቅናሽ የምንሸጥ ምርጥ ሕዝብ ነን።

ጠንቋዮችና መተተኞች፥ 'ወንጌል አማኞች' ተብለው ፈቃድ የሚያገኙባት አገር ብቸኛ ሕዝብ ነን።

'የብሉይ ኪዳን ታቦትና የአዲስ ኪዳን መስቀል ኦርጅናሌው አለን' ብለን፥ 'አሳዩን' ስንባል 'ትቀሰፉላችሁ' የምንል መቅሰፍት ተከላካይ ሕዝብ ነን።

የአዲሱ ዘመን ሃይማኖት በመንግሥት እስፖንሰር የሚደረግባት አገር ያለችን ዘመን ቀደም ሕዝብ ነን።

ትሕትና አናታችን ላይ የወጣ እብሪተኞች ሞልተን የፈሰስንበት አገር ሕዝብ ነን።

98%አችን ተመራጭ ያልሆንን የፓርላማ አባላት የሆንንባት ነፃ አገር ሕዝብ ነን።

ሐሰተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ ሐዋርያትን ከወንጌላውያን ጋር ቀይጦ የሚያቅፍ ቆንስላ ያለን ብርቅዬ ሕዝብ ነን።

እኛ ልዩ ሕዝብ ነን።

ዘላለም ነኝ።

December 26, 2023




## በወንጌላውያን አማኞች መካከል (በቆንስላው) አንድነት ልንፈጥር አይቻልም ወይ? ሐሰተኞች የምትላቸውን ቀርበህ አናግረህ ታውቃለህ?

ከጥያቄዎች፤ ትናንት በለጠፍኩት ልጣፍ ላይ ከቀረቡት አስተያየቶች አንዱ ጥያቄ ነው። ከታች ያለው ጥያቄ። እዚያ በትንሹ ከመለስኩት በኋላ የሌሎችም ጥያቄ ሊሆን ስለሚችል ለብቻው ትንሽ ሰፋ አድርጌ ልመልሰው ብዬ እዚህ አቅርቤዋለሁ።

ሁለት ጥያቄዎች አሉኝ ጋሽ ዘሌ ለአንተ ፡-

1) ለጊዜው ፌደራልዝሙ ይቆይና በወንጌላውያን አማኞች መካከል (በቆንስላው) ግን ቢያንስ Major በሆኑ አስተምህሮዎች እና በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙርያ እንዳው ከልብ ብንመካከር አንድነት ልናመጣ አንችልም ???

2) ሀሰተኞች ያልካቸውን ነብያት በMedia ሳይሆን በግል በonlineም ሆነ በአካል ፍቅር በተሞላበት መንገድ ልትነግራቸው ምን ያህል ጥረት አድርገሃል ?? አመሰግናለሁ ! ማወቅ ፈልጌ ነው ! Dereje Abriham

. . .

ደሬ፥ ይህ የአንተ ብቻ ሳይሆን ከልብም፥ በሽሙጥም ተደጋግሞ የተጠየቀና የመለስኩበትም የብዙዎች ጥያቄ ስለሆነና ወደ ፊትም ስለሚሆን፥ በገጼ ከሚቀርቡልኝ ብዙ ጥያቄዎች እንደ አንዱ አድርጌ መልስ በመስጠት አካፍለዋለሁ። ሁለቱንም እመልሳቸዋለሁ።

1) የመጀመሪያው ጥያቄ ስለ አንድነት ነው። "በወንጌላውያን አማኞች መካከል (በቆንስላው) ግን ቢያንስ Major በሆኑ አስተምህሮዎች እና በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙርያ እንዳው ከልብ ብንመካከር አንድነት ልናመጣ አንችልም?" ብለሃል። ብዙዎቻችን ኅብረት፥ አንድነት ጠቃሚ እንደሆነ ብቻ እናስባለን። አንድነት ልናመጣ አንችልም ወይ? ነው ጥያቄው። እንችላለን። ሌላው ቀርቶ ከሐሳውያን ጋርም አንድነት ልናመጣ እንችላለን፤ የውሸት አንድነት። ልክ አሁን እንዳለው የመሰለ የቆንስላው አንድነት። ያ ግን #አንዳችነት እንጂ አንድነት አይደለም። መሰባሰብ፥ መከማቸት፥ መደመር፥ መጨመር፥ ብዙ መሆን በራሱ ጥሩና ትክክል ይመስለናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንድነት እንደሚነግረን ሁሉ ስለ መለየትም እንደሚነግረን ቆም ብለው የሚያስቡ ግን ብዙ አይደሉም።

መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዳንድ አስተማሪዎች፥ ትምህርቶች፥ ልማዶች፥ ያለ ሥርዓት ከሚሄዱ ሰዎች ተለዩ ይለናል። ኢየሱስ ሰይጣን ሆኖ ነበር የሚል ሰው ንስሐ ገብቶ፥ 'ተሳስቼ ነበር፤ አሳስቼ ነበር' ሳይል የቆንስላው መሥራችና አመራር ከሚሆን ከዘላለም ፖዝ ጋር አንድነት ምን ማለት ነው? ሥላሴን የማይቀበሉና በሥላሴ የማያምን አሳችን በይፋ ጋብዘው የሚያስሰብኩ እንደ ሐሰተኛ ነቢይ ሚራክል ተካ ወይም ካሳ ኬራጋ ጋር አንድነት ሳይሆን #አንዳችነት መመሥረት ይቻላል። 'እኔና አብ አንድ ነን!' ወይም፥ 'የምትናገረው አካል ይዞ ይከሰታል! ተናግረህ መፍጠር ትችላለህ!' ከሚሉ ጋር #አንዳችነት መፍጠር ይቻላል። ኅብረት ግን አንድነት ግን አይቻልም። ይህ አንድና ሁለት ብቻ ምሳሌ ነው።

ይህ አስተምህሮን የተመለከተ ነው። አስተዳደርንስ? ጥያቄው ስለ ቆንስላው ነውና ቆንስላውን እያሰብን ነው የምመልሰው። ቆንስላው ከጅምሩ መንግሥታዊ፥ ከኃላፊነቱም መንግሥታዊ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን የትውልድ አድራሻውም ቤተ መንግሥት ነው። መሪዎቹ በዲፕሎማቲክ ፓስፖርት የሚጓዙ ሰዎች ናቸው። ይህንን አስተዳደራዊ መዋቅር ምን እናድርገው? ቆንስላው ፈቃድ ሰጪ የመንግሥት ክንፍ ነው። መንግሥትንና ሕግን እየጠቀሰ በእርሱ ላይ በሚናገሩት ሁሉ ሳይቀር ይዝታል ያስፈራራል። ስለ ምን አስተዳደራዊ መዋቅር ነው የምንመካከረው? የቆንስላውን ዓይነት አመራር የተከተለ መዋቅርና አስተዳደርን የተከተለ #አንዳችነት መፍጠር ይቻላል። ያ ግን #አንዳችነት እንጂ አንድነት አይደለም።

2) ሁለተኛው ጥያቄ፥ "ሀሰተኞች ያልካቸውን ነብያት በMedia ሳይሆን በግል በonlineም ሆነ በአካል ፍቅር በተሞላበት መንገድ ልትነግራቸው ምን ያህል ጥረት አድርገሃል?" የሚል ነው። ይህም በተደጋጋሚ የመለስኩት ቢሆንም፥ ቢያስለችም ልድገመው።

እኔም ሌሎቹም፥ ሁሌም የምንገልጠው የሐሰተኞቹ ሐሰት በአደባባይና በማኅበራዊ ሚድያ የተነገረውን ነው። በድብቅና በጓዳ፥ ለጥቂቶች፥ ለኔ ወይም ለእኛ ብቻ የተነገረ የምስጢር ስሕተት የለም። ምላሽ የሰጧቸው ወገኖች ደግሞ አንድና ሁለት አይደሉም። ብዙ ናቸው። እኔ ከእነዚያ ብዙዎቹ አንዱ ብቻ ነኝ።

እነዚህ አሳቾች ለስሕተቶቻቸው የተሰጧቸውን ከወቀሳ እስከ መግለጥ የሚደርሱ ምላሾች አሳምረው ያውቃሉ። ‘ቀርበው ካልነገሯቸው አያውቁም።’ የሚሉት አባባል በራሱ ስሕተት ነው። ሲጀመር እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብቡና መንፈስ ቅዱስን የሚሰሙ ከሆኑ ማንም ሳይነግራቸው በፊት ራሳቸው በራሳቸው ታርመው ይጸጸታሉ። ማንም ሳይነግራቸው። በዚህ የታደሉ ካልሆኑ ደግሞ ከቅርቦቻቸው የሚነግሯቸው አላጡም። ብዙዎቹ አጃቢዎቻቸው መሐይሞችና ተከፋዮች ስለሆኑ፥ ወይ መሳሳታቸውን አያውቁም፥ ወይም ቢያውቁም አይናገሩም። ለገንዘብ እንጂ ለእውነትና ለስሕተት ደንታም የላቸውም።

አሳቾቹ የሚገለጡትን ስሕተቶቻቸውን አሳምረው እንደሚያውቁ የሚጠረጥር የዋኅ ካለ ለማስረዳት እችላለሁ። አንዳንዶቹ ፈጥነው ምላሽ የሚሰጡት ለሰሙት እውነት ነው። ምላሻቸው ግን የንስሐ ሳይሆን ጩምሮና አውቆ የማሳት ነው። ቀድሞ ስተው ሊሆን ይችላል፤ የኋለኛው ግን የማሳትና የእብሪት አካሄድ ነው።

እኔን በተመለከተ፥ የኔ አቋም በግል ከሰዎቹ ጋር ተቀምጦ ምሳ መብላት ወይም ቡና መጠጣትና፥ 'ሕይወት እንዴት ነው?' ማለት አይደለም። ራሳቸው በግል ሊያገኙኝ ወይም እንዳነጋግራቸው በሁለታችን መካከል ሆነው ወንበር ሊያሰናዱልኝ የሞከሩ ጥቂት ያልሆኑ አሉ። ይህ የኔ አሳብ አይደለም ሆኖም አያውቅም። እንከራከር (ወይም debate እናድርግ) ብለውም የጠየቁ አሉ። ይህኛው በግላጭና በአደባባይ የሚደረግ ስለሆነ፥ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ። ከሁለቱ ጋር በክርክሩ ተስማምቼ፤ ግን እነሱ በሰፈሩት ቅድመ ሁኔታ እንዲሆን ብቻ ስለፈለጉ ሰረዣቸዋለሁ። ክርክሮቹን ተስማምቼ የነበረው በአደባባይ የተናገሯቸውን ስሕተቶች በአደባባይ ላሳቷቸው ሰዎች በማሳወቅ ንስሐ እንዲገቡ እድል የሚፈጥር በግልጽ በሚድያ መነጋገር ስለሆነም ነው። እነዚህ አሳቾች ከተናገሯቸው የሚበዙ ገና ያልተናገሯቸውና ያልሰማናቸውም ስሕተቶችም ይኖሯቸዋል እኮ! እነዚያ መፈተሽ አለባቸው። እነዚህ ሰዎች ጥልቅ ፍተሻ ሊደረግባቸው ያስፈልጋል። ክርክር ያንንም ሊያወጣጣ ይችላል።

በግልና በጓዳ ሳይሆን ሕዝብ የሰማው፥ አገር ያወቀው፥ ፀሐይ የሞቀው ነገር ተናግረው በዚያው በተናገሩበት መንገድ መግለጥና ወደ እውነት ማምጣት እንጂ በግል ከነዚህ ሰዎች ጋር ተቀምጬ መነጋገር በግሌ አላስብም። ለአደባባይ ስሕተት የግል ጠረጴዛ ውይይት መፍትሔ እንደማይሆን፥ ለመሸነጋገል ካልሆነ ሁለታችንም እናውቀዋለን። የኔ ለእነርሱ በግል መንገር አጠገባቸው ሆኖ ስሕተታቸውን ከነገራቸው ሰው ምንም የተለየ አይደለም። እኔ ከዚያ የናቁትና አልሰማም ካሉት ሰው ምንም የተለየሁና የተሻልኩ አይደለሁም። አንዱ፥ ‘በዝግ ስብሰባ ተነጋግረን ጨርሰናል’ እንዳለው፤ ከአሳቾች ጋር ዝግ ስብሰባ ብሎ ነገር የለም። ይህ የድርድርና የተኩስ አቁም ስምምነት ጉዳይ አይደለም። አሳቾች ዛሬ ከስሕተታቸው የሚታቀቡት አንድ ሰውን ለማስደሰት ከሆነ ነገ ሌሎችን ለማስደሰት ከበፊቱ የባሱ ጩካኞች ሆነው እንደማይመጡ ምን ዋስትና አለን? እነዚህ አሳቾች በአደባባይ ሰዎችን አስተው አወናብደዋል፤ ማሳታቸውን ያውቃሉ፤ ካላወቁ የነገርናቸውን አሳምረው ሰምተዋል። ከሰሙ እርምጃ መውሰድ ፈንታቸው ነው።

ሌላው ተያያዥ ጥያቄ፥ "ፍቅር በተሞላበት መንገድ ልትነግራቸው ምን ያህል ጥረት አድርገሃል?" የሚለው ነው። ሐሰተኞችን መግለጥንና ስሕተትን ማሳየትን ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ አድርገው የሚያዩ ሰዎች በጣም ያስደነግጡኛል። ስሕተትን መንገር ፍቅርን ማሳየት ያልሆነው ከመቼ ወዲህ ነው? ስሕተትን እያዩ ዝም ማለት ማፍቀር ነው ማለት ነው?

ዘላለም ነኝ።

December 29, 2023




እኔ 'ምለው?

ቆንስላው ግን መፈተሻውን የት እንደጣለ እስካሁን ያወቀና ያገኘለት ማንም የለም ማለት ነው? በቃ በደመ ነፍስ ነው የሚመላለሰው?

. . . . .

የቆንስላው እርማ የተለጠፈበት የሥልጠና ማስታወቂያ ነው። ስነ መለኮትና አስተምህሮ በተጣለበት ምንም ትምህርት ይሰጣል።

January 6, 2024

አስብ አስብና . . .



February 20, 2024

ቆንስላው ሆይ! ከቆንስላነትህ አትውረድ (ነው? ወይስ ከፍ አትበል?) ብቻ በመንግሥት እንባ ጠራጊነትህ ቆይ!



March 8, 2024




ዐፄ ቴዎድሮስ አልባሌ ለብሰው፥ ሌላ መስለው ዜጎቻቸውን ይጎበኙ ነበር። አንድ ምሽት አንድ ባላገር ቤት ሄደው አሳድሩኝ ብለው ገብተው እራት በልተው፥ አውግተው አደሩ። ትኋን ሲልሳቸው፥ እንቅልፍ አጥተው አደሩ።

ማለዳ ተነሥተው ባለቤቱን ወደ ውጭ ጠርተው፥ 'በል ይህን ቤትህን አቃጥልልኝ፤ አሁኑኑ አጋይልኝ!' አሉት።

ባለቤቱም፥ 'ምነዋ ባስጠጋዎት፥ ባሳደረዎት ምን አጥፍቶ ብዬ ላጋየው ቤቴን?' አለ።

'ትኋኖቹን ማቃጠል ስለማይቻል ቤቱ መቃጠል አለበት። ሌላ እኔ አሠራልሃለሁ።' አሉት።

የአገራችን ቆንስላ እንደዚያ ነው። የደም መጣጮች ጎሬ ነው። ቆንስላውን ከትኋኖቹ ማጽዳት አይቻልም። የሚሻለው ከሰዎች ውስጥ ቆንስላውን ማውጣት ነው።

ዘላለም ነኝ።